# ክፍል ሦስት

## ገዢውን ማወቅ



# ምዕራፍ ዐስር

## የገዢው ባህርይ

*ለራሱ (ብቻውን) የተተወ ሰው የራሱ አጥፊ ይሆናል::*

ዓለምን ወደ ለማያዊው መንግሥት ለመለወጥ የገዢው መኖር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አይተናል:: አሁን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ባህርይ በጥልቀት ልንመለከት በጣም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም ምንም እንኳን ገዢው በምድር ላይ ከሁሉ በላይ ቢሆንም፤ ሰዎች ደግሞ ከሁሉ ነገር በላይ ያልተገነዘቡትና ቸልም ያሉት እርሱኑ ነው::

እስከ አሁንም ድረስ ወደ መንግሥቱ ያልገቡ ሰዎች፤ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው ውስጥ ሊጫወተው የሚገባው ሚና እጅግ ወሳኝ እንደሆነ አይገነዘቡትም፤ ምክንያቱም እርሱ ሚስጥራዊና ሊታወቅ የማይችል ነው ወደሚል ድምዳሜ አምርተዋል:: ወይም ደግሞ እርሱ የሆነ ዐይነት መንፈስ እንደሆነ ያስባሉ፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ "መንፈስ" ለሚለው ቃል በዚህ ዘመን የሰጠነው ማብራሪያና በኪንግ ጀምስ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ውስጥ "መንፈስ ቅዱስ" ለሚለው ቃል የተሰጠው "Holy Ghost" የሚለው ቃል ነው:: ገዢውን በሕይወታቸው የተቀበሉ ሰዎች እንኳን ስለማንነቱ የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው:: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት አንዳንዶች እርሱ (መንፈስ ቅዱስ) ዓላማው እነርሱ ደስ እንዲላቸው የሚያደርግ ስሜት ወይም አነቃቂ እንደሆነ ያስባሉ:: እስኪ ገዢው ያልሆናቸውን (እንዲህ አይደለም የምንላቸውን) በመዘርዘር ባሕርዩን እንቃኝ::

### መንፈስ ቅዱስ ያልሆነው

ስብእና የሌለው "ነገር" (IT) አይደለም::

መንፈስ ቅዱስ "ነገር" ወይም "ዕቃ" አይደለም:: አንዳንድ ሰዎች ስብዕና የሌለው ዕቃ አድርገው ስለሚቆጥሩት፤ "ይሰማሃል?" ወይም "እርሱ አለህን?" ሲሉ ይደመጣሉ:: መንፈስ ቅዱስ ስብእና ያለው (ሰውነት) ነው:: በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ስለ እርሱ የስብእና ባህርያት በዝርዝር እንወያያለን::

## መንፈስ ቅዱስ

### ግዝፈ ዓለማዊ "ኃይል" ወይም "ከመረዳት የሚያልፍ አዕምሮ" አይደለም

መንፈስ ቅዱስ፤ በተጨማሪ፣ ስለ ግዝፈ ዓለም እውቀት ይኖረን ዘንድ የምንቀበለውና "ጠልቀን የምንገባበት" የሆነ ዐይነት ኃይል ወይም ከመረዳት የሚያልፍ አዕምሮ አይደለም:: እርሱ በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ንቃተ ህሊና ድምርም አይደለም:: ለአንዳንድ ሰዎች፣ እነዚህ ፍልስፍናዊ ሀሣቦች፤ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር አንድ ሆነውባቸዋል:: ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስን ማንም ሊቆጣጠረው አይችልም፣ ወይም ማንም እውቀቱንም ይሁን ኃይሉን ሊይዘው አይቻለውም:: የእኛ ንቃተ ህሊና አካልም አይደለም:: ከንጉሡ ጋር ግንኙነት በሚኖረንና ለመንግሥቱም ፈቃድ ራሳችንን አሳልፈን በሰጠን ጊዜ እውቀትንና ኃይልን የሚሰጠን የተለየ ህልውና ነው:: እንዲሁ ዝም ብለን ከመፈለግና ከመቀበል ይልቅ በሕይወታችን የመንግሥቱን ዓላማ ለማራመድና እኛን እንደ ንጉሡ ልጆች ለማጠናከር ስለሚሠራው ኃይሉ አመስጋኞች መሆን አለብን::

## መንፈስ ቅዱስ

### ደመና ወይም ጭጋግ አይደለም

አንዳንድ ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲያስቡ፤ ጭስ፣ ወይም ጭጋግ አለበለዚያም ደመና ሆኖ ወደ አንድ ስፍራ የሚመጣ እና አንዳንድ ጊዜም ሰዎች በወለል (በመሬት) ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ይመስላቸዋል:: ይህን ስል ግን መንፈስ ቅዱስ በህልውና በመገኘት ወይም ሊታይ በሚችል መንገድ የሚገልጥባቸው እውነተኛ ጊዜዎች የሉም እያልኩ አይደለም:: ይሁን እንጂ ሁልጊዜም እነኝህን መገለጫዎች የሚፈልጉ ሰዎች ለግምታዊነትና ለፈጠራ የተጋለጡ እንደሆኑ እምናለሁ::

ኢየሱስ መንፈስን በጣም ቀላል ከሆነ ጭጋግ ጋር ከማመሳሰል ይልቅ፤ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር "እርሱ" የሚል ቃል ነው የተጠቀመው፤

> "ግን *እርሱ* የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል:: የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ሁሉ ይነግራችኋል:: *እርሱ* ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና::"

ኢየሱስ "መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ" ማለት ይችል ነበር:: ይሁን እንጂ "እርሱ" የሚለውን ቃል በመደጋገም ተናግሯል፤ በዚህም መንፈስ



ቅዱስ የሆነ 'ኃይል' ወይም 'ደመና' እንዳልሆነ እርግጠኞች እንድንሆን የፈለገ ይመስላል::

## መንፈስ ቅዱስ

### ስሜት ወይም ግንዛቤ አይደለም

እንደገናም፣ መንፈስ ቅዱስ የሆነ ስሜት አይደለም:: እንደሚመስለኝ የዚህ ችግር ከፊል ምክንያት፣ ወደ ህብረት አምልኮ የሚመጡ አንዳንድ ሰዎች ስለሕይወታቸው ሊቋቋሙት ከሚችሉት በላይ በውስጣቸው ጭንቀት አለ:: ይሁን እንጂ ምቹ ሁኔታ ውስጥ መግባት እንደሚችሉ ስለሚሰማቸው እየጮሁ ዙሪያውን ይሮጣሉ:: በመሬት ላይ ይንከባለላሉ፣ እና ይህንን መንፈስ ቅዱስ ነው ይላሉ:: በቃ ዝም ብለው ውጥረትን ነው የሚለቁት::

የመንፈስ ቅዱስን ነገር ለመለማመድ ድምፅ ማለማት አያስፈልጋችሁም:: ከፍተኛ ድምጽ የሚሰጡ ከበሮዎች፤ የቃጭሎች ጩኸት፣ ሁከትና ጭብጨባም አያስፈልገንም:: መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ ብታነቡ፣ አብዛኛውን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ራሱን የገለጠው በፀጥታ ውስጥ እንጂ በስሜት ውስጥ አልነበረም:: ነቢዩ ኤልያስ እንዲህ ዐይነት ልምምድ ነበረው፤

> "እነሆም እግዚአብሔር አለፈ፣ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅና ብርቱ ንፋስ ተራሮችን ሰነጠቀ፤ ዐለቶችንም ሰባበረ፤ እግዚአብሔር ግን በንፋሱ ውስጥ አልነበረም:: ከንፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም:: ከምድር መናወጥ በኋላ እሣት ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳት ውስጥ አልነበረም:: ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምጽ ሆነ:: ኤልያስ ያንን በሰማ ጊዜ ፊቱን በመጎናጸፊያው ሸፈነ፤ ወጥቶም በዋሻው ደጃፍ ላይ ቆመ:: እነሆ ኤልያስ ሆይ በዚህ ምን ታደርጋለህ? የሚል ድምጽ ወደ እርሱ መጣ::"

ይሁን እንጂ ይህን ቃል ለመጨመር እፈልጋለሁ፤ መንፈስ ቅዱስ ስሜት አይደለም፤ ነገር ግን በእርሱ መገኘት ሰላሙን፣ ደስታውንና መጽናናቱን ስትለማመዱ ያለ ምንም ጥርጥር በስሜታችሁ ላይ ተጽእኖን ያሳድራል::

## መንፈስ ቅዱስ ማነው?

### መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መስፋፋት ነው

ስለ መንፈስ ቅዱስ ባህርይ ማወቅ ያለብን ትልቁ ነገር እርሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው:: የእግዚአብሔር መስፋፋት የሚለውን ሀረግ መጠቀም እወዳለሁ:: እርሱ ወደ ሰው እና ወይም ሁኔታ፤ የመንግሥቱን ዓላማና ፈቃድ በግለሰቡ ሕይወት ወይም ሁኔታ ውስጥ ለማድረግ የተዘረጋ እግዚአብሔር ነው::

### ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነው

ቀደም ሲል፤ ኢየሱስ ምንም እንኳን ፍጹም ሰው ቢሆንም ፍጹም አምላክ ስለሆነበት እውነታ ተነጋግረናል:: እግዚአብሔር ወልድ በዓለም ውስጥ ሊተገብር ያለውን የመቤዠት ዓላማ ይፈጽም ዘንድ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆነ:: እነዚህን በአንድ ጊዜ ሁለት ባህርያት የመልበሱ እውነታ ከአብ ጋር ያለውን አንድነትና እኩልነት ፈጽሞ አላጠፋውም:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ፤ "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም:: ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ፤ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ" ሲል ይናገራል::

አስቀድሞ ያለህን ነገር እንደገና ለመያዝ አትሞክርም:: ኢየሱስ፣ ምንም እንኳን በስብእናውና በተግባሩ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ልዩ ቢሆንም፣ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ኢየሱስ ከአብ ዘንድ የተላከው በመንፈስ በኩል ነበር:: ከሰማይ የተላከው መልዕክተኛ ለማርያም፣ ለኢየሱስ እናት፣ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑልም ኃይል ይፀልልሻል፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" ሲል ተናግሯል:: ኢየሱስም ከአብ ጋር አንድ ስለመሆኑ፤ "እኔና አብ አንድ ነን" እና፤ "የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል፤ ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ ማደሪያ እናደርጋለን" ሲል ተናግሯል::

> **መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ ከአብና ከወልድ ጋር እኩል ነው**

"አባት" ብለን ከእግዚአብሔር ጋር እያይዘን የምንናገርበት ቃል ለዋዊ ከሆነው አባት ጋር ወይም ለአንድ "ትልቅ" ወይም "በእድሜ ለገፉ" ሰው ከምንጠቀምበት ቃል ጋር ግንኙነት ያለው አይደለም:: እግዚአብሔር



ከኢየሱስ ክርስቶስ ይልቅ "በእድሜ የገፋ" አይደለም:: እግዚአብሔር አባት ዘላለማዊ እንደሆነ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስም ዘላለማዊ ነው:: ይልቁንም "አባት" የሚለው ቃል እግዚአብሔር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተላከበት ምንጭ እንደሆነ ያመለክታል::

እንደዚሁ ሁሉ፤ መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው፤ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር እኩል ነው:: ዮሐንስ በወንጌሉ፤ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚያመልኩትም በመንፈስና በእውነት ሊያመልኩት ያስፈልጋቸዋል" ሲል ጽፏል:: ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፤ "ሌላ አጽናኝ" ይለዋል፤ እርሱም ኢየሱስ በምድር የጀመረውን ሥራ የሚቀጥል ነው:: በመሆኑም እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ይሁን እንጂ ራሱን በሶስት የተለያዩ ስብእናዎችና አሠራሮች ይገልጻል::

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ዳሩ ግን እኔ <u>ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ</u> አጽናኝ፤ እርሱም ከአብ የሚመጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ . . . " ኢየሱስም ሆነ መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም በምድር ላይ መሠራት የነበረበትንና አሁንም የሚያስፈልገውን ሥራ ለማከናወን የወጡት ከአብ ዘንድ ነው:: ኢየሱስ ይቤዠን ዘንድ ከአብ ተላከ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ኃይልን ያለብሰን ዘንድ በኢየሱስ ተላከ:: ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረንን ግንኙነት እንደገና ሊያድስ ተላከ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ አዲስ ወደሆነ ወደ መንግሥቱ ሕይወት ሊያስገባን ተላከ::

የሥላሴ አምላክን ጽንሰ ሀሣብ በውሃ ምሳሌ ውስጥ ልገልጠው እወዳለሁ:: በፈሣሽ መልክ ያለው ውሃ ልክ እንደ እግዚአብሔር አብ ነው፤ እርሱ ምንጭ ወይም መነሻ ነው:: ጥቂት ውሃ ወስዳችሁ ብታቀዘቅዙት ጥጥር በረዶ ይሆናል:: በረዶው በኢየሱስ ይመሰላል፤ ስጋ የሆነው ቃል፤ እርሱ የሚጨበጥ ነበር፤ ሊታይና ሊዳሰስም የሚችል ነበር፣ የሚሰማና የሚነካ ነበር:: ያንኑ በረዶ ወስዳችሁ ደግሞ በሆነ ማሰሮ ውስጥ ክተቱና እስኪተን ድረስ አሙቁት፤ ወደ ተንነት ይለወጣል:: ተን (እንፋሎቱ) እንደ መንፈስ ቅዱስ ነው፤ ተጽእኖ ማምጣት የሚችልን ኃይል የሚያመነጭ፤ ነገር ግን ሊታይ የማይችል ነው:: በረዶም ይሁን ተን አስቀድሞ ወደነበሩበት ወደ ፈሳሽነት መለወጥ ይችላሉ:: ሦስቱም የውሃነቱ ባህርይ ያላቸው ናቸው፤ ይሁን እንጂ በተለያዩ ገጽታዎች ይገለጣሉ::

### እንደ እግዚአብሔር ያለ ክብር ይቀበላል

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለመሆኑ ሌላው ማረጋገጫ፤ እርሱን መሳደብ ስለሚያስከትለው ውጤት ኢየሱስ የተናገረው ቃል ነው:: "እውነት እላችኋለሁ፣ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ፤ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይቀትም::" ኢየሱስ

ፈጽሞ ምህረት የማይገኝበት ብቸኛው ኃጢአት እንደሆነ የተናገረው፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሠራን ሃጢአት ነው:: ይህንን ያለው ለምን ነበር? ይህንን የተናገረበት ምክንያት (1) ሰዎች በኢየሱስ ስራ ከኃጢአታቸው መንጻት እንደሚያስፈልጋቸው ሰዎችን የሚወቅስ በመሆኑና (2) በመንፈስ እንድንወለድ የሚያስችለን እንዲሁም ወደ ሰማያዊው መንግሥት የሚያመጣን እርሱ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ እምናለሁ:: በመሆኑም አንድ ሰው ሙሉ ለሙሉ ለመንፈሱና ለስራውም ልቡን የሚያጠነክር ከሆነ፤ በክርስቶስ በኩል ወደሚገኘው ምህረት ሊቀርብ አይችልም::

ኢየሱስ ክርስቶስ አንጽቶናል፣ አብ ይቅር ብሎናል፣ መንፈሱ ደግሞ አድሶናል:: የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ፤ ከመዝሙር ምዕራፍ 95 ጠቅሶ እንዲህ ጽፏል፤ "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል፡- ዛሬ ድምጹን ብትሰሙ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ":: በሌላ አባባል፤ ድምጹን ብትሰሙ፣ ወቀሳውን ብታደምጡ፤ "ጊዜው አሁን ነው" ሲል ብትሰሙ፤ ልባችሁን እታጠንክሩ፤ ምክንያቱም እናንተን መጣራት የሚያቆምበት ቀን ይመጣል ማለቱ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለረዥም ጊዜ እንደሚታገስ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ እስከ "ለዘላለሙ" ይታገሳል አይለንም:: ሞኝነትን ለረዥም ጊዜ ይፈቅዳል፣ ነገር ግን ለረዥም ጊዜ ብቻ::

"ሃይማኖቱን የከዳ ሰው" የሚሰው ቃል የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን መንፈስ ለማድመጥ ጨርሶ ወደ ማይችልበት ሁኔታ ውስጥ የገባን ሰው ነው:: መንፈስ ቅዱስ አንተን መውቀሱን እንዲያቆም አትፈልግም:: መንፈስ ቅዱስ ንስሃ መግባት እንዳሰብህ፣ ምህረትን እንድትቀበልና ወደ መንግሥቱ እንድትገባ ሲወቅስህ ፈጥነህ ወደ እርሱ መሮጥ ይገባሃል! ለምን? ምክንያቱም ያ ማለት አሁንም ከእግዚአብሔር ጋር በመልካም ግንኙነት ውስጥ አለህ፣ አንተን ሊያናግርህ ይችላል ማለት ነው:: ሰዎች ምን ይሉኝ ይሆን? እያልክ እያሰብክ፤ የክብርህ ጉዳይ ምላሽ ከመስጠት እንዳያግድህ ተጠንቀቅ:: ይልቁን መጨነቅ ካለብህ ልትጨነቅበት የሚገባህ ነገር መንፈስ ቅዱስ አንተን መናገሩን እንዳያቆም ነው::

በሰማይና በምድርም ሁሉ እጅግ ከፍ ያለውን እንደምታደምጠው ተስፋ አደርጋለሁ:: እርሱ ሊገመት ከሚችል በላይ፣ ብዙዎች ሊያዩዋቸው ተስፋ ከሚያደርጓቸው መላእክት ይልቅ ታላቅ ነው:: መላእክት ለአስተዳደሩ የሚሠሩ ናቸው፤ <u>እርሱ</u> ግን አስተዳደሩ ነው::

| |
|---|
| መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይወቅሳል፤ ዳግም በመንፈስ እንዲወለዱም ያስችላቸዋል:: |



## መንፈስ ቅዱስ የተለየ ጠባይ፣ ችሎታና ፍቃድ ያለው አካል ነው

ቀደም ብለን እንዳየነው በመጀመሪያ ደረጃ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጫ ነው:: ሁለተኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ሰብእና ነው:: አንድ ሰብዕና ከሌሎች ይልቅ ልዩ የሚያደርጉት የተለዩ ጠባዮችና ችሎታዎች ይኖሩታል፤ በመሆኑም እርሱ የተለየ ህልውና ነው፣ ገዢው የተለየ ሰብእና፣ ጠባይና ፈቃድ አለው:: ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ላይ፣ ሰማያዊ ወኪል ሆኖ የሚኖር ገዢ ዋንኛ ፍላጎቱ እኛ በምድር ላይ የንጉሡን ዓላማ እናደርግ ዘንድ ነው::

ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሰብእናና ስለተግባሩም በመግለጥ እንደተናገረው፤ ከጠባዮቹ መካከል ሁለቱ የማስተማርና የመምራት ብቃቶቹ ናቸው:: እርሱ "ስሜት" አይደለም:: "ስሜት" ወይም "አንድ ኃይል" ገዢ ሊሆን አይችልም:: "ጭጋግ" ሊያስተምር ወይም ሊመራ አይችልም:: የመንግሥቱ ዜጎች የሆኑ ብዙ ሰዎች ከገዢው ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት የላቸውም፤ ምክንያቱም በእነርሱ ውስጥ እጅግ የከበረው እርሱ መኖሩን አልተገነዘቡም:: የከበረው እርሱ::

## መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ ሕዋሶች አሉት

መንፈስ ቅዱስ "ሕዋሶች" ደግሞ አሉት፣ እነርሱም የሰብእናው አካል ናቸው:: ይህም ማለት፣ ልክ የሰው ልጆች አካላዊ የሆኑ ሕዋሶች እንዳሏቸው፣ እርሱ ደግሞ መንፈሳዊ የሆኑ ሕዋሶች አሉት ማለቴ ነው:: በመንፈሳዊ ሁኔታ ስንናገር፣ መንፈስ ቅዱስ ያያል፤ ይሰማል፤ ይዳስሳል፣ ያሸታል ወይም በምድርና በምድር ላይ ከሚኖሩት ሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙ ነት ነገሮችን ይረዳል ማለቴ ነው::

## መንፈስ ቅዱስ ስሜት ብቻ ሳይሆን ትልቅ ስሜት አለው

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ::" እርሱ የሚለንን ላለማድረግ እልከኞች ስንሆን፣ ሰማያዊውን መንግሥት በሚቃወም ሁኔታ ብንመላለስ ወይም እርሱን ችላ ብንለው ልናሳዝነው እንችላለን::

አሁን ማተኮር የምፈልገው እርሱን ችላ በምንልበት ሁኔታ ላይ ነው:: እስኪ እንዲህ አስቡ፣ አንድን ሰው ችላ ብትሉት በአጠቃላይ ከእናንተ ጋር መነጋገሩን ያቆማል:: በጣም ችላ እያላችሁት በሄዳችሁ መጠን እርሱም የዚያኑ ያህል ችላ ይላችኋል:: ለምሳሌ እኔን ልትቀበሉኝ ፈቃደኞች ካልሆናችሁ፤ እኔ ለእናንተ ምንም ጠቀሜታ የሌለኝ ሰው እንደሆንኩና ለእኔ ምንም ፍላጎት የላችሁም ወደሚል ድምዳሜ እደርሳለሁ:: ወይም ደግሞ እየተናገርኳችሁ ሳለ ችላ ካላችሁኝ እነዚህ ሰዎች ሊሰሙኝ ፍላጎት የላቸውም ወደሚል ስሜት ላዘነብል እችላለሁ:: ኢየሱስ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል" ብሎናል:: እኔ

በክፍል ውስጥ የማስተምር አስተማሪ ስለነበርኩ፣ አንድ ነገር ልንገራችሁ፤ ለአንድ አስተማሪ በክፍል ውስጥ ለመማር ፍላጎት ከሌላቸው ተማሪዎች የሚበልጥ የከፋ ነገር የለም።

መንፈስ ቅዱስ ችላ ስንለው ችላ ማለታችንን የሚያውቅ ስብእና እንደሆነ መገንዘብ ይኖርብናል። ትምህርቱንና ምሪቱን ችላ ስንል፤ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ፍላጎት እያጓደልንበት ነው። በተጨማሪ ደግሞ በመንግሥቱ ውስጥ የመማርና የማገልገል እድላችንን እያጣነው እንሄዳለን። በመሆኑም ይህን በማድረጋችን አሉታዊ በሆነ ሁኔታ የምንጎዳው እኛ ብቻ አይደለንም። ገዢው ለጎረቤትህ ምግብ እንድትሰጠው አምስት ጊዜ ያህል ገፋፍቶሃል እንበል። መልስ ካልሰጠህ በመጨረሻው በዚህ ጉዳይ ላይ መናገሩን ያቆማል። እናም ሁለት ነገሮች ይከሰታሉ፤ አንተ ከባርኮት ትጎድላለህ፤ ምናልባት ጉረቤትህ ደግሞ መራቡን ይቀጥላል።

ወይም ደግሞ ገዢው በሌሊት ተነስተህ ስለ አንድ ሰው እንድትጸልይ ገፋፍቶህ ይሆናል እንበል፤ አንተ ግን እንዲህ፤ "በጣም ደክሞኛል፤ በጣም አድካሚ የሆነ ቀን ነው ያሳለፍኩት፤ በመሆኑም መተኛት ያስፈልገኛል" አልክ። መንፈስ ቅዱስ መልሶ፤ "ትክክል ነህ፤ ነገር ግን አንድ ሰው እርዳታ ይሻል፤ እኔ ደግሞ ለመማለድ የምገለገልበትን አንድ ሰው እሻለሁ፣ ምክንያቱም ሰማያዊው መንግሥት በምድር ላይ የሚሠራበት መንገድ እንዲህ ነው" ይልሃል። አንተም እንዲህ "ይሄ ድምጽ ዝም ብሎ የራሴ የሆነ ግምት ነው፤ እኔ ደክሞኛል" ብለህ ታስባለህ። እናም በአልጋህ ውስጥ ቆየህ፣ ደግመህም ያንን ግፊቱን አልሰማህም። በሚቀጥለው ቀን አንድ ሰው በአደገኛ ወይም በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደነበር፣ እናም የአንተ ፀሎት በአስቸኳይ የሚፈለግ እንደነበር ትረዳለህ።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከምናደምጠው ይልቅ ሌሎች ሰዎችን አብልጠን እናደምጣቸዋለን። የእርሱን ምክር ከመሻት ይልቅ የሌሎች ሰዎችን ምክር እንፈልጋለን። አንዳንድ ጊዜ፤ የኛን ትኩረት ለማግኘት ሲል የእርሱን ህልውና የምናውቅበትን የኛን መረዳት ይወስደዋል።

አንዳንድ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ለረዥም ጊዜ አልሰሙም። ለምን? በማለዳ ይነሳሉ የቀኑን ተግባራቸውን ከመጀመራቸው በፊት እያመሰገኑትም። ውሳኔ ሲሰጡ፣ ገንዘባቸውን በሥራ ላይ ሲያውሉ፤ ስራቸውን ሲያንቀሳቅሱ፣ ንግዳቸውን ሲያከናውኑ ወይም ት/ቤት ሲሄዱ እያሳውቁትም ወይም ወደ እርሱ አያቀርቡም። በመሆኑም እነርሱን በሚመለከት ዝም ይላል።

ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ማድረግንና ማድመጥን ልትማሩ ያስፈልጋችኋል። በቃሉ በኩል ይናገረናል፤ በልባችን



በኩል ይናገራል እንዲሁም ለሆኑ ሁኔታዎች በማነሳሳትና ውስጣችንን በሀሳቡ በመሙላት ይናገረናል። እርሱን ችላ አለማለትንና ድምጹንም መስማት ልንለማመድ ያስፈልገናል፤ ይልቁንም በማንነታችን የሚደሰት እና ምን እንደምንሠራ፣ በመንግሥቱ ውስጥ ያለንን ሚና እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ እንደምንተገብር በቅርበት ሆኖ የመከታተል ፍላጎት ያለው ስብእና ስለሆነ ልንቀበለው ያስፈልገናል።

> ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ህብረት ማድረግንና ድምጹን መስማትን ልንማር ያስፈልገናል

## በእኛ የተገለጠው የገዢው ባህርይ

እስኪ አሁን ደግሞ ባህሪውን አስመልክቶ በተገለጠው መሠረት ገዢው በእኛ የሚሠራውን እንመልከት። መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ያለውን የተለየ ሚናና ኃላፊነቶች መጽሐፍ ቅዱስ ያብራራል፣ ይተረጉማልም። በተጨማሪም፣ በሁሉም ሥራዎቹ ውስጥ፣ ገዢው የሚተገብረው በንጉሡ ቃል መሰረት ብቻ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "እርሱ ግን የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፤ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና፣ የሚመጣውንም ይነግራችኋል እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝም ወስዶ ይነግራችኋልና።"

## አማካሪና አጽናኝ

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አለ፤

"አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤ እኔም የነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል"

እኔም አብን እለምናለሁ፣ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል።"

ከላይ ባየናቸው ጥቅሶች ውስጥ "አጽናኝ" ለሚለው ቃል የተሰጠው የግሪክ አቻ ቃል "ጳራቅሊጦስ" የሚል ሲሆን፤ ይህም የሚማልድ፣ የሚያማክር እንዲሁም "ጥብቅና የሚቆምና የሚያጽናና" ማለት ነው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች፤ "ረዳት" የሚል ቃል ይጠቀማሉ። ይህም የሚገልጸው ከአጠገባችን (ከጐናችን) ሆኖ የሚረዳንን ሰው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የተጠሩለትን ሕይወት መኖር ይችሉ ዘንድ በገዢው ስብእና በኩል ወደ እነርሱ ተመልሶ እንደሚመጣ ቃል ገብቶላቸዋል፤ "ጥቂት ጊዜ አለ አታዩኝም ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ ታዩኛላችሁ።"

ሰዎች እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፣ "እማኝ" (የመንግሥቱ ዜጋ) ለመሆን እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን እኔ ለዚህ የሚያበቃ ጥንካሬ የለኝም። ይህን ላለማድረግ እና ያንን ለማድረግ በቂ ጥንካሬ ሲኖረኝ ያኔ መንግሥቱን እቀበላለሁ።" እነኝህ ሰዎች ዛሬም ውሳኔ አላደረጉም፣ ምክንያቱም በመጀመሪያ መጠንከር እንዳለባቸው ያስባሉ። ምናልባት አንተም ራስህን በራስህ መንገድ ለመለወጥ በዚሁ ሁኔታ ውስጥ እየታገልክ ይሆናል። ንጉሡ እንዲህ ይለናል፣ "ተመልከት፣ የመንግሥቱን ባህል ለመማር የምትፈልግ ከሆነ፣ ከሰማይ (ከአገር ቤት) እርዳታ ያስፈልግሃል።" ገዢውን ወደ ሕይወትህ መቀበል እንድትለወጥ ያስችልሃል። አስተሳሰብህን እንዴት እንደምትለውጥና እንዴት እንደምትኖር መንገዱን ያሳይሃል።

እንደዚሁ ደግሞ፣ ምንም እንኳን የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች ብትሆኑም፣ አንዳንዶቻችሁ ተስፋ ቆርጣችኋል፣ ምክንያቱም ወደ ጨለማው መንግሥት ባህርያትና ተግባራት ተመልሳችሁ እንደምትወድቁ ይሰማችኋል። ገዢው ግን እንዲህ ይላችኋል፣ "እኔ እንደገና ፀንታችሁ እንድትቆሙ እረዳችኋለሁ።" ይህ የእርሱ ሥራ ነው፣ እርሱ ሥራውን በእናንተ ላይ አያቋርጥም።

ኢየሱስ፣ ዘጠና ዘጠኙን በጎች በሜዳ ትቶ የጠፋውን አንድ በግ ለመፈለግ በወጣው እረኛ ምሳሌ፣ ንጉሡ ለአንተ የሚያደርገውን ከፍተኛ ጥንቃቄ ገልጾልሃል። ይሄ ግን ተመልሰን ወደ ጨለማው መንግሥት ባህርያት እንድንሄድ ፈቃድ አይሰጠንም። አንድ ጊዜ በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ከገባን፣ ሆነ ብለን በቀደመው አሮጌ መንገዳችን መመላለስ አይጠበቅብንም። አንዳንድ ሰዎች ሆነ ብለው ከመንግሥቱ ባህርይ ተፃራሪ የሆነ ነገር ያደርጉና፣ ወዲያውኑ ደግሞ ንጉሡ ይቅርታ እንዲያደርግላቸው ይፈልጋሉ። ይህ የመንግሥቱ ዜጋ ሆነን በእውነት መለወጣችንን የሚያንፀባርቅ ነገር አይደለም። በርግጥ በሰማያዊው መንግሥት መለኪያ ለመኖር የምንሻ ከሆነ፣ ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ብንሳሳትም፣ ገዢው በመለኪያው መሠረት እንድንኖር ይረዳናል። እርሱ ስኬታማዎች እንድንሆን ይፈልጋል።

## መሪና አስተማሪ

ኢየሱስ ስለ ገዢው እንዲህ ሲል ተናገረ፣

> "ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፣ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፣ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል።"

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፣ ገዢዎች በቅኝ ግዛት ውስጥ የሚቀመጡት መረጃ ለማስተላለፍ ብቻ አይደለም፣ ይልቁንም የግዛቲቱ ነዋሪዎች አስተሳሰባቸው፣ አደራረጋቸውና የአኗኗር ደረጃቸው በአገር ቤቱ



መለኪያ፣ ልማድና - ሁለንተናዊ ባህል መሠረት እንዲሆን ለማሠልጠን ነው። ይህ ደግሞ አጠቃላይ ትምህርትንና በየግል የሚሰጥ ሥልጠናን ይጨምራል።

ገዢው ልኡላዊ ከሆነው ዙፋን ወደ ቅኝ ግዛት የተላከ በመሆኑ፣ የልዑላዊውን (የበላዩን) ፍላጎት ያውቃል። በዚሁ ዓይነት መንገድ፣ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃሎችና ለእኛ የተወልንን መመሪያዎች እውነት ልንረዳ እንድንችል የሚያደርገን፣ ከሰማይ የሆነው ገዢ ብቻ ነው። ስለ ንጉሡና ስለመንግስቱም ዋና ወይም ትክክለኛ ወደ ሆነ መረጃ የሚያገናኘን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። እንደ ንጉሡ የልብ ሃሣብ ካልሆኑ ስህተት ከሆኑ ነገሮችና ከሌሎች ሰዎች አስተሳሰቦች ይጠብቀናል።

በቅኝ ግዛት ውስጥ ገዢ ከሚኖሩት ተግባራት መካከል አንደኛው፣ ሉአላዊው ለዜጐቹ ባስተላለፋቸው መመሪያዎች ወይም ቃሎች ምን ማለቱ እንደሆነ መተርጎም ነው። ባለፍነው ክፍል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ "መካር" ተብሎ ተጠርቶ አይተናል። "መካር" የሚለው ቃል ህግን ከመተርጐም ጋር ይያያዛል፣ በመሆኑም ገዢው የንጉሡን ቃሎች ወደ ሕይወታችን እያመጣ ሕጉን ያብራራልናልም።

ነቢዩ ኢሳያስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ - የጥበብና የማስተዋል የምክርም መንፈስ ያርፍበታል"። በእኛ ደግሞ ይህ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ በውስጣችን ይኖራል። እውቀት መረጃ ሲሆን ጥበብ ደግሞ እውቀት እንዴት ተግባራዊ እንደሚደረግ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ ጥበብ እውቀትን አግባብ ባለው መልኩ መጠቀም ነው። ገዢው እውቀታችንን እንዴት እንደምናወጣና ለሕይወታችን እንዴት እንደምንተገብረው ያሳየናል። በዓለም ላይ ትክክለኛና ተግባራዊ የሆንን ሰዎች እንድንሆን የሚያስችለን እርሱ ነው። በአንዳንድ የሃይማኖት ክበባት፣ ይህ የሚታሰበው በተቃራኒው ነው። ሰዎች እንግዳ በሆነ መንገድ ነገሮችን እንዲተገብሩ የሚያደርጋቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል። ይሁን እንጂ እውቀታችንን በቤተሰባችን፣ በንግዳችን፣ በማህበረሰባችን ውስጥ፣ በሀገራችንና ዓለም ዓቀፋዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደምንችል የሚያሳየን እርሱ ነው።

> ገዢው መንፈሳዊ ዕውቀትን ዘርፈ ብዙ ለሆኑ ለሕይወት ጉዳዮቻችን እንዴት እንደምንጠቀም ያሳየናል።

## ረዳትና አስቻይ

ንጉሡ ልጅ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ ራሱን በሚመለከት ከነቢዮ ኢሣያስ መጽሐፍ ጠቅሶ እንዲህ አለ፣

> "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድውዮች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፤ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ፤ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል::"

ሉአላዊው ለቅኝ ግዛቱ የሚፈልገውን ነገር ሲያስታውቅ፤ ነገሩ እንዲከናወን ዜጎቹን ማበረታታትና መከናወኑንም ማረጋገጥ የገዢው ሥራ ነው:: መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ ሲፈጽም፣ በግዛቲቱ ላይ እንደ ምክትል ገዢነታችን ሚናችንን በመወጣት ለርሱ ዓላማና መሻቱ መተባበር ይጠበቅብናል:: እዚህ ያለነው "የየራሳችንን" መንግሥት ለመመስረት አይደለም:: በዚህ ያለነው የምንወክለውን ሉአላዊ መንግሥታችንን ለመመስረት ነው::

## የመንግስቱን ዓላማ በማሟላት ረገድ

ከዚህ በላይ ከኢሳያስ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሰው ምንባብ በምድር ላይ ያለውን የመንግስቱን የትኩረት አቅጣጫ፣ ማለትም በምድር ለሚኖሩ ሰዎች ስለ አብ የተስፋ ቃል በመንገር፣ ከጨለማው አገዛዝ ነጻ እያወጣቸው የመንግሥቱን ባህርይና እንዴት ወደርሱ እንደሚገቡበት እያሳያቸው ያብራራል:: እነኝህን ነገሮች ሁሉ ማከናወን እንድንችል የሚረዳን ገዢው ነው::

የንጉሡ የመጨረሻ ዓላማው በነቢዩ እንባቆም አፍ እንደተናገረው ነው፤ "ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለችና::" እንግዲህ መንግሥቱን በተመለከተ ይህንን ቃል እንደ መመሪያ አድርገን ልንወስደው እንችላለን:: በተጨማሪም፤ የእግዚአብሔር ክብር የእግዚአብሔርን ባህርይ ያመለክታል:: ኢየሱስ፣ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው፣ ደቀመዛሙቴ አድርጓቸው" ብሎ እንደተናገረው በገዢው ምሪት ሆነን መፈፀም አለብን:: ትንቢቱ የሚፈፀመውም በዚህ መንገድ ነው::

ገዢው የመንግሥቱን ባህል አሁን በምድር ላይ ወደሠለጠነው ወደ ጨለማው (ባዕድ) መንግሥት ባህል እንድናመጣው ይጠራናል:: ቀደም ሲል፤ ደቀመዝሙር ማድረግ ማለት የመንግሥቱን ፍልስፍናና እሴቶች ማስተማር እንደሆነና በዚህም ተማሪዎቹ በንጉሡ የአመለካከት ቅኝት ውስጥ እንደሚዘፈቁ ተመልክተናል:: "ዓለም" የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "ኢትኖስ" ማለት ሲሆን የሚያመለክተውም ዘርን ወይም የሰዎችን ቡድኖች ነው:: የትኛውም በምድር ላይ ያለ የተለየ የሰዎች ቡድን ወደ መንግሥቱ ባህል ሊለወጥ ያስፈልገዋል::



የባሃማስ ንጉሣዊ ገዢ የነበሩት በቅኝ ግዛቲቱ ውስጥ የተለያዩ የማሻሻያ ፕሮጀክቶችን፣ እንደ መንገዶችን የመጠገን ሥራ የመሳሰሉትን እንዲሠሩ ኮምሽነሮችንና የህዝብ አማካሪዎችን ከዚያቹ ቅኝ ግዛት በመወከል ይሾማቸው ነበር:: እንደዚሁ ሁሉ፣ ገዢው ለኛ በዓለም ውስጥ ሰማያዊ አስተዳደርን በመወከል መልካም ሥራ እንሠራ ዘንድ ሥልጣን ይሰጠናል:: ጳውሎስ እንደጻፈው፤ "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን::"

## ወደ ተሰጡን ስጦታዎች ምንጭ እንደገና በማገናኘት ረገድ

እያንዳንዱ ሰው የተወለደው ከእግዚአብሔር ከተሰጡት ስጦታዎች ጋር ነው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ስጦታዎች ወደ ላቀ የብቃት ደረጃ ደርሰው ለመንግሥቱ አገልግሎት እንዲውሉ ከተፈለገ፣ ከዋናው ምንጫቸው ጋር እንደገና መገናኘት ይኖርባቸዋል:: ማንም ቢሆን ከፈጣሪው መንፈስ ጋር ካልተገናኘ በቀር፤ የስጦታውን እውነተኛ ባህርይ በትክክል አያውቀውም:: ከዚህም በላይ፣ ገዢው ስጦታዎቻችንን እኛ ልናመጣ (ልናሳድግ) ከምንችለው ደረጃ በላይ በማሳደግ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል:: ጳውሎስ፣ ነቢዮ ኢሣያስን በመጥቀስ እንዲህ ጽፏል፤ "ነገር ግን ዓይን ያላየችው፣ ጆሮም ያልሰማው፣ በሰውም ልብ ያልታሰበው፣ እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንደተጻፈ እንዲህ እንናገራለን:: መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና፤ ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው::"

> ገዢው የመንግሥቱን ባህል ወደ ጨለማው ባህል እንድናመጣው ይጠራናል::

ገዢው ከስጦታዎችህ ምንጭ ጋር እንደገና የሚያገናኝህ በመሆኑ፤ የተሰጠህ ምን እንደሆነ ልትገነዘብ ትችላለህ፤ ይህም የስጦታዎችህን እሴት ብቻ ሳይሆን መጠናቸውንም እንድታውቅ ያደርግሃል:: በሌላ አገላለጽ፤ ማንኛውም ሰው ቢሆን በራሱ የአዕምሮ ችሎታ ብቻ፤ ንጉሡ ለመንግስቱ ዓላማ በውስጡ ያስቀመጠውን ስጦታ ሊለየውና ሊገነዘበው አይችልም:: ስለዚህም ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጥህ ያስቀመጠልህ በርግጥ ምን እንደሆነ ለማወቅ ካስፈለገህ፤ ከገዢው ጋር መገናኘት የግድ የሚያስፈልግህ::

ጳውሎስ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፤ "እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን እናውቅ ዘንድ፤ የእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም::" ይሄ ቃል የሚነግረን፣ መንፈስ ቅዱስ ካልገለጠልን በስተቀር ያለን ምን እንደሆን እንኳን ልንገነዘበው እንደማንችል ነው:: ይህ እውነት ዓላማህንና ያለህን እምቅ ችሎታ

ውጤታማ ለማድረግ እጅግ የሚጠቅም ነው። ስለራስህ ያሉ ነገሮችን እንኳ፤ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ልብ ካሉ ጥልቅ ነገሮች ጋር እንደገና ካላገናኘህና ስጦታዎችህን በውጤታማ በሆነ መልኩ እንድትጠቀምባቸው ካላስቻለህ በስተቀር በጭራሽ ልትገነዘባቸው አትችልም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ጳውሎስ፤ "ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም" ሲል ጽፏል። ያለ ገዢው፤ በውስጣችን ጥልቅ ውስጥ የተቀመጠውን በጭራሽ ልንገነዘብ አንችልም። ከእግዚአብሔር መንፈስ ውጭ እኛ ማን እንደሆንን ልናውቅ አንችልም። ስለዚህም ነው አብዛኞቻችን ካለን እምቅ ችሎታ በታች በጣም በወረደ ሁኔታ የምንኖረው።

እዚህ ጋ፤ አብረን የተወለድናቸው ስጦታዎች እንዳሉና መንፈሱን በተቀበልን ጊዜ ደግሞ በተጨማሪ የተሰጡን ስጦታዎች እንዳሉ ልብ ልንል ይገባል። በእነኝህ በሁለቱ አይነት ስጦታዎች መካከል ልዩነት እንዳለ አምናለሁ፤ በመሆኑም በሚቀጥሉት ምዕራፎች ስለ "መንፈስ ስጦታዎች" በሰፊው እናወራለን። ይሁን እንጂ በእዚህ ስፍራ ላይ እየተናገርኩላቸው ያለሁት ስጦታዎች፤ በምድር ላይ ለመንግሥቱ የተለየ ዓላማ (ተግባር) እንድትፈጽም አብረውህ ስለተወለዱ ስጦታዎች ነው። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ በእነኝህ ስጦታዎች እንጠቀም ዘንድ ኃይልን ያለብሰናል። ኃይልን የሚያለብሰን ግን ብቃት እንዲኖረን ለማድረግ አይደለም፤ ምክንያቱም ያ ብቃት ቀድሞውኑ በእኛ ውስጥ አለ። ይልቁንም ኃይልን የሚያለብሰን ሙሉ ለሙሉ ስጦታዎቹን ለእኛ በመግለጥና እንዳሉን እንኳን የማናውቃቸውን ስጦታዎች በማስተዋወቅ ነው። ከዚህም በላይ፤ ንጉሡ ስጦታዎቹን የሰጠን ሌሎች ሰዎችን ለመጥቀም በመሆኑ፤ ለግላዊ (ለስግብግብ) ዓላማ ሳይሆን ለመንግሥቱ ዓላማ እንዴት እንደምንጠቀምባቸው ያሳየናል።

## ወቃሽ

ኢየሱስ ገዢውን አስመልክቶ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አለ፤

> "እርሱም መጥቶ፤ ስለ ኃጢአት፤ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዢ ስለተፈረደበት ነው"

ከላይ ባሰፈርነው ጥቅስ ውስጥ፤ "ዓለም" የሚለው ቃል ሰዎችን የሚመለከት አይደለም፤ ይልቁንም ስርዓትን ወይም የአመለካከት ቅኝትን የሚያሳይ ነው። በሰዎች ባህርይ ላይ ተጽእኖ የሚያስከትለው በጨለማው መንግሥት የተመሠረተው ሥርዓት ነው። በመሆኑም፤ ከመንግሥቱ



ውጭ ያሉት ሰዎች ምህረት እንደሚያስፈልጋቸውና በሰማያዊው አስተዳደር ከሚገኘው አባታቸው ጋር መገናኘት እንደሚገባቸው በመንገር የሚወቅሳቸው ገዢው ነው። በተጨማሪም የመንግሥቱን ዜጎች ከመንግሥቱ ባህርይ ተፃራሪ ስለሆነው ዝንባሌአቸውና ድርጊታቸው ይወቅሳል። በመንግሥቱ የሕይወት መስኪያ ልክ መኖር እንድንመርጥ በአዕምሯችን በኩል የሚሠራው ገዢው ነው።

መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን "ተከቶ" እንዲሠራ እንዳልተሰጠን ልብ ልንል ይገባል። እርሱ ያነሣሣናል እንጂ በጭራሽ አያስገድደንም። በሌላ አገላለጽ፤ የመንግሥቱ ዜጎች ሁሉ የሚጠበቅባቸውን፣ የመንግሥቱን የሕይወት መስኪያ ልክ፣ ህጉን፣ ስርአቶቹንና የመንግሥቱን ባህል እንዲገነዘቡ ያደርጋል፤ በተጨማሪም የእነዚህን ነገሮች ጥቅም በመግለጥ ያበረታታቸዋል።

ንጉሡ - አባት የራሱን ዜጐች በመቆጣጠር ተግባር ውስጥ አይደለም ያለው። እርሱ የሚፈልገው ልጆቹ እርሱ የሚሻውን እንዲሹ ነው። ፈቃዳችንንም ያከብራል። ገዢው የአብ ፈቃድ ምን እንደሆነ ያሳየናል፤ ፈቃዱንም ለመፈፀም ከርሱ ጥበብ፣ ጥንካሬና ኃይል በፈለግን ጊዜ ይረዳናል።

## ወደ እግዚአብሔር ማሪኪ

ሰዎችን ወቃሽና አሳማኝ በመሆን ረገድ፣ መንፈስ ቅዱስ በንጉሡ ዙፋን ፊት የመንግሥተ ሰማይ መለኮታዊ ማራኪ ነው። ገዢው በሰዎች ሕይወት ውስጥ ሲሠራ፤ በትህትና ለአብ ይማርካቸዋል። በተጨማሪም እርሱ የሚያጣጥል አይደለም። ነቢዩ ሆሴዕ፤ ንጉሡ ለሕዝቡ ያለውን በዘገበ ጊዜ፣ "በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኳቸው" በሚል ውብ በሆነ ተምሳሌታዊ አቀራረብ ገልጾታል።

> ልጆቹ እርሱ የሚሻውን እንዲሹ ንጉሡ ይፈልጋል

## አስተባባሪ

እውነተኛ የሆነ ገዢ የንጉሡን ፍላጎት የሚዳረር ማንኛውንም ነገር ለሕዝቡ በጭራሽ አያስተላልፍም። እንደዚሁ ሁሉ፤ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተላልፈው ከሰማያዊው ዙፋን የሚመጣውን ብቻ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "እርሱ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል"።

ይህ የኢየሱስ ቃል አገራችን ባሃማስ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ውስጥ በነበረች ጊዜ ያየነውን ነገር ያስታውሰኛል። በየዓመቱ ህዝቡ በናሳሁ በሚገኘው ክሊፎርድ ፓርክ በተሰኛ አደባባይ በመሰብሰብ፤ መንግሥታዊው

ገዢ እንግሊዝ ውስጥ ከሚገኙት ንግሥት የተላከውን፣ "ከዙፋን የመጣ ንግግር" የተባለ ሰነድ ያነቡልናል፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ ንግግሩን ለማዳመጡ እርግጠኛ ለመሆን ሲባል በመላው አገር በዓል ይሆናል፤ ሁሉም ነገር ይዘጋል፡፡

ንጉሣዊው ገዢ በግዛቲቱ የአስተዳደር ባለሥልጣናት ተከበው በወንበሩ ላይ ይቀመጡና የእንግሊዝ ንግሥት ለቅኝ ግዛቲቱ የላኩትን ያነባሉ፡፡ ያ ንግግር ለአዲሱ ዓመት እቅድና ተግባራዊ ግዳጅ ይሆናል፡፡ ሉዓላዊው አገዛዝ ለመንግሥቱና ለቅኝ ግዛቲቱ ያለውን ፍላጐት እንድናስታውስ እንድንደረግና እንዲሁም ንግሥቲቱ ከቅኝ ግዛቲቱ የሚጠብቁት ነገር ምን እንደሆነ እንድናውቅ በአንድነት እንሰበሰብ ነበር፡፡ የንግግሩ ይዘት የመንግሥታቸው ህግ፣ ባህልና የሕይወት መለኪያ ቅኝት እና ለቅኝ ግዛቲቱም ያላቸውን የወደፊት እቅዶች የሚገልጹበት ነበር፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፤ እርሱን ለማድመጥ ከሚያጩናንቅ የሕይወት ተግባር ራሳችንን አሳርፈን በፊቱ ስንቀርብ መንፈስ ቅዱስ ያስማቋረጥ ከሰማያዊው ዙፋን ንግግር ያቀርብልናል፡፡ የገዢው ቃል ከንጉሡ ቃል ጋር በጭራሽ የሚጣረስ አይደለም፤ ወይም ደግሞ እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ መልዕክቶችን አያመጣም፡፡ ንጉሡ አስቀድሞ የተናገረውን ነገር እና የሚፈልገውን ያስታውሰናል፤ በተጨማሪም የመንግሥቱን የወደፊት ሁኔታ በመተንበይ ይናገራል፡፡

## ቀዳሽ

ጳውሎስ በተሰሎንቄ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> "እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጧችኋልና፡፡"

እንደ ቀዳሽነቱ፤ ገዢው ከንጉሡ ባህርይ ተፃራሪ ከሆኑት በሕይወታችን ካሉ ነገሮች ነፃ እንድንሆን ይረዳናል፣ ለመንግሥቱም ጠቀሜታ የሚውሉ ስጦታዎቻችን እንዳያድጉ እንቅፋት ከሚሆኑ ሁኔታዎች ነፃ ያደርገናል፡፡ ቀደም ሲል፤ መንጻት ወይም መቀደስ ማለት ሙሉ ለሙሉ መንጻትን እንዲሁም መለየትን የሚያመለክት እንደሆነ አይተናል፡፡ በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ለእድገታችንና ለመሻሻላችን እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ያስወግዳቸዋል፡፡ ልክ ስንዴውን ከገለባው እንደመለየት ማለት ነው፡፡ ገለባው ለእኛ መልካም አይደለም፡፡ እርግጥ ነው መለየቱ በሚከናወንበት ጊዜ "የማበራየቱ ሂደት" የሚያሳምም ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ ለጥቅማችን ነው፡፡ ንጉሡ ያለንን እምቅ ኃይል እንዳንጠቀምና ዓላማችንን ከግቡ እንዳናደርስ የሚያደርግ ማንኛውንም ነገር አይፈልግም፡፡



እንዲሁም ገዢው፤ ለሰማያዊው መንግሥት አገልግሎት ይለየናል፣ ንጉሡ አዲስ በሚፈጠረው ምድርና አዲስ ሰማይ ከራሱ ህዝብ ጋር ለመኖር ለሚመሰስባትም ቀን ይቀድሰናል፡፡ የእንግሊዝ ንግሥት በሃማስን ሊጎበኙ በሚሄዱበት ጊዜ፣ ንጉሣዊው ገዢ ህዝቡ ሁሉ ለዚህ እንዲዘጋጅ መመሪያ ይሰጣሉ፡፡ መንገዶቹን መጥረግ፣ የአውራ ጎዳና መብራቶችን ማጽዳትና ዛፎችንና አበባዎችን መትከል የግድ ነበር፡፡ ንግሥቲቱ የማያዩት ቢሆንም እንኳን በመኖሪያ ግቢያችን ያሉትን ዛፎች እንከረክማለን፡፡ ለንጉሡ ዳግመኛ መምጣት፣ የሕይወታችንን የትኛውንም ዘርፍ የማዘጋጀት ተግባር የመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

በመሆኑም ገዢው እንደ ባህርው ሊቀርጸን የሚጠቀምባቸው ዋነኛ መንገዶች እነዚህ ናቸው፡፡ በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ ገዢው በውስጣችን ሊያሳድረው ስለሚፈልገው የመንግሥቱ ባህል ዘርዝር አድርገን እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ዐስራ አንድ

## የገዢው ባህል

*ባህልህ መገኛህን ያሳያል*

## የገዢው ንጉሣዊ ችሎታዎች

የመንግሥተ ሰማይ ባህል ከንጉሡ ባህርይ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ሁልጊዜም ልናስታው ሰው የሚገባ ነገር ነው። ስለ መንፈስ ቅዱስ ጠባይና ስለባህሉ በሚንነጋገርበት ጊዜ፤ ስለ ራሱ ስለ ንጉሡ ችሎታዎች እየተናገርን ነው ማለት ነው። የገዢው ሚና ንጉሡን መወከል እስከሆነ ድረስ፤ የገዢውን ጠባይና አሠራሩን ለማየት እንችላለን፤ ንጉሡም ምን እንደሚመስል ድምዳሜ ልንሰጥ ይቻለናል። እንደዚሁ ደግሞ፣ መንፈስ ቅዱስ የሰማያዊውን ንጉሥ ባህርይ የሚያንጸባርቅ እስከሆነ ድረስ፤ የእርሱ ጠባይ የንጉሡን የተለየ ባህርይ የሚያሳይ ነው።

ይህ ጽንሰ ሀሣብ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ የተለመደ ነው። በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ገብተን ምግብ ለመብላት ብንቀመጥና አስተናጋጁ ጋጠወጥና ቸልተኛ ቢሆን፤ ስለ ምግብ ቤቱ ባለን አጠቃላይ ግምት ላይ አሉታዊ ጥላ ያጠላበታል። ነገር ግን፣ ወደ አንድ ጫማ መሸጫ መደብር ሄደን ደግሞ በዚያ የምንፈልገውን ነገር እንድናገኝ የሚረዳንን ጥበበኛና ትዕግስተኛ የሆነ ሰው ብናገኝ፤ እርሱ ስለሚሠራለት ድርጅት መልካም የሆነ አመለካከት ይኖረናል። አንድን ግለሰብ፣ የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም በመወከል አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ሁኔታ፤ ስለተወከለው ሰው፣ የንግድ ድርጅት ወይም ተቋም ባለን ግንዛቤ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

### የንጉሡ ባህርይ የመንግሥቱን ሁኔታ ይወስናል

የአንድ አገር ባህል የአገሩ ብሔራዊ ጠባይ እንደሆነ ተደርጐ ሊጠቀለል ይችላል። የአገሩ ባሕል የእምነቱ፣ የዝንባሌው፣ ለነገሮች የሚሰጠው ዋጋ (እሴት)፣ የመርሆዎቹ፣ የሕይወት ልምምዶቹና የጠባዮቹ ድምር ውጤት ነው። በአንድ መንግሥት ውስጥ፤ የንጉሠ ነገሥቱ ዐይነትና ባህርያት እጅግ ወሳኝ ነገሮች ነበሩ፤ ምክንያቱም በሚገዛው ግዛት ላይ ተጽእኖ አሳድረዋል፤ አብዛኛውን ጊዜም ሁኔታዎችን



ይወስናሉ። በመንግሥቱ ውስጥ ሕይወት ምን እንደሚመስል ያሳያሉ። ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን እንዲህ ሲል ጽፏል፦

"በድሃ ህዝብ ላይ የሚገዛ ክፉ መኮንን እንደተራበ አንበሳና እንደተራበ ድብ ነው።"

"ጻድቃን በበዙ ጊዜ ህዝብ ደስ ይለዋል፣ ኀጥአን በሠለጠኑ ጊዜ ግን ህዝብ ያለቅሳል።"

በሌላ አገላለጽ፤ የመሪው የባህርይ አቅጣጫ በመላው የሀገሪቱ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ይህ በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእስራኤል መንግሥት ታሪክ ሲፈጸምና በመጨረሻም መንግሥቱን ይሁዳና እስራኤል ወደሚባሉ ሁለት መንግሥታት እንደከፈለው እናያለን። የተለያዩ ነገሥታት ባህርይ በህዝቡ ላይ መልካም ወይም ክፉ ተጽእኖ ያሳድራል። ለምሳሌ ያህል፤ በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ እንዲህ ተጽፎ እናነባለን፤ "የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ በእስራኤል ላይ ሁለት ዓመት ነገሠ። በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ፤ በአባቱም መንገድ እስራኤልንም ባሳተበት መንገድ ሄደ። " ስለዚህ ሰው የተጻፈው ታሪክ እንደሚናገረው ድርጊቱ፤ "የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን አስቆጣ" ይላል። ኢዮርብዓም የእስራኤልን ህዝብ ጌታን መከተሉን ትቶ ጣዖታትን እንዲያመልክ አደረገው፤ በተጨማሪም ከሌዊ ልጆች ብቻ ካህናት ይሁኑ የሚለውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመተላለፍ፤ ካህን መሆን የሚፈልገውን ሰው ሁሉ ካህን እንዲሆን አደረገ። የእርሱ ልጅ የሆነውም ናዳብ በግልጽ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ ሄደ።

በተጨማሪም በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ ስለ ሌላ ንጉሥ እንዲህ እናነባለን፤

". . . አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ይልቅ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ አደረገ። በናባጥም ልጅ በኢዮርብዓም ኃጢአት መሄድ ታናሽ ነገር መሰለው፤ የሲዶናውያንንም ንጉሥ የኤትበአልን ልጅ ኤልዛቤልን አገባ፤ ሄዶም በአልን አመለከ፣ ሰገደለትም። በሰማርያም በሠራው በበአል ቤት ውስጥ ለበአል መሠዊያ አቆመ። አክዓብም የማምለኪያ አጸድ ተከለ። አክዓብም ከእርሱ በፊት ከነበሩት ሁሉ ይልቅ የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣውን ነገር አበዛ።"

እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጣው የኢዮርብአም ተግባር ጥቂት ነገር እንደሆነ ስለቆጠረ፤ አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ይልቅ የከፋውን ኃጢአት አደረገ። ክፉ የሆነው አመራር በእስራኤል ነገሥታት ሀረግ በተከታታይ ይቀጥል ነበር፤ ህዝቡም በክፉ ስራቸው ይገፋበታል። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ እንደሚዘግበው፤ በውጤቱ ህዝቡ ያተረፉት መከራን ብቻ ነበር። "የታሰረውና የተለቀቀውም እንደጠፋ፤ እስራኤልንም

የሚረዳ እንዳልነበረ፤ እግዚአብሔርም እጅግ የመረረውን የእስራኤልን ጭንቀት አየ።”

በይሁዳ ግን፤ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ እንደተዘገበው ንጉሥ ሕዝቅያስን በምሣሌነት እናያለን፤

> “እርሱም አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን አደረገ . . . ሕዝቅያስ በእስራኤል አምላክ በእግዚአብሔር ታመነ። ከእርሱም በኋላ ከእርሱም በፊት ከነበሩት ከይሁዳ ነገሥታት ሁሉ እርሱን የሚመስል አልነበረም። ከእግዚአብሔርም ጋር ተጣበቀ፤ እርሱንም ከመከተል አልራቀም፤ እግዚአብሔርም ለሙሴ ያዘዘውን ትእዛዛቱን ጠበቀ። እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበር፤ የሚሄድበትም መንገድ ተከናወነለት።”

መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፤ እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ የይሁዳን ህዝብ በበቀል ከተሞሉ ጨካኝ ጠላቶቻቸው እጅ እንደታደጋቸውና በነበሩበት አስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ እንዴት መሆን እንደሚገባቸው ንጉሡ ሕዝቅያስ በተናገረ ጊዜ እንዴት እንደሰሙት ይዘግባል። ህዝቅያስን ባያምኑትና ለእግዚአብሔር የነበረውን ታማኝነት በምሳሌነት ባይቀበሉት ኖሮ በጠላቶቻቸው ወጥመድ ውስጥ ይወድቁ ነበር።

ለስኬታማ መንግሥት ቁልፉ የንጉሡ መልካም ባህርይ ነው። እንደዚሁ ሁሉ፤ የሰማያዊው ገዢ ባህርይ በምድር ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ሁኔታዎች ይወስናል። በተጨማሪም፤ የእርሱ ባህርይ በትክክል ከንጉሡ ባህርይ ጋር ተመሳሳይ ነው። በቅኝ ግዛት ውስጥ እርሱ የንጉሡን ባህርይ አኳኋን ይወክላል።

ንጉሡ የመንግሥቱን ባህርይ እንድንገነዘብ ይፈልጋል፤ በመሆኑም ልንተማመንበትና በእርሱም ውስጥ መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን። ስለዚህ ነበር ኢየሱስ እርሱ ምን እንደሚመስል ለተከታዮቹ ያለማቋረጥ መግለጫዎችን የሚሰጣቸው፤

> “እኔ መልካም እረኛ ነኝ፤ መልካም እረኛ ስለበጎቹ ነፍሱን ያኖራል።”

> “እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ አይራብም፤ በእኔ የሚያምን ሁሉ ዳግመኛ አይጠማም።”

> “እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ ከልቤም ትሁት ነኝ፤ ለነፍሣችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ። ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።”



ኢየሱስ ስለባህርይው ሊያብራራላቸው ይፈልግ ነበር፤ ምክንያቱም በእርሱ ዘመን የኖሩ ሌሎች ነገሥታት የሚተገብሩት ተቃራኒ የሆነውን ባህርይ ነበር። ለምሳሌ ያህል፤ አንድ ጊዜ ደቀመዛሙርት ከእነርሱ መካከል ማን ታላቅ እንደሆነና የበለጠውን ክብር እንደሚቀበል እርስ በእርሳቸው ይጨቃጨቁ ነበር። ኢየሱስ ይህንን ክርክር የሰማያዊውን መንግሥት ባህርይ ለማብራራት እንደ ምክንያት ተጠቀመበት። በማቴዎስ መጽሐፍ የተዘገበው ቃሉ ይህን ይመስላል፤

> “የአህዛብ አለቆች እንዲገዟቸው፤ ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም። ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፤ ከእናንተ ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።”

> ለስኬታማ መንግስት ቁልፉ የንጉሡ መልካም ባህርይ ነው

በዚህና በሌሎች ብዙ መንገዶች፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እነርሱ ይኖሩበት ከነበረው ከጨለማው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ የተለየ እንደሆነ ያለማቋረጥ ለማስተማር ሞክሯል። ያለማቋረጥም የንጉሡን ጠባይና ባህርይ በመግለጽ መልካም ስለሆነው መሪ እውቀት እንዲኖራቸው ይፈልግ ነበር።

ጠቅላላ የንጉሡን ባህርይ የማወቅ ሀሳብ አሳሳቢ ነገር መሆኑን፤ “የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች” ከሚለው የኢየሱስ ቃል እንረዳለን። የዚህ የተለየ መንግሥት ዜጎች እንድንሆን ይጋብዘናል፤ ስለ መንግሥቱም ባህርይ ምንነት ሊያረጋግጥልን ይፈልጋል።

## የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ የመንግሥትን ባህል ማሳደግ ነው

ጳውሎስ የሰማያዊውን መንግሥት ባሕርይ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ዜጎች ሕይወት ለማሳደር ፈልጐ ነበር፣ እነርሱም ከንጉሡ ጋር መሰለፍ (መስማማት) ማለት ለነርሱ ምን ማለት እንደሆነ ይማሩ የነበሩ ነበሩ። በገላትያ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች በጻፈው ደብዳቤ የንጉሡን ባህርይ የሚያሳዩ አስፈላጊ ጠባያትን ዝርዝር አቅርቧል፤

- ፍቅር
- ደስታ
- ሰላም
- ትዕግስት
- ቸርነት
- በጎነት
- እምነት
- የውሃት
- ራስን መግዛት

በምድር ላይ የትኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫ እነዚህ ባህርያት ይኖሩታል። ጳውሎስ እነዚህን ጠባያት፤ "የመንፈስ ፍሬ" ሲል ይጠራቸዋል። ገዢው ባለበት ስፍራ ሁሉ እነዚህ ባህርያት እየተገለጡ የመንግሥቱ ባህል በዚያ እንዳለ ማስረጃዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ጳውሎስ እነዚህን ጠባያት በፍሬ የመሰለበት ምክንያት ፍሬ በአንድ ሌሊት ስለማይታይ ነው፤ ከጊዜ ጋር እያደገ ይሄዳል። እናም በገዢው ምሣሌነትና አመራር የንጉሡን ባህል በሕይወታቸው እየተንከባከቡ ማሳደግ እንደሚገባቸው ያውቁ ዘንድ ይፈልግ ነበር። በመጀመሪያ፤ ገዢው በሰማይ የሚገኘውን እውነተኛ ባህርይ ያስተምረናል። በመቀጠልም እርሱ በእኛ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ ምክንያት ይህ የመነሻ ባህርይ በእኛ ዘንድ እንዳለና በሕይወታችን ልንገልጸው እንደሚገባን ያሳየናል።

መንፈስ ቅዱስን በምትቀበሉበት ጊዜ፤ የመንግሥቱን ባሕርይ ዘር ደግሞ ትቀበላላችሁ። በሕይወታችሁ ውስጥ ዘሩ እንዲያድግ የሚያደርጉትን የመንግሥቱን ባሕርያት በመጨመር ይህንን ዘር ታሳድጉታላችሁ። ለምሳሌም፤ አንድ የፖም ዛፍ ፍሬ ያፈራ ዘንድ ዛፉ "መስራት" አያስፈልገውም። የዛፉ ፍሬ ዘር በራሱ ውስጥ አለ፤ እናም ቀስ እያለ በእድገት ሂደት ውስጥ፤ አስፈላጊ የሆኑ ግብዐቶችን ማለትም በመሬት ውስጥ ያሉ ንጥረ ነገሮችንና የጸሀይ ብርሃንን በመጠቀም በቅርንጫፎቹ አማካይነት ፍሬው መገለጥ ይጀምራል። ፍሬው በሕይወታችን ውስጥ እንዲያድግ የሚያስችሉት መንፈሳዊ ንጥረ ነገሮች፤



ከንጉሡ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነትን መቀጠል፤ የመንግሥቱን ህገ መንግሥት ማጥናት - ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ እንዲሁም በውስጣችን ለሚኖረው ገዢ ምሪት ራሳችንን መስጠት ናቸው።

ልክ የፖም ፍሬዎች ከፖም ዛፍ መገኘታቸው ተፈጥሯዊ እንደሆነ ሁሉ፤ የመንፈስ ፍሬ በአንድ የመንግሥቱ ዜጋ ሕይወት ውስጥ ማደጉ የተለመደ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ የሚያንጸባርቀው የንጉሡን ባህርይ ነው። ለምሳሌ ያህል ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ በጎነት ነው። በመሆኑም በመንግሥቱ ውስጥ የምንኖር ከሆነ በጎዎች መሆናችን የተለመደ ነገር ነው። በጎዎች ካልሆንን ግን ልንሆን የተገባንን ዐይነት ሰዎች አይደለንም። ገዢው ዋና (የመነሻ) ከሆነው ባህርያችን ጋር ያገናኘ ናል፤ ይህም እንደ ሰው ልጅነታችን ለእኛ የተገባ እውነተኛ ሕይወት ነው።

> የንጉሥ - ስባት ባህል በፍቅር፣ በደስታና በሰላም ይታወቃል

የመንፈሱ ጠባይ ወይም ፍሬ የሚያሳየው የንጉሡን ባህል ነው፤ በመሆኑም በመጀመሪያ ደረጃ የፍቅር ባህል፣ የደስታ ባህል እንዲሁም የሰላም ባህል መሆኑን እናያለን። ከላይ በተጠቀሰው ዝርዝር በተመለከቱት ጠባያት የተሞላ ባህል ምን እንደሚመስል ገምቱ! ለተሰጡን ሃላፊነቶች ታማኝ መሆን የእኛ ባህል ነው። የዋሃት ባህላችን ነው። ከሌሎች ሰዎች ጋር ግብስብስ ወይም ባለጌ ልንሆን አይገባም። ኢየሱስ "ትሁታን ብጹዓን ናቸው፤ ምድርን ይወርሳሉ" እንዳለው ራስን መግዛት የእኛ ባህል ነው። ፍላጎቶቻችንን ወይም ቁጣችን በጭራሽ ከቁጥጥር ውጭ ሊሆኑ አይገባም። በሕይወታችን ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢፈጠር እነዚህን ጠባያት ይዘን በመጽናት መኖርና ማሳየት አለብን።

በእኛ ውስጥ የሚኖረው ንጉሣዊው ገዢ በሚኖርበት ጊዜ፤ የንጉሡን ባህርይ እንድናጸባርቅ በማስቻል ሕይወታችንን ያድሰዋል። ለሕይወት አዲስ እይታና የመንግሥቱን አዲስ ሥርዓተ ትምህርት በመስጠት ግላዊ የሆነውን ባህላችንን ይቀይረዋል። የንጉሡ የአመለካከት ቅኝት እንዲኖረንም ያደርጋል። እንዴት እንደምናስብ፣ እንዴት እንደምንናገር እንዴትስ እንደምንመላለስ እንደገና ያስለጥነናል።

### ባህል መገኛውን ይገልጻል

ባህልህ መገኛህን መግለፁ የግድ ነው። ምግባርህ፣ ለሌሎች የምትሰጠው ምላሽ፣ ችግሮችን የምትጋፈጥበት መንገድና ግራ መጋባቶች በተከሰቱ ጊዜ የምትሰጠው ምላሽ ሁሉ የሰማያዊውን መንግሥት ባህል የሚያሳዩ መሆን ይገባቸዋል። በአንተ ውስጥ ያለው የመንፈሱ ጠባይ

የባህርይህን ልዩ መሆን ይገልጻል:: ይህ የተለየ ባህርይህ ሰማያዊ ከሆነው ቅርስህ ጋር ያገናኝሃል::

ቀደም ሲል፤ የሰዎች ልዩ ሁኔታና የተለየ ግለሰባዊ ጠባይ ከየት አገር እንደሆኑ ወዲያውኑ እንድናውቃቸው እንደሚያስችለን አውርተናል:: አንድን ሰው ትመለከትና፤ "ይህ ሰው አውስትራሊያዊ ነው" ትላለህ:: ይህ ለማንኛውም አገር ዜጋ የሚሠራ ነው:: አውስትራሊያዊ የሆነ ሰው ብቻ የሚናገረው ወይም የሚያደርገው አንድ የተለየ ነገር አለው:: በምድር ላይ ሆነው ሰማይን የሚወክሉ ሰዎችን በተመለከተም እንደዚሁ ያለ ልምምድ ሊኖራቸው የግድ ነው:: ሰዎች ባህርያችንን ተመልክተው፤ "አንተ ከሰማያዊው አስተዳደር የመጣህ ነህ" ለማለት መቻል ይገባቸዋል:: ኢየሱስ "በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" ሲል ተናግሯል:: በመንግሥቱ ውስጥ መሆን ማለት ወደ ንጉሡ ባህርይ ስር ነቀል በሆነ ሰውጥ መሸጋገር ማለት ነው:: ገዢው በአንተ ውስጥ የሚኖር ከሆነ፤ በንጉሡ ላይ እያመጽክ በመኖር ደስተኛ አትሆንም:: እንዲህ ብታደርግ ምቾት የማይሰጥና ያልተለመደ ነገር ይሰማሃል::

## የባህል ግጭት

ከመንግሥተ ሰማይ ጋር ስትስማማ፤ በመሠረቱ አሁን በሁለት ዓለማት ወይም መንግሥታት ውስጥ እየኖርክ ነው:: የማይታየው የእግዚአብሔር መንግሥት በገዢው መገኘት በኩል በአንተ ውስጥ ይኖራል:: ሰብዓዊ መንግሥት፣ ኃይልን ከሉሲፈር የሚያገኘው የጨለማው መንግሥት፣ ደግሞ በዙሪያህ አለ:: በተጨማሪም፤ መነቀል የሚገባቸው የዐመጸኛው ባህርይ ቅሬታዎች አሁንም በሕይወትህ ውስጥ አሉ::

በመሆኑም ለየትኛው መንግሥትና ባህል እጅ እንደምንሰጥ በሁለት ምርጫዎች ላይ እንወድቃለን:: ጳውሎስ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የኖሩትን በፊልጵስዮስ የሚገኙ የመንግሥቱን ዜጎች፤ ትኩረታችሁን በመንግሥተ ሰማይ ላይ አድርጉ ምክንያቱም፤ "ሀገራችን ግሰማይ ነው" እያለ ያጽናናቸዋል:: የመንፈስን ፍሬ ከዘረዘረላቸው በኋላም ለገላትያኑ፤ "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ስጋን ከክፉ መሻቱ ጋር ሰቀሉ:: በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ" ሲል ያሳስባቸዋል:: ደቀመዝሙር የሆነው ዮሐንስም የኢየሱስን ተከታዮች እንዲህ ሲል ያበረታታል፤ "በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይልቅ የበለጠ ነው::" በሌላ አባባል፤ "በእናንተ ውስጥ የሚኖረው ገዢ ኃይል በእናንተ ዙሪያ ካለው የዓለም ኃይል ይልቅ የበለጠ ነው" እያላቸው ነው::

አብዛኛውን ጊዜ የእነዚህ ባህሎች ግጭት፤ በተለይም በገዛ ቤተሰቦቻችን መካከል ሲከሰቱ እናያለን:: እስኪ በሌላ ማለትም በመንግሥትና በቅኝ ግዛት ምሣሌ ይህንን ነገር ላብራራው:: በካሪቢያን



አገሮች የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ህዝቦች ጥቁሮች ናቸው:: አብዛኞቹ፤ ዘሮቻቸው በአፍሪካ ከሚገኙ ተመሳሳይ መንደሮች በባርነት ወደ ካሪቢያን አገሮች የመጡ በመሆናቸው ግንኙነት አላቸው:: ከአንድ ቤተሰብ የሆኑ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ተለያይተዋል:: ለተለያዩ ቅኝ ገዢ መንግሥታት ተሸጠዋል:: በዚህ ምክንያት፤ ከአንድ ቤተሰብ የሆኑ ነገር ግን የተሸጡባቸውን የተለያዩ መንግሥታት ቋንቋና ባህል ወርሰው የሚኖሩ ሰዎች ታገኛላችሁ:: በመሆኑም ዛሬ፤ ከአንድ ቤተሰብ የነበሩ ዘሮች እርስ በእርሳቸው ለመግባባት አይችሉም:: አንዳቸው የሌላኛውን ቋንቋ አያውቁም::

ምንም እንኳን ይህ የቅኝ አገዛዝ አሳዛኝ ውጤት ቢሆንም፤ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ስትገባና ሙሉ ለሙሉ የተለየ ባህል ስትወስድ፤ አንተም ተመሳሳይ ገጠመኝ ይኖራሃል:: ምክንያቱም የተለወጠ ሕይወትህ የተጨበጠ መረጃ በአንተ ስለሚታይ፣ የገዛ ራስህ ቤተሰብ አባላት፤ አብሮ አደጎችህ የሆኑ ሰዎች፣ አንተን ወይም እያደረክ ያለውን ነገር ለምን እንደምታደርግ አይረዱህም:: ቋንቋህ እንደተለወጠ ይታዘባሉ፤ ዝንባሌህና ጓደኝነትህ ሁሉ እንደተቀየረ ይረዳሉ:: ከሰማያዊው መንግሥት ጋር የተቃረኑ ነገሮች ማድረግ ማቆምህን ያያሉ:: በመንግሥቱ ውስጥ ለመኖርህ ማረጋገጫው በተለየ የሕይወት ዘይቤ ባህል ውስጥ መኖርህ ነው::

## በመንፈስ መመላለስ

አንዳንድ ጊዜ፤ አንድ እግራችንን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አንድ እግራችንን ደግሞ ዓለማዊ በሆነው መንግሥት ውስጥ ለማድረግ እንሞክራለን:: ለንጉሡ ባህል እንግዳ የሆነ ባህርይ እያሳየን እንደገና ደግሞ ገዢው በተለየ ሁኔታ እንዲመለከተን እንፈልጋለን:: ይሁን እንጂ ጳውሎስ ለገላትያውያን እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> "በመንፈስ ተመላለሱ፤ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ:: ስጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በእርሳቸው ይቃዋወማሉ፤ ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም:: በመንፈስ ብትመሩ ግን ከህግ በታች አይደላችሁም::"

ጳውሎስ አመጸኛ ባሕርይ የተላበሰ ባህል ምን እንደሚመስል ለማሳየት እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤

> "የሥጋ ስራም የተገለጠ ነው፤ እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ ዐመፀኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህንንም የሚመስል

ነው:: አስቀድሜ እንዳልኩ እነዚህን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም”

በዚህ ስፍራ “ መውረስ” የሚለው ቃል በመንግሥቱ ውስጥ መኖርን ወይም መመላለስን ነው:: የመንግሥተ ሰማይ ባህልና ዓለማዊ የሆነው ባህል ተቃራኒዎች ናቸው:: ባዕድ በሆነ ባህል ውስጥ እየኖርክ በመንግሥተ ሰማይ መመላለስ አትችልም::

የገዢው ሚና የመንግሥቱን ዜጎች ንጉሡ በተመላለሰበት የሕይወት ዐይነት ለመለወጥ እስከሆነ ድረስ እኛ በጨለማው ባህል ዐይነት መመላለስ በምንጀምርበት ጊዜ ይገስፀናል፣ ያርመናል:: ይህንንም የሚያደርገው በሁለት መንገዶች ነው፤ በመጀመሪያ አዕምሯችን ማስጠንቀቂያ በሚያሰማበት ውስጣዊ ሥርዓት ይጠቀማል:: በሁለተኛ ደረጃ የንጉሡን ትምህርት እንድናስታውስ ያደርገናል:: በመንግሥቱ ህገ መንግሥት ውስጥ የተዘገበውን ወደ አዕምሯችን ያመጣል ወይም የንጉሡን የተጻፈ ቃልና መንገዶች - ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ነው - እንድናስብ ያደርገናል:: ጳውሎስ፤ “ከህግ በታች” የማንኖር ሰዎች መሆናችንን ጽፎልናል:: በሌላ አገላለጽ፤ “አድርግ” እና “አታድርግ” የሚሉትን ህጎች አጥብቀን ለመከተል የምናደርገው ሙከራ አይሠራም ማለት ነው:: የተለወጠ ባህርይ ብቻ ነው ንጉሡ የኖረውን አይነት ሕይወት እንድንኖር የሚያስችለን:: ገዢውም ይህንን አዲስ ባህርይ ይሰጠናል፣ እንድንከተለውም ያስችለናል::

> ንጉሡ የኖረውን ዐይነት ሕይወት እንድንኖር የሚያስችለን የተለወጠ ባህርይ ብቻ ነው

“ንግግር ከዙፋን” የተባለውን በንጉሣዊ ገዢው በኩል የእንግሊዝ ንግሥት በባሃማስ ለሚኖሩ ዜጎች ያላቸው ፈቃድ ነው ተብሎ የሚነበበውን እናስታውስ:: ከሰማያዊው ዙፋን የሆነውን ንግግር ቅዱሳት መጻሕፍት አስፍረው የዘዋል:: ከመጻሕፍቱ ጋር በቅርብ ስንተዋወቅ፤ ገዢው የንጉሡ ፈቃድ ምን እንደሆነ ያስተምረናል፤ ያሳስበናልም:: “አንተ ይህንን ለማድረግ አቅደሃል፤ ይሁን እንጂ ንጉሡ ለአንተ መልካም ነው ያለው ይህ አይደለም:: ይህ እኮ ከሰማያዊው ዙፋን በሆነው ንግግር ውስጥ የተጻፈ ነገር አይደለም” እያለ ይነግረናል:: መንፈስ ቅዱስ የሚናገረው ከዙፋኑ በሆነው ንግግር መሠረት ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ያ የንጉሡ ሀሳብ ነው:: እንደገናም፤ የእኛ ተግባር የሚሆነው፤ “የእኔ ፈቃድ አይሁን፤ የአንተ ፈቃድ ግን ይፈጸም” ብሎ ምላሽ መስጠት ነው:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ “ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም:: እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ ነው:: ሕይወትም ነው::”



በአዲሱ ዋና መምህር በኢየሱስ ክርስቶስ ሥር እንደሆንህ ማስታወስ ይገባሃል:: በአዲስ የሕይወት ፍልስፍና ሥር ነህ:: የአዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተማሪም ነህ:: የአዲስ አመለካከት ዘይቤ ባለ አደራ ነህ:: ሌሎችን ትምህርት ቤቶች ሁሉ ጥለህ፤ ለመንግሥቱ ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ ራስህን ሰጥተሃል:: እናም ገዢው የንጉሡን ትምህርት ከሕይወትህ ጋር ሊያዋህድና እንድትገልጸውም ሊያስችልህ የአንተ የግል መምህር ነው:: እርሱ በንጉሥ ልጆች ውስጥ የመንግሥቱን ባህርይ ለማሳደር እንደሚታጋ ንጉሣዊ አስጠኚ ነው:: የመንግሥተ ሰማይ ወራሽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ልንለማመድ ያስፈልገናል::

ገዢው፤ ልክ ንጉሡ - ልጅ እንዳደረገው ፈጣሪን እንደገና እንደ አባታችን እንድንቆጥረውና “አባ አባት” ብለን እንድንጠራው በማስቻል ማስተማሩን ይጀምራል:: ይህ ዝምድና እንደገና በፈጣሪያችን መልክ እንደገና እንድንሠራ ያስችለናል:: የእርሱን ባህርይ ማንጸባረቅ የሚያስችለንን ብቃት ያጣነው በዐመጽ ምክንያት ነው:: ከጨለማው መንግሥት ጋር ቀድሞ በነበረን ግንኙነት ሳቢያ ያ ባህርይ በውስጣችን ተዘባርቋል:: ገዢው፤ እኛ አስቀድሞ የተፈጠርነው ለምን እንደሆነ የማስተማር ከባድ ሥራ አለበት::

> የመንፈስ ፍሬ ንጉሡ የተገበራቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ እነርሱ እርሱ ራሱ ናቸው::

እየተመለከትናቸው ያሉ ችሎታዎች ወይም የመንፈስ ፍሬ በንጉሡ የተተገበሩ ብቻ ሣይሆኑ እነርሱ እርሱ ራሱ ናቸው:: ንጉሡ ነገሮችን የፈፀመው በፍቅር ብቻ አልነበረም እርሱ ራሱ ፍቅር ነው:: ያሳየው ሰላም ማለት ምን እንደሆነ ብቻ አልነበረም፤ እርሱ ራሱ ሰላም ነው:: የትኛውም የንጉሡ ባህርይ ይሁን፤ በእኛም ሕይወት ውስጥ እንዲሁ ሊገለጥ የተገባው ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በማቴዎስ መጽሐፍ ውስጥ እንደተዘገበው “የሰማዩ አባታችን ፍጹም እንደሆነ፤ እናንተ ደግሞ ፍጹማን ሁኑ” ሲል ይህን ማለቱ ነበር::

የንጉሥ አባታችንን ባህርይ ማንጸባረቅ እንደሚገባን ማወቃችን፤ ወደ የግል መንፈሳችን፣ ነፍሳችንና ስጋችን ባህል ምን መግባት እንዳለበት ጠንቅቀን እንድንጠብቅ ያደርገናል:: ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፤ “ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት፣ በእናንተ የሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በስጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ::” ጳውሎስ እየተናገረ ያለው፤ “ሰውነታችሁ የገዢው መኖሪያ ቤት እንደሆነ አታውቁምን? እርሱ ቅዱስ ነው፤ በእናንተም ውስጥ ይኖራል: በመሆኑም ማደሪያውን በንጽህና ልትጠብቁለትና እንደባህርይውም ልታዘጋጁለት

ያስፈልጋችኋል፤ ኢየሱስ ስለ መንፈሳችሁ፣ ነፍሣችሁና ስጋችሁ መቤዠት ዋጋ ከፍሏል፤ በመሆኑም ገዢው በእናንተ ውስጥ ይኖራል:: ስለዚህ የገዢው ቤት ጠባቂዎችና ባለአደራዎች እንደመሆናችሁ መጠን፤ ማደሪያውን በመንከባከብ ክብርን ልትሰጡ ይገባችኋል" እያለ ነው::

ኢየሱስ እንዲህ ሲል አስተማረ፤ "የሰውነት መብራት ዓይንህ ናት፤ ዓይንህ ጤነኛ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ጤነኛ ይሆናል:: ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ደግሞ ጨለማ ይሆናል::" የዓለም ባህል ወደ ሕይወታችን የሚገባው በዓይናችንና በጆሯችን በኩል ነው:: በቴሌቪዥን፣ ወይም በኢንተርኔት የምናያቸው ወይም በመጻሕፍት የምናነባቸው ማናቸውም ነገሮች፤ ውስጣዊ የሆነውን ግላዊ ባህላችንን ጥራት ያበላሻሉ:: እንደዚሁም ደግሞ ያለማቋረጥ የምናደምጣቸው ነገሮች ሕይወታችን ላይ ተጽእኖ ያሣርፋሉ:: አጥፊ የሆነ ባህል እንዲወረንና፤ ሕይወታችንንና ለሰማያዊው መንግሥት ያለንን ሥራ እንዲያበላሽ በፍጹም መፍቀድ የለብንም::

የመንግሥቱ ዜጋ መሆን ማለት በተወሰነ ደረጃ ውጥረት ባለበት ሁኔታ ውስጥ መሆንን ይጠይቃል፣ ምክንያቱም የምንኖረው የዐመጽና የሞት ባህል ባለበት መካከል ስለሆነ ነው:: አሮጌው ባህል፣ አዲሱ ባህል ከሚፈልገው ሁኔታ ጋር ይዋጋል:: እኛ በዚህ የምንኖረው፤ የብርሃንን መንግሥት ለማስፋፋትና የጨለማውን መንግሥት በማስወገድ ዓላማ ነው:: ኢየሱስ ከመሞቱ ጥቂት አስቀድሞ እንዲህ ሲል የጸለየው ለዚህ ነው፤ "ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም፤ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም . . . ወደ ዓለም እንደላክሽኝ እንዲሁ ወደ ዓለም ላክኋቸው::"

ምንም እንዲህ ባለ ውጥረት ውስጥ ያለን ብንሆን እንኳን፤ በመንግሥተ ሰማይ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋሃትና ራስን መግዛት ውስጥ እንኖራለን:: ጳውሎስ በኤፌሶን ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> "በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤ በእነርሱም በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፤ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው:: በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ የስጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን በስጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን:: ነገር ግን እግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን:: በፀጋ ድናችኋልና፤ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት፤ ከሁሉ የሚበልጠውን የፀጋውን ባለጠግነት ያሳይ ዘንድ፤ ከእርሱ ጋር አስነሣን፤ በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን . . . እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን::"



በምድር ላይ የምንኖር ቢሆንም፤ በሰማያዊው መንግሥቱ ውስጥ እንኖር ዘንድ ካመጣን ንጉሥ ጋር በሰማያዊ ሥፍራ ተቀምጠናል፤ በተጨማሪም በምድር ላይ የሰማያዊውን መንግሥት ባህል መኖር የሚያስችለን የዚህ መንግሥት ብቃት አለን:: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን አባታችሁን ያከብሩ ዘንድ፤ ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ::"

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች - የመንግሥቱ ባህል ኃይል ናቸው

መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ቀን በወረደ ጊዜ፤ የመንግሥቱ ዜጎች የመንግሥቱን ባህል በምድር ላይ ያስተዋውቁ ዘንድ የገዢውን ኃይል ከልዩ ልዩ መንግሥታዊ ችሎታዎች ጋር ተቀብለዋል:: እነዚህም ችሎታዎች "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች" ይባላሉ:: "ፍሬ" ከንጉሡ ባህርይ ጋር ይያያዛል:: በእኛ ውስጥ የንጉሡ ባህርይ ማደጉን ያመለክታል:: "ስጦታዎች" ከንጉሡ ኃይል ጋር የተያያዙ ናቸው:: አንደኛው ባህርይ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ችሎታ ነው፤ ይሁን እንጂ ሁለቱም ቢሆኑ ለመንግሥታዊው ሕይወት እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው:: ከችሎታዎቹ አንዳንዶቹ የጥበብ፣ የእውቀት፣ የእምነት፣ የፈውስ፣ ተዓምራትን የማድረግና የትንቢት ስጦታዎች ናቸው:: በምዕራፍ አሥራ ሦስት ውስጥ እነኝህን ስጦታዎች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን:: በዚህ ስፍራ ግን ባህርይ በጊዜ ሂደት ውስጥ የሚያድግ ሲሆን፤ ከገዢው የሆነ የኃይል ችሎታ ግን ወዲያውኑ አንድ ሰው መንገዱን ከንጉሡ ጋር ሲያደርግና የመንፈስ ቅዱስን መፍሰስ በሕይወቱ በተቀበለ ጊዜ ሊያገኘው የሚችል መሆኑን ልናስታውስ ይገባናል::

ከእነኚህ የኃይል ስጦታዎች ጋር ታላቅ ኃላፊነትም አብሮ ይመጣል:: ባህርይ ከኃይል ይልቅ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ነገር ነው፤ ምክንያቱም የኃይል አጠቃቀማችንን ይቆጣጠርልናል:: ለተሣሣተ ፍላጎትና ዓላማ እንዳንጠቀምበት ይጠብቀናል:: ኃይላችንን ሰዎችን ከመርዳት ይልቅ ሰዎችን ለመጉዳት እንዳናውለው ይከላከለናል:: ሁሉም ሰው ቢሆን ኃይል ይፈልጋል፤ በተሰጠን ጊዜ ግን ብዙውን ጊዜ የተሰጠንን ኃይል መቆጣጠር እንደሚያስፈልገን አናስብም:: ብዙ ሰዎች ኃይልን በብርቱ ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን

> የመንፈስን ፍሬ በሕይወታችን ከማፍራት ይልቅ የመንፈስን ስጦታ መቀበል ይቀላል

በዚያው መጠን ጐን ለጐን መሠረታዊ የሆኑ የመንግሥቱን ባህርያት በውስጣቸው የማሳደግ ወሳኝነቱን አይገነዘቡትም:: የመንፈስን ፍሬ በሕይወታችን ከማፍራት ይልቅ፤ የመንፈስን ስጦታ መቀበል ይቀላል:: የእግዚአብሔርን ባህርይ በሕይወታችን ከማሳደግ ይልቅ፤ የእግዚአብሔርን ኃይል ማግኘት ይቀላል:: በመሆኑም፤ እንደ ፍቅር፣ በጎነትና ራስን መግዛት የመሳሰሉትን ባህርያት ማሳደግ የግድ ነው፤ ምክንያቱም የስጦታ አጠቃቀማችን የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጉታል::

ባህርያቱም ሆኑ ስጦታዎቹ ሁለቱም ጠቃሚዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ ባህርያቱ ወሳኝ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፤ ምክንያቱም ኃይል ያለ ባህርይ እጅግ አደገኛ ነው:: እነዚህን ሁለት ነገሮች ማመጣጠን በሁሉም የመንግሥቱ ዜጎች ዘንድ ትልቅ ተግዳሮት ነው:: ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ እንዴት እንደሚኖሩ፣ እንዴት እንደሚያስቡና እንዴት እንደመንግሥቱ ዜጎች እንደሚተገብሩ በማስተማር ሦስት ዓመት ተኩል የፈጀው ለዚህ እንደሆነ አምናለሁ:: በመጀመሪያ አሰለጠናቸው፤ ቀጥሎም በበዓለ ሃምሣ ቀን በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ የሰማያዊውን መንግሥት ኃይል ተቀበሉ:: በተጨማሪም፤ ወደ መንግሥቱ ባህል የመለወጥ ተግባር ቀጣይና የሕይወት ዘመን ሂደት በመሆኑ፤ እርሱ ወደ አባቱ ከተመለሰ በኋላም ገዢው እነርሱን ማሠልጠኑን እንደሚቀጥል ነግሯቸዋል::

## የባህል ተጽእኖ

በመጨረሻውም፤ ባህል ተጽእኖ በማምጣት እንደሚስፋፋ ሁሉ፤ የመንፈስ ቅዱስ ባህርያትና ስጦታዎች በምድር ላይ የሰማያዊው መንግሥት ተጽእኖ ማሳደሪያዎች ናቸው:: ገዢው ሕይወታችንን ወደ ንጉሡ ባህርይ እንዲለውጥ እስከፈቀድንለትና ኃይሉንም መግለጥ ስንጀምር ሕይወታችን በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ተጽእኖ ያመጣል:: ሰማያዊው መንግሥት በምድር ላይ የሚስፋፋው በዚህ መንገድ ነው:: ጴጥሮስ፤ በበዓለ ሃምሣ ቀን የወረደው መንፈስ የንጉሡ የተስፋ ቃል ፍጻሜ መሆኑን በገለጸ ጊዜ፤ በዚያ ስፍራ ተሰብስበው በነበሩ ሰዎች ላይ ያመጣው ተጽእኖ ኃይለኛ ነበር፤

> "ቃሉንም (ስለመንግሥቱ) የተቀበሉ (የጴጥሮስን)፤ ተጠመቁ፤ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤ በሐዋርያትም ትምህርትና በህብረት እንጀራንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር:: ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ድንቅና ተአምራት ተደረገ:: ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤ ያላቸውንም ሁሉ በአንድነት አደረጉ:: መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉ ነበር:: በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቆረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር:: እግዚአብሔርንም



> እያመሰገኑ በህዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው:: ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር::"

ይህ አስደናቂ የሆነ የባህል ለውጥን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ ነው! አማኞቹ ያሳዩት ፍቅር፣ ያላቸውን በጋራ መካፈላቸው፣ ትምህርታቸውና የመንግሥቱን ኃይል የመግለጥ ተግባር እነዚህ ሁሉ የመንግሥቱ ባህል ማንፀባረቂያ ናቸው፤ ይህን አዲስ መንግሥታዊ የሕይወት ዘይቤ በዓይኖቻቸው በተመለከቱ ሰዎች ሁሉ ፊት ሞገስን አቀዳጃቸው፣ በመሆኑም የሰማያዊው መንግሥት ተጽእኖ በምድር ላይ በየዕለቱ እያደገ ይሄድ ነበር::

በንጉሣዊ ገዢ ሥር እንዳሉ ምክትል ገዢዎች የመንግሥቱ ባህል አምባሳደሮች ሆነን እናገለግላለን:: መንግሥታዊው ተጽእኖ ከአንድ ግላዊ መስጠት ጀምሮ ወደ ማኅበረሰብ፣ አገር አቀፍ ከዚያም ዓለም ዓቀፋዊ ወደሆነ ለውጥ ያድጋል:: ይሁን እንጂ የሚጀምረው ራሱን ከጨለማው መንግሥት ባህል ወደ የሕይወትና ብርሃን መንግሥት ከለወጠ አንድ ግለሰብ ነው:: አንተ አሁን የተሰለፍከው ከየትኛው መንግሥት ጋር ነው?

# ክፍል ሀራት

## የገዢው ሚና እና በጐ ጫና



# ምዕራፍ ሀስራ ሁለት

## የመንግሥቱን ባህል መግለጥ

*ውስጣዊ አስተዳደር ሲጠፋ ሁልጊዜም ውጫዊ ህግን ተፈላጊ ይሆናል*

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው፤ እያንዳንዱ አገር ራሱን ልዩ በሆነ ባህላዊና ማህበራዊ መገለጫዎቹ ይገልጣል:: በአንድ በተወሰነ አገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን በድርጊታቸው፤ በአኳኋናቸው፣ በአነጋገራቸውና፣ በአስተያየታቸው ከየት እንደሆኑ ልታውቃቸው ትችላለህ:: እናም "ያ ሰው ባሃማዊ ነው፣" "ያኛው ኢጣልያዊ ነው" ወይም "ያ ሩሲያዊ ነው" ትላለህ:: ረዘም ላለ ጊዜ ከተለያዩ አገራት ወይም ክፍሎች ከመጡ ሰዎች መካከል ከተቀመጥክ በኋላ፤ የሁኔታዎቻቸውን፣ የዝንባሌዎቻቸውንና የንግግሮቻቸውን ልዩነት ትገነዘበዋለህ::

ቀደም ያለው ምዕራፍ ያብራራልን ይህን ነበር፤ የሰማያዊው መንግሥት ዜጎች እንደመሆናችን መጠን፤ የአዲሱን አገራችንን የተለዩ ጠባያት መቀበል ልንጀምር ያስፈልገናል:: ምንም እንኳን አሁንም በጨለማው መንግሥት የተከበብን ብንሆንም፤ ከውጭ ወደ ውስጥ ሳይሆን ከውስጥ ወደ ውጭ ልንኖር ይገባናል:: እንዲህ ዐይነቱን ሕይወት ኖረን የማናውቅ በመሆኑ፤ በመንግሥቱ ውስጥ ስንኖር እንዲመራንና ኃይልን እንዲሰጠን በገዢው መደገፍ ይኖርብናል:: ይህም የአመለካከት ቅኝነትን፣ የሕይወት ዘይቤንና ልዩ ልዩ ልማዶችን የሚያካትት ነው፤ በመሆኑም በእኛ ውስጥ ያለው ነገር በባህርያችን፣ በአፋችን ቃልና በድርጊታችን ሊገለጽ ይችላል::

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ፤ ለሌሎች ልዩ ልዩ ገጽታዎች ሁሉ ዋነኛ የሆነውን የመንግሥቱን ባህል ገጽታ ለመዳሰስ እፈልጋለሁ:: እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ጉዳይ ብዙውን ጊዜ በምዕራፍ አሥራ ሦስት ውስጥ በጥልቀት ወደምንመለከተው ወደ መንፈስ ስጦታዎች የሚያመራና ከእርሱም ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው::

እስኪ ነገሩን ለመጀመር፤ ሰዋዊ ወደሆኑ አገሮች፣ ወይም መንግሥታት ሁሉ ባሕርያት እንመልከት::

## የሁሉም ህዝቦች ባሕርያት

መንግሥታት እንዲመሠረቱና ራሳቸውንም እንደ መንግሥት ጠብቀው እንዲያቆዩ፤ መንግሥታቱ የግድ ሊኖሯቸው የሚያስፈልጉ ባህርያት (ጠባያት) አሉ።

1. መሬት (ግዛት)፤
2. ባህል (ህዝቡ የተመሠረተበትና አመለካከቶቹ)፤
3. እሴቶች (የሀገሪቱ ህዝብ የሚኖርባቸው መለኪያዎች)፤
4. ቋንቋ (የተለመደ የተግባቦት መስመር)

ለምሣሌ ያህል፣ አሜሪካን እንደ አንድ አገር ያደረጋት የተለየ ጉሣ ስለኖራት ወይም የኑሮ ደረጃዋ አይደለም፤ መሬቱ፣ መሠረታዊ የሆኑ እምነቶች፤ በህገመንግሥቱና እጅግ ጠቃሚ በሆኑ ብሔራዊ ሰነዶች ውስጥ የሰፈሩ እውነቶች፣ ከእነዚህም መሠረታዊ እምነቶች የመነጩ እሴቶችና የጋራ ቋንቋ፣ እንግሊዝኛ፣ መኖር ነው።

## ለአንድ መንግሥት ቋንቋ የሚሰጠው ኃይል

አላይ ከጠቀስናቸው የአንድ አገር ባሕል የመግለጫ አራት ባህርያት መካከል፤ ቋንቋ ቀዳሚውና ትልቁ ነው። ለአንድ ህዝብ ቋንቋ ያን ያህል ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?

### ቋንቋ በብሔራዊ ማንነት ቁልፍ ነገር ነው

በመጀመሪያ ደረጃ፤ ቋንቋ ለአንድ ህዝብ ብሔራዊ ማንነቱ ቁልፍ ነገር ነው። የእንግሊዝ መንግሥት ባሣማስን በተቆጣጠረ ጊዜ፤ በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር ህዝቡ እንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር እንዲችል ማስተማር ነበር። ቋንቋ ኃያል ነገር ነው፤ ምክንያቱም ሰዎች ስለ ሕይወት ብቻ ሣይሆን ሕይወት ራሱ እንዴት እንደሚተገበር አመለካከቶችን እንዲጋሩ ያስችላቸዋል። ባህል የተቀመጠው በቋንቋ ውስጥ ነው ለማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም ባህልን የሚቀርጸው ቋንቋ በመሆኑ ነው። አንተና እኔ አንድ ዐይነት ቋንቋ የማንነጋገር ከሆነ፤ ፈጽሞውኑ አንድ ዐይነት ባህል ሊኖረን አይችልም፤ ምክንያቱም እንዳችን ከእንዳችን መግባባት ስለማንችል ነው። ስለዚህ ቋንቋ ለአንድ ማህበረሰብ ቁልፍ ነገር ነው። ሁሉም ሰዎች በአንድ ወጥ ልሣን እስካልተናገሩ ድረስ አንድ አገር በእርግጥ አገር ሊባል አይችልም።



## ቋንቋ ብሔራዊ አንድነትን ይፈጥራል

በሁለተኛ ደረጃ፤ ቋንቋ ብሔራዊ አንድነትን ይፈጥራል። አንድ ህዝብ የጋራ የሆነ ቋንቋ ከሌለው፤ የህዝቡ አንድነት መፈረካከስ ይጀምራል። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ በዚህ ጉዳይ ላይ አሜሪካ በአሁኑ ጊዜ ተግዳሮት እየገጠማት ነው። አንዳንድ ሰዎች ሀገሪቱ በይፋ ባለ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ አገር እንድትሆን ይፈልጋሉ፤ ምክንያቱም እጅግ በርካታ ስደተኞች የእስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑ አገሮች የመጡ በመሆናቸው ነው። ከእነኚህ ስደተኞች ብዙዎቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለማጥናት ፍላጎት የላቸውም፣ በዚህ ምክንያት የእስፓን ቋንቋ ምልክቶችና ስነ ጽሁፎች ታትመዋል።

ባለፉት ትውልዶች፤ ለምሳሌ ያህል ስደተኞች ከአየርላንድና ከኢጣልያ ወደ አሜሪካ በመጡ ጊዜ፣ ሌሎችንም ቋንቋዎች የሚናገሩ በርካታ ህዝቦች በዚያ ነበሩ። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ስደተኞች አብዛኞቹ እንግሊዝኛ መናገር በመፈለጋቸው ልጆቻቸውንም ጭምር የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲማሩና እንዲናገሩ አደረጉ፤ በመሆኑም ሁኔታው ካሁኑ የተለየ ነበር። የራሳቸው ቋንቋ ይፋዊ እውቅና እንዲሰጠው አልጠየቁም፤ ነገር ግን የእንግሊዝኛ ቋንቋን በመማር ከአሜሪካ ባህል ጋር ለመዋሃድ ፈቀዱ። በአሁኑ ጊዜ በይፋ ባለ ሁለት ቋንቋ አገር የመሆን ጥያቄ፤ በአሜሪካ ምክር ቤት ያሉትን አንዳንድ ሰዎች፤ እንግሊዝኛ የአገሪቱ ይፋዊ ቋንቋ ሆኖ በህግ እንዲታወጅ ጥያቄያቸውን እንዲያቀርቡ አነሳስቷቸዋል።

በታሪክ፤ አሜሪካውያን ቋንቋቸው እንግሊዝኛ እንዲሆን ተስማምተዋል፤ ፈረንሣውያን ቋንቋቸው ፈረንሳይኛ እንዲሆን ተስማምተዋል፤ እንዲሁም ደግሞ የስፓኝና በላቲን አሜሪካ አገሮች የሚኖሩ ህዝቦች ቋንቋቸው እስፓኝ እንዲሆን ተስማምተዋል። ወደ አንድ ሌላ አገር ስደተኛ ሆነህ የምትገባ ከሆነ፤ የዚያን አገር ቋንቋ መልመድህን እርግጠኛ የመሆን ኃላፊነት የአንተ እንደሆነ ይቆጠራል። ያለበለዚያ፤ አለመስማማት ይፈጠራል። ስለዚህም ማንኛውም አገር የጋራ የሆነ ቋንቋ ይይዛል፤ ምክንያቱም ይህ ለአንድነት ቁልፍ ነገር ነው።

### ቋንቋ ለስኬታማ ተግባቦት ቁልፍ የሆነ ነገር ነው

በሦስተኛ ደረጃ፤ ቋንቋ ስኬታማ ለሆነ ተግባቦት ቁልፍ የሆነ ነገር ነው። ብሔራዊ ባህል፣ እሴት፣ ታሪክ፣ ግብ፣ ፍላጎትና እቅድ መተላለፍ የሚችሉት፤ የአንድ አገር መሪዎችና ህዝቦቿ እነዚህን ነገሮች ስኬታማ በሆነ መልኩ ለእርስ በእርሳቸው ማስተላለፍና ለቀጣዩም ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ ሲችሉ ብቻ ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ ቋንቋ ያስፈልጋል፤ በተለይም ደግሞ ግንኙነቱ በትክክል መተላለፉን ለማረጋገጥ ይረዳል።

### ቋንቋ ስኬታማ ለሆነ ገለጻ ቁልፍ የሆነ ነገር ነው

በአራተኛ ደረጃ፤ ነገሮችን ስኬታማ በሆነ መልኩ ለመግለጽ፤ ቋንቋ ቁልፍ የሆነ ነገር ነው:: ያሰብከውን ነገር ለመናገር የቃላት እጥረት ያለብህ ከሆነ ሀሳብህን እንደሚገባ ግልጽ አድርገህ ማብራራት አትችልም:: እንዲህ ዐይነቱ እጥረት ሰዎች እንደ አንደኛ ደረጃ ዜጋ ሆነው በአገራቱ ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ ችግር ይፈጥርባቸዋል::

### ቋንቋ የጋራ የሆነ ቅርበን የሚያጎላ ነው

በአምስተኛ ደረጃ፤ ቋንቋ የጋራ የሆነ ቅርበን የሚያጎላ ነው:: የሚናገሩትን ሰዎች የትውልድ አገር ለይቶ ያሳያል:: ለምሳሌ ያህል፤ ከፓርቱጋል የሆነ አንድ ሰው ከብራዚል የሆነውን ሌላ ሰው ቢያገኝ፤ ቋንቋቸው ተመሳሳይ እንደሆነ ይገነዘባሉ፤ ምክንያቱም ምንም እንኳን ቋንቋውን በሚናገሩበት ጊዜ እንደ የክልላቸው ልዩነት ቢኖረውም፤ ሁለቱም የሚናገሩት የፖርቱጊዝ ቋንቋ በመሆኑ ነው::

### ቋንቋ ትውልዳዊ ዝውውር ቁልፍ ጉዳይ ነው

በስድስተኛ ደረጃ፤ ቋንቋ ትውልዳዊ ለሆነ ዝውውር ቁልፍ ጉዳይ ነው:: ቤተሰቦች ከአንድ አገር ተነስተው ሲሰደዱና ወላጆች የትውልድ አገራቸውን ቋንቋና ልማድ ጠብቀው ሲያቆዩ፣ ነገር ግን ልጆች ይህንን ለማድረግ ሳይፈልጉ ሲቀር፤ በመጨረሻው የልጅ ልጆች ከአያቶቻቸው ጋር መነጋገር የማይችሉበትና ከታሪካቸውም ጋር ተቆራርጠው የሚቀሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ ታገኛለህ:: ይህም ማለት፤ እሴቶቼን፣ እምነቶቼንና ቤተሰባዊ ልማዶቼን ለልጆቼ ማስተላለፍ የምፈልግ ከሆነ፤ ከእነርሱ ጋር የጋራ በሆነ ቋንቋ መግባባት መቻል አለብኝ:: ስለዚህ ቋንቋ ከትውልድ እስከ ትውልድ የቤተሰብን ቅርበ ጠብቆ ያቆያል::

### ከመንግሥቱ ጋር አንድነትንና ተግባቦትን ማጣት

እነዚህ የቋንቋን ኃይልና እሴት የሚመለከቱ ነጥቦች፤ በምድር ላይ ካለው የመንግሥቱ ባህል ጋር አንድምታ ያለው ጉዳይ ነው:: የሰው ልጆች በንጉሣቸው ላይ ባመጹና ገዢውንም ባጡ ጊዜ፤ በሰማያዊው መንግሥትና በምድር ላይ በሚኖሩ ሰዎች መካከል የነበረው ቀጥተኛ የተግባቦት መስመር ተቋረጠ:: ከዚህ የተነሣ፤ ከዚህ በኋላ መንግሥተ ሰማይና ምድር "የጋራ ቋንቋ" አልነበራቸውም ለማለት እንችላለን:: ከዚያ አመጽ በኋላ የሰው ልጆች የባለውን ራሳቸውን ከንጉሣቸው ለማግለል የራሳቸውን ቋንቋ ለመጠቀም ሞከሩ:: እስኪ ይህ እንዴት እንደተከሰተ እንመልከት::

የዘፍጥረት መጽሐፍ "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች:: ከምስራቅም ተነስተው በሄዱ ጊዜ በሰናኦር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ በዚያም ተቀመጡ" በማለት ይዘግብልናል:: በዘፍጥረት



ምዕራፍ ሦስት ውስጥ አዳምና ሄዋን ከኤደን ገነት ከተባረሩ በኋላ፤ በተለይ የምስራቁ የገነት ክፍል በጥበቃ ሥር በመዋሉ ተመልሰው ወደዚያ ሊገቡ እንዳልቻሉ እንማራለን:: ምናልባትም ገነትን የለቀቁት በምስራቅ አቅጣጫ ሊሆን ይችላል፤ የሰዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድም የሰው ዘር በዚያው በምስራቅ አቅጣጫ መስፋት ቀጥሏል::

በዘፍጥረት ምዕራፍ ዐሥራ አንድ ውስጥ፤ ሰዎች በምስራቅ አቅጣጫ አሁንም መሰራጨት መቀጠላቸውን እንመለከታለን፤ የጋራ ቋንቋም እንደነበራቸው እናያለን:: ህዝቡ ትልቅ ግንብ ያለበት ከተማ ለመስራት እንዴት እንደወሰኑ የሚነግረን ይሄው ምዕራፍ ነው ክስተቱ የሚያሳየን የቋንቋን ኃይል ነው:: ህዝቡ የፈለጉት እስከ ሰማይ ደረስ የሚጠጋ ግንብ ለመስራት ነበር፤ ይህንንም ሲያደርጉ፤ "ግንብንም እንሠራለን፤ ለራሳችንም የስም መጠሪያ እናደርጋለን" ብለው በማሰብ ነበር:: የእግዚአብሔር ምላሽ "ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንንም ለማድረግ ጀመሩ፤ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመስራት አይከለከሉም" የሚል ነበር:: እግዚአብሔር "አንድ ሕዝብ አንድ ቋንቋ" ያለውን አስተውል፤ ይህም ቋንቋ ለኃይል ቁልፍ እንደሆነ ያመለክታል::

> ንጉሡ ራዕዮቻችንን
> እርሱ ባስቀመጠው
> በልባችን እንድንገነባ
> ይፈልጋል::

ነገር ግን የሕዝቡ የግንባታ ፍላጐታቸው ከአገር ቤት መለያታቸውን አመልካች ነበር:: አንድ ነገር ለራስህ ዝናና ዓላማ የምትገነባ ከሆነ፣ አዕምሮህን፣ ችሎታህን፣ እና ንጉሡ የሰጠህን ነገር ተጠቅመህ እንኳ ብታደርግ፣ እናም የራስህ አድርገህ ብትቆጥረው፣ ይህ ጣዖትን እንደማምለክ ነው:: ከንጉሡ የበለጠብን ማንኛውም ነገራችን ጣዖት ነው:: በዘፍጥረት ምዕራፍ 11 የምናነባቸው ሰዎች ከፈጣሪ - ንጉሣቸው በላይ አስፈላጊ ነው ያሉትን ግንብ ሲገነቡ ነበር::

ንጉሡ ሰዎች ከተሞችን ወይም ግንቦችን መገንባታቸውን አይቃወምም:: በርግጥ እርሱ በልባችን ያኖራቸውን ሕልሞቻችንን እንድንገነባ ይፈልጋል:: ይልቅስ፣ እርሱ ለዝናቸው ያደረጉትን ስግብግብ ዓላማቸውንና እብሪታቸውን ይቃወማል:: ሁሉን ነገር ለራሳችን ሳይሆን ለንጉሡ ክብር ማድረግ አለብን:: ለርሱ ክብር ካልሆነ፣ ውሎ አድሮ ይጉዳናል::

እንደገና፣ ግንቡን የመገንባት ብቃታቸው ቁልፍ ነገር ቋንቋቸው አንድ መሆኑ ነው:: "እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፣ ይህንም ለማድረግ ጀመሩ፣ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም::" ለግንቡ መሠራት አቅም የሆነው የቋንቋ ኃይል ነው:: በዚህ ዘመን ብዙ አገሮች ፕሮጀክቶቻቸውን በጋራ እንዳይሠሩ ቋንቋ መሰናክል ሆኖ እንመለከታለን፣ ብዙ የተለያዩ ኩባንያዎችም በሌሎች

አገሮች ለመሥራት እየፈለጉ ቋንቋ የተግባቦት ችግር ምክንያት ሆኖባቸዋል::

በዚያን ጊዜ መላው ዓለም አንድ ቋንቋ የነበረው በመሆኑ፣ መላው ዓለም ታላቅ የሆነ እምቅ ኃይል ነበረው ለማለት እንችላለን:: ይሁን እንጂ ያንን የቋንቋ ኃይል የተጠቀሙበት አንድ ነገር ለራሳቸው ለመገንባት ነበር፤ ንጉሡም ይህንን የመሠለ ቃል ተናገራቸው፤ "ይህ ትክክል አይደለም:: እየተጠቀማችሁበት ያለው ነገር ሁሉ የእኔ ነው:: መሬቱ የእኔ ነው:: ውሃውም የእኔ ነው:: ጭዱ የእኔ ነው:: የምትጠቀሙበት ሚስማርና መዶሻ የተሠሩት እኔ ከፈጠርኩት ቁስ ነው::" እናም ምላሹ፣ "ኑ እንውረድ፤ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው" የሚል ነበር:: እግዚአብሔር "ግንቡን እናፈራርሰው" አልነበረም ያለው፤ ምክንያቱም ያ አስፈላጊ ነገር አልነበረም:: አንዳቸው ከአንዳቸው ጋር መነጋገር እስካልቻሉ ድረስ የግንቡ ሥራ መጠናቀቅ አይችልም::

የዘፍጥረቱ ዘገባ እንዲህ ሲል ይቀጥላል፤ "ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ፤ እግዚአብሔር በዚያ የምድርን ቋንቋ ሁሉ ደባልቋልና":: ይህ ክስተት "ባቢሎን" የሚል ቃል የምናገኝበት ነው:: "ባቢሎን" ማለት ትርምስምስ ማለት ነው:: አንድ ሰው "ተደናገረ" በምንልበት ጊዜ፤ የሚናገረውን ነገር መረዳት አይቻልም ማለታችን ነው:: ግንቡ ከመጀመሪያው ባቢሎን ግንብ ተብሎ አልተሰየመም ነበር:: ያ ስም የወጣለት፤ ንጉሡ የሕዝቡን በአንድ ቋንቋ የመግባባት ችሎታ ካጠፋ በኋላ ነበር::

የሰውን ዘር ቋንቋ መደበላለቅ፤ ንጉሡ - አባት አንድ ቀን በገዢው መመለስ በኩል፤ ከእርሱና ከእርስ በርሳችን ጋር የነበረንን ግንኙነትና አንድነት እስኪያድሰው ድረስ እኛን የሚጠብቅበት መንገድ ነው:: የሰውን ልጆች ከኤደን ገነት ማባረሩ፤ ከሕይወት ዛፍ እንዳይበሉና ለዘላለም በአመፅና ከእግዚአብሔር ተለይተው ለመቤዠት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ እንዳይኖሩ ለመጠበቅ አስችሏል:: በተመሳሳይ ሁኔታም፤ የሰዎችን ቋንቋ መደብላለቁ፤ ሰዎች ለራሳቸው ስግብግብ ዓላማ ብቻ በመሮጥና ግባቸውን በማሳደድ ራሳቸውን በራሳቸው ከማጥፋት እንዲቆጠቡ ረድቷል:: ይህም የተደረገው መጨረሻቸው ያማረ እንዲሆን ነው::

ኃይልን ለማግኘት ቁልፍ ጉዳይ አንድ ቋንቋ ከሆነ፤ ለድካምም ቁልፍ ጉዳይ የተደበላለቀ (ብዙ) ቋንቋ ነው:: የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እጅግም ስኬታማ ያልሆነበት ምክንያት ይህ እንደሆነ እምናለሁ:: የቋንቋ ልዩነቶችና እነርሱም የሚፈጥሯቸው ቅይጥ ባህሎች መግታት በማይቻልበት ሁኔታ አለመግባባቶችንና ልዩነቶችን እያነሳሱ ይገኛሉ:: በእግባቡ የተዋቀሩና የተደራጁ ተቋማት ቢኖሩም እንኳን ይህንን መሠረታዊ ሁኔታ ሊለውጡት ከቶውንም አልቻሉም::



በመሆኑም፤ የሰው ልጆች አመጸኝነት ከእግዚአብሔር እና ሰዎች እርስ በእርሳቸው ጋር የነበራቸውን ተግባቦትና አንድነት አበላሽቷል:: ይህም ንጉሡ ልጅ በገዢው በኩል አንድ ጊዜ እንደገና ግንኙነትን የሚፈጥሩበትን ሁኔታ እስካመቻቸ ድረስ ነበር:: ይህ ግንኙነትንና አንድነትን እንደገና የማደስ ሂደት በዋነኛነት ሰማያዊ በሆነው ቋንቋ በመነጋገር ይገለጻል፤ እርሱም በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠ ችሎታ ነው:: ገዢው የመንግሥቱን ባህል እንደገና ወደ ምድር ለማምጣት ለምን ቁልፍ እንደሆነ፤ አንድ ጊዜ ደግመን፤ ልንመለከት እንችላለን::

## ከሰማይ የተሰጡ ቋንቋዎች

መንፈሱን በውስጣችን ከተቀበልን በኋላ ገዢው ከሚሰጠን የመጀመሪያ ነገሮች አንዱ ከሰማይ በተሰጡ ቋንቋዎች የመናገርን ችሎታ ነው:: የሚሰጠን ቋንቋ ምናልባትም ምድራዊ ሆኖ፤ ነገር ግን ተናጋሪው የማያውቀው ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ የሚሰጠን ቋንቋ በምድር ላይ የማይታወቅ ሰማያዊ ቋንቋ ሊሆን ይችላል:: ከሰማይ በተሰጠ ቋንቋ አማካይነት ገዢው የሰው ልጆች እንደገና "የጋራ የሆነ ልሳን" እንዲካፈሉ ያስችላቸዋል:: በዚህም ከሰማያዊው ንጉሥ ጋር እንዲነጋገሩና የእርሱ መንግሥት ዜጎች እንደሆኑ ለማሳየት ያስችላቸዋል:: ኢየሱስ የተሃድሶ ተልዕኮውን ካጠናቀቀ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ":: ነገር ግን በተጨማሪ፤ "ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ <u>በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ</u> . . . እጆቻቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይፈወሳሉ" ብሏቸዋል:: በዚህም ኢየሱስ፤ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ግንኙነት ካለው ሕይወት የሚገለጠውን ተጨባጭ ማስረጃ ዝርዝር እያቀረበ ነበር::

የአብ የተስፋ ቃል ለመንግሥቱ ኃይል ብቻ አልነበረም፤ ይልቁንም የመንግሥቱን ቋንቋ የሚጨምር ነበር:: እንደ ኢየሱስ ገለጻ፤ ዜግነትን ስትቀበል፤ አዲስ ቋንቋንም ትቀበላለህ:: ገዢው ከሰማያዊው መንግሥት የሆነውን ቋንቋ ይሰጥሃል:: በበዓለ ሃምሣ ቀን መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ ምን እንደተፈጠረ እስኪ እንደገና መለስ ብለን እንይ፤

> "በዓለ ሃምሣ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፤ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፤ ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ንፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው:: እንደ እሣትም የተከፋፈሉ ልሣኖች ታዩዋቸው:: በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው:: በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሣኖች ይናገሩ ጀመር:: ከሰማይ በታች ካሉ ህዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምጽ በሆነ ጊዜ ህዝብ ሁሉ ተሰበሰበ፤ እያንዳንዱም በገዛ

ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ:: ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ:- እነሆ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? የጳርቴና፣ የሜድ፣ የኢላሜጤም ሰዎች በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰደቅያም፣ በጳንጦስም፣ በእስያም፣ በፍርጊያም፣ በጵንፍልያም፣ በግብጽም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፤ በሮሜም የምንቀመጥ አይሁድም ወደ ይሁዲነት የገባን የቀርጤስና የአረብ ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሣኖቻችን ሲናገሩ እንሰማለን!"

"ሁሉም መንፈስ ቅድስ ሞላባቸው፤ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች መናገር ጀመሩ::" ንጉሥ - አባትን ለማምለክና የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በመጠባበቅ ላይ የነበሩ እነዚያ አንድ መቶ ሃያ ሰዎች በድንገት በገዢው አማካይነት በሌላ ቋንቋዎች መናገር ቻሉ:: በዚህ በተለየ ክስተት ከእግዚአብሔር የተሰጡት እነዚህ ቋንቋዎች እነዚያ ከመላው ዓለም የተሰበሰቡ ሰዎች ሊረዷቸው የሚችሉ የሰው ቋንቋዎችን የሚያካትቱ ነበሩ:: ንጉሡ፤ ለመንግሥቱ ዜጎች በተሰጡ ልዩ የቋንቋ ስጦታዎች አማካይነት የተሃድሶ ፕሮግራሙን እያስተላለፈ ነበር:: ይህ የተስፋው ቃል የመፈጸሙ ምልክት ነበር:: በገዢው ወደ ምድር መመለስ በኩል በሰማይና በምድር መካከል የነበረው የግንኙነት መስመር እንደገና መከፈቱንም ያመላክታል:: በተጨማሪም እግዚአብሔር በዓለም በሚኖሩ ሰዎች መካከል የነበረውን አንድነት እንደገና ለማደስ ያለውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው::

> ገዢው በእኛ ውስጥ መኖር በጀመረ ጊዜ ህልውናውን ማየት ብቻ ሳይሆን ልናደምጥ ይጠበቅብናል

ጴጥሮስ በዚያ ተሰብስበው በአዲስ ቋንቋ የመናገራቸውን እውነት ለተመለከቱ ሰዎች እንዲህ ሲል ተናገረ፤ "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሳው፤ ስለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና፤ የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ፤ ይህንን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው::" ገዢው በእኛ ሕይወት መኖር በጀመረ ጊዜ፤ ህልውናውን ማየት ብቻ ሳይሆን ልናደምጥ ይጠበቅብናል:: ይህ ህልውናውም በንግግር በተገለጠ ማስረጃ ሲገለጥ ይጠበቅበታል::

የዚህን ክስተት ውበት ልብ እንበል:: በባቢሎን ግንብ ክስተት፤ እግዚአብሔር የሰዎችን ቋንቋ በብዙ ቋንቋዎች በመደበላለቁ ሊያደክማቸው ቻለ:: በዚህ ስፍራ ግን፤ በአዲሱ መንግሥታቸው ሕይወት



ሊያጠነክራቸውና የመንፈስን ተስፋ መልዕክት መስማት ለሚፈልጉ ሌሎች ሰዎች እንዲያስተላልፉ ለሕዝቡ የቋንቋዎችን ስጦታ ሰጠ:: በተጨማሪም ይህ የቋንቋዎች ስጦታ የመንግሥቱን ዜጎች፤ ለንጉሡ - አባት ቤተሰብ እንደሆነ አንድ ህዝብ፣ አንድ በማድረግ አገልግሏል::

ከሰባ በላይ ወደሆኑ አገሮች ተጉዣለሁ፤ የተጓዝኩት አብዛኛውን ጊዜ በኮንፍረንሶች ላይ ለመስበክ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ለጉብኝት ነበር:: ከተጓዝኩባቸው አገራት የአብዛኞቹን ቋንቋ አልረዳውም:: ይሁን እንጂ፤ በተሳተፍኩባቸው በአብዛኞቹ ኮንፍረንሶች፤ ሰማያዊ ስጦታ የሆነውን ቋንቋ በተቀበሉ ሰዎች መካከል ያለውን አንድነት የሚያስረግጥ አንድ የተለየ ነገር ይፈጠር ነበር::

ለምሣሌ ያህል፤ በቅርቡ በዩክሬን በአገልግሎት ላይ ነበርኩ፤ በዚያ ስፍራም ከሃያ ሽህ የሚበልጡ ሰዎች በጉባኤው ውስጥ ነበሩ:: የዩክሬንን ቋንቋ አላውቅም:: ይሁን እንጂ ማምለካችንን በጀመርን፤ ጊዜ ያ ስፍራ ሰማያዊ ስጦታ በሆነው ቋንቋ ተጥለቀለቀ:: በሃያ ሽህ የሚቆጠሩ የዩክሬን ቋንቋ ተናጋሪዎች በልሳን መናገራቸውን ስሰማ እኔም ተቀላቀልኳቸው፤ "አሁን ሁላችን አንድ ነን!" ስል አሰብኩ:: እናም ድንገት በቤቴ ውስጥ እንደሆንኩ ተሰማኝ:: ይህም እንደገና የአንድነት ኃይል ያለው በቋንቋ ውስጥ እንደሆነ እንዳስታውስ አደረገኝ::

ተመሳሳይ በሆነ ሁኔታ፤ ከጥቂት ዓመታት በፊት እኔና ባለቤቴ ወደ ጀርመን ሄደን ነበር:: ንግግር እንዳደርግ ይጠበቅብኝ ወደነበረው አንድ ፔንትኮስታል ቤ/ክ ሄድኩ:: እርግጥ ነው በዚያ ሁሉም ጀርመንኛ ይናገራሉ:: ከዚያም ማምለክና በልሳን መናገር ጀመሩ:: በድንገትም በቤቴ እንደሆንኩ ያክል እንደገና ተሰማኝ:: በልሳን ሲናገሩ ስሰማቸው፤ "እኛ ሁላችን አንድ ነን!" የሚል ስሜት ተሰማኝ:: የልዩነቶቻችን አጥሮች ሁሉ ፈራርሰው ነበር:: ሁላችንም የመንግሥቱ ዜጎች መሆናችንንና የጋራ ቅርስ ያለን መሆኑን ተገንዝበነው ነበር:: ይህንን ያደረገው ልሣን ነበር:: ከዚያ በኋላ የአምልኮው ጊዜ አበቃ፤ ህዝቡም እንደገና በጀርመንኛ ቋንቋ መነጋገር ጀመሩ:: ከዚያ በኋላ ከንግግራቸው አንዲትም ቃል አልተረዳሁም፤ እንደገና ደግሞ እንግድነት ተሰማኝ:: ብዙዎቻችን መረዳት ከምንችለው በላይ ከሰማይ የተሰጡን ቋንቋዎች እጅግ ኃያል ናቸው::

## በልሣን የመናገር ዓላማዎች

የገዢው ዓላማ በአገር ቤቱ(በሰማይ) የአኗኗር ዘይቤና ቋንቋ እኛን ማሰልጠን ነው:: ይህም ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ወሣኝ የሆነ የመንግሥቱ ባህርይ ነው:: እስቲ በልሣን መናገር ለእኛ አስፈላጊ የሚሆንባቸውን በርካታ መንገዶች ቀጥለን እንቃኝ::

## የመንግሥቱን የዜግነት መለያ ይሰጠናል

በልሳን መናገር ለመንግሥቱ የዜግነት መለያ መሠረታዊ ቁልፍ ነገር ነው። በተጨማሪም፤ ከንጉሡ ጋር እርቅ መፍጠራችንን ተከትሎ በሰማያዊው ቋንቋ ለመናገር የመቻልን ስጦታ መቀበላችን የሚያሳየው ገዢው፣ አስቀድሞ እንደነበረው፣ ከንጉሡ - አባታችን ጋር የጋራ የሆነ ሰማያዊ ቋንቋ እንድንካፈል ያስቻለን መሆኑን ነው።

## ከንጉሡ ጋር ቀጥተኛ ተግባቦት እንዲኖረን ያደርጋል

በተጨማሪም፤ ልሣናት የሰውን ዘር እንደገና አንድ ጊዜ ከንጉሥ - አባት ጋር በቀጥታ እንዲገናኙ ያስችላሉ። ለምሣሌም፤ አንዳንድ ጊዜ መሻታችንንና ፍላጎታችንን ምድራዊ በሆነ ቋንቋችን ለሰማያዊው አስተዳደር መግለጽ አስቸጋሪ ሆኖ የምናገኝበት ሁኔታ አለ። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ፤ ገዢው በመንፈሣዊ ተግባቦት ለእኛ እና በእኛም በኩል ለአብ ይናገራል ሲል ጳውሎስ ጽፏል፤

> "እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፤ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሣብ ምን እንደሆነ ያውቃል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለቅዱሳን ይማልዳልና።"

ገዢው ከሰማይ የሆኑ ቋንቋዎች ለእኛ ይሰጠናል፣ በመሆኑም ከምናደርጋቸው ከሌሎች ተግባቦቶች በተጨማሪ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ፍላጎቶቻችንንና ጥያቄዎቻችንን ለንጉሡ ለመግለጽ ያስችለናል።

## ከንጉሡ ጋር ግንኙነት እንዳለን ምልክት ነው

የኢየሱስ ተከታዮች በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወርዶ "በአዲስ ቋንቋ" በተናገሩ ጊዜ፤ እነዚህ ደቀመዛሙርት ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ግንኙነት እንዳላቸው በዓለ ሃምሣን ለማክበር በዚያ ተሰብስበው ለነበሩ በሺህዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ምልክት ነበር። በመሆኑም ጳውሎስ እንዳስተማረው፤ "እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፤ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።"

## በመንግሥቱ ውስጥ ዜጎች ለመሆናችን ማስረጃ ነው

ጴጥሮስ የመንግሥቱን ወንጌል በቂሣሪያ ከተማ ይኖሩ ለነበሩ አዳዲስ የመንግሥቱ ዜጎች በሚናገርበት ጊዜ፤ መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እናነባለን። እነዚህ ሰዎች የመንግሥቱ



ዜጎች እንደሆኑ ጴጥሮስና ሌሎች አማኞች ተገንዝበው ነበር፤ "በልሳኖችም እየተናገሩ እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ይሰሟቸው ነበርና።" በልሣን መናገራቸው በሰማያዊው መንግሥት ውስጥ ዜጎች ለመሆናቸው ጥርት ያለ ማስረጃ ነበር።

## ስለ ልሣናት የተለመዱ ጥያቄዎች

ስለ ልሣናት በተወያያችሁ ጊዜ ሁሉ ሰዎች ሳያነሷቸው የማይቀሩ የተወሰኑ ጥያቄዎች አሉ . . .

- ልሣናት እውነተኛ ነገሮች ናቸው?
- ልሣናት በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን ለነበሩና ለቀደሙ ተከታዮች ብቻ ነበሩን?
- እንደ መንግሥቱ ዜጎች ሆነን ለመኖር በልሣናት መናገር አስፈላጊ ነገር ነውን?

እስኪ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ እንስጥ።

### ልሣናት እውነተኛ የሆኑ ነገሮች ናቸውን?

ልሣናት በሰማይና በምድር መካከል የተፈፀሙ እውነተኛ ተግባቦቶች (ግንኙነቶች) ናቸው። ብዙ ሰዎች ልሣናት እውነተኛ የሆኑ ነገሮች ስለመሆናቸው ይገረማሉ፤ ምክንያቱም በልሣናት መናገር እንግዳ እንደሆነ ወይም እንደማይገባ ነገር ተደርጎ በመቆጠሩ ነው። የቀድሞዎቹ የኢየሱስ ተከታዮች፤ ኢየሱስ በልሣን ትናገራላችሁ እንዳላቸው በልሣናት ተናግረዋል። ባለፉት ሁለት ክፍለ ዘመናት የመንግሥቱ ዜጐች በልሣናት ከንጉሡ ጋር ተነጋግረዋል። በልሣን መናገር ለመንግሥቱ ዜጎች የተገባ ነገር መሆኑን ከተገነዘብን፤ እንግዳ እንደሆኑ ነገሮች መቆጠራቸው እያበቃና እውነተኛ የሆነ ዓላማቸው ግልጽ እየሆነ ይመጣል።

> ከሰማይ የተሰጡት ቋንቋዎች ኃያል ለዋዛጅ በመሆናቸው ምክንያት ሉሲፈር ለጥብቅ ይዋጋቸዋል

### ልሳናት በኢየሱስ ዘመን ለነበሩትና ለተከታዮቹ ብቻ የተሰጡ ነበሩን?

ልሣናት ለመንግሥቱ ዜጎች የተሰጡት የመንግሥቱን ዓላማ ሲፈጽሙ እንዲያግዟቸው ሲሆን፤ እኛም አሁን በምድር ላይ የምንኖረው ይህ እርዳታና እገዛ በሚያስፈልገን ዘመን ውስጥ ነው:: ልሣናት በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች አስፈላጊ እንደነበሩ ዛሬ ለምንኖረውም ዜጎች ጠቀሜታ አላቸው:: በዚህ ምድር ላይ የንጉሡን አባት ፈቃድ ለማከናወን በምናደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ከርሱ ጋር ግንኙነት እንድንፈጥር ያስችሉናል::

ይሁን እንጂ በልሣን መናገርን አስመልክቶ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩት አንዳንድ አለመግባባቶችና ግጭቶች የሚያስደንቁን አይደሉም:: የባቢሎንን ግንብ አስመልክቶ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ የተዘገበውን እንዲህ እናነባለን፤

> "እግዚአብሔር አለ፤ እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፤ ይህንንም ለማድረግ ጀመሩ፤ አሁንም ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም፤ ኑ እንውረድ፣ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው:: እግዚአብሔርም ከዚያ ምድር ሁሉ ላይ በተናቸው::"

ቀደም ሲል እንደተወያየነው፤ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ለመግባባት ካልቻሉ የመለያየት ዝንባሌ ያሳያሉ:: ሁላችንም ብንሆን ህብረት ማድረግ የምንወደው ልንግባባቸው ከምንችል ሰዎች ጋር ነው:: ስለዚህም ነው፣ በጥቅሉ፣ እንግሊዝኛ ተናጋሪ የሆኑ ህዝቦች ሁሉ አንድ ላይ የሚወግኑት፤ ፈረንሣይኛ ተናጋሪ የሆኑት ህዝቦች በአንድ ላይ የሚከማቹት፤ የስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪዎች እጅ ለእጅ የሚያየዙት፤ ነገሩ እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: ቋንቋ ልዮነቶችን ይፈጥራል፤ ልዮነቶችም የውድድርን፣ የመገፋፋትንና የግጭቶችን ስሜት ይፈጥራሉ:: ጠለቅ ብለን ካየነውም፤ ጦርነቶች ብዙውን ጊዜ የሚጫሩት በቋንቋ ልዮነቶች ምክንያት ነው::

በመሆኑም፤ አንዳንድ የመንግሥቱ ዜጎች የልሣናት ስጦታዎችን ጠቀሜታ ካልተገነዘቡና ስጦታውንም ካልተቀበሉ፤ በእነርሱና በሌሎች የመንግስቱ ዜጎች መካከል ግጭትና አለመግባባቶች መከሰታቸው አይቀሬ ነው፤ ይህ ደግሞ አሳዛኝ ነገር ነው:: ሰማያዊ ስጦታ የሆኑት ቋንቋዎች በተቀበሏቸው ሰዎች መካከል አንድነትን የመፍጠር (የማዋሃድ) ኃይል አላቸው:: ለዚህም ነው ሉሲፈር በንጉሡ ልጆች ላይ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትንና የሰማያዊ ስጦታዎችን መፍሰስ አጥብቆ የሚዋጋው:: አንዳንዶቹን የመንግሥቱን ዜጎች የልሣናትን ስጦታ የሚቃወሙ አስተምህሮችን (ዶክተሪኖችን) እንዲያዘጋጁ ያበረታታቸዋል:: እንደዚህ በማድረጉም ሁሉም የመንግሥቱ ዜጎች አንድ የሚያደርጓቸውን የጋራ "ቋንቋ" እስመናገራቸውን እርግጠኛ ለመሆን ይሞክራል:: ከፍ ባለ ደረጃ



ልሣናትን በመቃወም ለምሳሌም "ልሣናት እውነተኛ ነገሮች አይደሉም" ወይም "ለመጀመሪያዎቹ ለኢየሱስ ተከታዮች ብቻ የተሰጡ ናቸው" ወደሚሉ አስተምህሯዊ አቋሞች የሚኖሩን በዚህ ምክንያት ነው:: እነዚህ በእግዚአብሔር የተሰጡ ቋንቋዎች በዚህ ዘመን የሉም (አይሰሩም) እያሉ የሚያስተምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች አሉ:: እንዳስመታደል ሆኖ እነዚህ ት/ቤቶች የሚያስተምሩት ድንቁርናን ነው:: ይሁን እንጂ በነዚህ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሣናት ላይ የሚሰነዘሩ ተቃውሞዎች ጉዳቶታቸው አንዳንድ የንጉሡ ዜጎች የመንግሥቱን ሕይወት ለመለማመድ የሚያስፈልጋቸውን ሙሉ ኃይል እንዳይቀበሉ እንቅፋት መሆናቸው ነው::

ሰይጣን እኛ በልሣን መናገር ስንጀምር አደጋ ውስጥ መግባቱን ያውቃል:: ልሣናት በሕይወታችን ልዩ ልዩ አቅጣጫዎች የሚያጋጥሙንን መሰናክሎች የምናሸንፍባቸው ቁልፍ ነገሮች ናቸው:: ለምሣሌ ያህል፣ እኔ በትምህርቴ እጅግ ደካማና የመጨረሻውን ዝቅተኛ ውጤት የማገኝ ተማሪ ነበርኩ:: በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበርኩበት ጊዜ በልሣን መናገር ከጀመርኩ በኋላ በትምህርት ቤት ውስጥ ከነበሩ ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት ያለው ተማሪ ሆንኩ፤ ትምህርቴን ሳጠናቅቅም በክፍሌ ከነበሩ ተማሪዎች መካከል አንደኛ ሆኜ ነው:: በመሆኑም ልሣናት፤ የመንግስቱ ዜጎች ለሆኑ ግለሰቦች ሕይወታቸውን እንዲታደሱና ለመንግሥቱ ዓላማ ጉዳዮች ኃይልን እንዲለማመዱ የሚያስችሉ ስጦታዎች ናቸው::

### የመንግሥቱ ዜጋ በመሆን በልሣናት መናገር አስፈላጊ ነገር ነውን?

በልሣን ሳንናገርም የመንግሥቱ ዜጎች ልንሆን እንችላለን:: ይሁን እንጂ ከመንግሥቱ ጋር በሚኖረን ተግባቦት ችግሮች ያጋጥሙናል፤ እንደገናም ቀደም ሲል እንደተናገርኩት፣ የመንግሥቱን ሕይወት ለመኖር የሚያስፈልገንን ኃይል እናጣለን:: ከዚህ ቀጥሎ የማቀርብላችሁ ምሳሌያዊ ማብራሪያ የመንፈስ ስጦታዎችና በተለይም ልሣናት እጅግ የተለመዱ መሆናቸውን ያሳያችኋል::

በእኔ ቤተክርስቲያን ውስጥ፤ ከተለያዩ አገራት የመጡ አባላት ወይም እንግዶች አሉኝ:: ከነዚህ መካከል ፊሊፒኒዮ የተሰኘ ቋንቋ የሚናገሩ ፊሊፒንሳውያን ሰዎች ይገኛሉ:: ከሀይቲ የሆኑ ክሪኦል የተሰኘ ቋንቋ የሚናገሩ ሃይቲያውያንም አሉ:: የስፓኝ ቋንቋ የሚናገሩ ሜክሲኳውያንም ከእኛ ጋር አሉ:: ከፊሊፒንስ የሆነች አንዲት ሴት በፊሊፒኒዮ ቋንቋ የጌታን ጸሎት ብትጸልይ ብዙዎቻችን ፈጽሞ አንገነዘባትም፤ ይሁን እንጂ ሊረዳት የሚችል ሰው ይኖር ይሆን? አዎን ከእራሷ እናት ምድር የሆኑ ሰዎች ያደምጧታል:: የሃይቲ ዜጋ የሆነው ሰው ከመዝሙር መጽሐፍ በክሪኦል ቋንቋ ቢያነቡ፣ ለእኛ ምንም ትርጉም አይሰጠንም፤ የሃይቲ ዜጎች

ለሆኑ ሰዎች ግን ትርጉም ያለው ነገር ነው፡፡ ከሜክሲኮ ለሆኑ የስፓኝ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ይህንኑ ልንል እንችላለን፡፡

እኛ እነርሱን ልንሰማቸው ያለመቻላችን፤ ቋንቋቸው እርባና ቢስ ነው ማለት ነውን? የሚነጋገሩበትስ ቋንቋ እውነተኛ አይደለም ልትል ያስችልሃልን? ወይስ ደግሞ እነርሱ የሚናገሩትን ነገር ማመንህ ወይም አለማመንህ፤ ቋንቋቸው ትክክለኛ የመሆኑን እውነት ይለውጠዋልን? በፍጹም፡፡ እነርሱን ተገነዘብካቸውም ወይም ተግባባሃቸውም ቋንቋቸው ህጋዊ የሆነ ቋንቋ ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> "በዓለም ምናልባትም ቁጥር የሌለው የቋንቋዎች ዓይነት ይኖራል፤ ቋንቋ የሌለውም ህዝብ የለም፡፡ እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፤ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል፡፡"

ከእነዚህ የቤተክርስቲያን አባላት ወይም እንግዶች መካከል አንደኛው እንግሊዝኛ ቋንቋ ተማረ እንበል፡፡ እንግሊዝኛ ቋንቋ የትውልድ አገሩ ቋንቋ ባለመሆኑ፤ በአገሩ ካሉ ሰዎች ጋር ለመነጋገር ስልኩን በሚያነሣበት ጊዜ ቋንቋውን ወደ አገሩ ቋንቋ ይቀይራል፡፡ በመሆኑም ከባህማስ የሆነ መረጃ የሚፈልግ ከሆነ እንግሊዝኛ ይጠቀማል፤ ነገር ግን መረጃውን የሚፈልገው ከአገሩ ከሆነ የእናት አገሩን ቋንቋ ይናገራል፡፡

በተመሣሣይ መንገድ፤ በምድር ላይ ሆነህ በልሣናት ስትናገር፤ ልክ ስልክህን አንስተህ ከእናት አገርህ ጋር እንደመነጋገር ያለ ነው፤ በትውልድ ቋንቋህም ትነጋገራለህ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፤ "በልሣን የሚናገር ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያስተውለው የለምና፤ በመንፈስ ግን ሚስጥር ይናገራል፡፡" ጸሎትን በሚመለከት በሰውኛ ቋንቋችን ከምንጸልይ ይልቅ አብልጠን በልሣን ልንጸልይ ያስፈልገናል፡፡ ይህም የሚሆነው ከመንግሥተ ሰማይ ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ የግንኙነታችን መሻት እንዳይዳከም ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ገዢው የእግዚአብሔርን ልብና ፈቃድ እንደሚያውቅ ይነግረናል፡፡ በመሆኑም በመንፈስ በምንጸልይበት ጊዜ፤ ንጉሡ እኛን እንደሚሰማንና ከእርሱም የጠየቅነውን ነገር እንደምንቀበል እናውቃለን፤ ምክንያቱም ገዢው እንደ አስተዳደሩ ፈቃድ እንድንጸልይ ስለሚረዳን ነው፡፡ ከመንግሥተ ሰማይ ጋር ቀጥተኛ መስመር ያስፈልገናል፤ ልሣናትም ቀጥተኛ የግንኙነት መስመሮች ናቸው፡፡ በመንፈስ በተሞላህ ጊዜ፤ በቀኑ በየትኛውም ክፍለ ጊዜና ከንጉሡ - አባትህ ጋር መገናኘት በምትሻበት በየትኛውም ሰዓት በልሣን መጸለይ ትችላለህ፡፡ ስለዚህ ነው፣ ጳውሎስ

> **ከመንግስተ ሰማይ ጋር የሚያገናኝ ቀጥተኛ መስመር ያስፈልገናል፤ ልሣናት ያ ቀጥተኛ መስመር ናቸው፡፡**



እንደሚለው፣ እኔና አንተ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አብልጠን መሻት የሚያስፈልገን፡፡ መንፈሳዊ ስጦታዎች ከሰማያዊው መንግሥት የሆኑ ጠቃሚ ህብቶች ናቸው፡፡

አንዳንድ ሰዎች በልሣን መፀለይን ዝም ብሎ እንደ ጉርምርምታ (መንተባተብ) ይቆጥሩታል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ትክክለኛው ነገር ተቃራኒው ነው፡፡ ሰማያዊ ስጦታ የሆኑት ቋንቋዎች፤ በምድር ካለ ማንኛውም ቋንቋ ይልቅ የልብን ሀሣብና ጥያቄዎች ከሰማይ ጋር ማገናኘት ይችላሉ፡፡ በልሳናት ስንጸልይ የምንናገረው በአዕምሯችን አይደለም፤ ይልቁንም በመንፈሳችን በኩል ነው፤ በመሆኑም መንፈስ ማንኛውንም ፍላጎቶቻችንን ያስተላልፋል፡፡ ለእኔ በእንግሊዝኛ ቋንቋ መጸለይ የእኔን የመጸለይ ችሎታ የሚያካትት ነው፡፡ ለዚህም ነው አብዛኛውን ጊዜ በልሣን የምጸልየው፡፡ በልሣናት መጸለይን እወዳለሁ፣ ምክንያቱም ፀሎቴ "መተርጎም" አያስፈልገውም፡፡

እንዲያውም የሰማይ መንግሥት ዜጋ ለሆነ ሰው በልሣናት መጸለይ እንደ ምርጫ የሚወሰድ ነገር እንዳልሆነ ደምድሜአለሁ፡፡ ምናልባትም በልሣናት መናገር በማይታመንበት ወይም በማይተገበርበት ቤተክርስቲያን ውስጥ አድገህ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ የተቀበልከው አስተምህሮ ይሁን ቤተክርስቲያንህ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖርህ አላደረጉህም፡፡ ይህ ግንኙነት እንዲኖርህ የሚያደርጉት የኢየሱስ መስዋዕታዊ ሥራና በአንተ ውስጥ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ መንግሥቱ አምጥቶሃል፤ በልሣን የመናገር ችሎታንም በመስጠት ከንጉሡ አባት ጋር ግንኙነትን እንድታደርግ አስችሎሃል፡፡

## የልሣናት ልዩ ልዩ መገልጫዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁለት የተለያዩ የልሣናት ዐይነቶች ተጠቅሰዋል፡፡ እነኝህ ልዩነቶች የሚያመለክቱት የቋንቋዎችን ገጸ ብዙ ጠቀሜታና ግንኙነቱን እንደምናደርግባቸው ሰዎች ሁኔታ የግንኙነታችን ዐይነት መለዋወጥ የመቻሉን እውነት ብቻ ነው፡፡

### ከንጉሡ ጋር ቀጥተኛና ግላዊ ተግባቦት ለማድረግ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በአብዛኛው የምንነጋገረው፤ በመጀመሪያው የልሣን የግንኙነት ዓይነት ላይ ሲሆን፤ እርሱም ከንጉሡ ጋር ለሚኖረን ቀጥተኛና ግላዊ የሆነ ግንኙነት የምንጠቀምበት ነው፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በልሣን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፡፡ የሚያስተውለው የለምና፤ በመንፈስ ግን ሚስጥርን ይናገራልና፡፡"

## ሌሎችን የመንግሥቱን ዜጎች አስመልክቶ ከሰማይ መንግሥት ጋር ስመገናኘት

ሁለተኛው ዐይነት በልሣናት የሚደረግ ግንኙነት ግላዊ ለሆነ ጉዳይ ሣይሆን በጋራ ለሆነ ግንኙነት የምንገለገልበት ነው:: ጳውሎስ ለመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የመንግሥቱ ዜጎች ለአገልግሎት የተሰጡትን መንፈሳዊ ስጦታዎች በግል ከተሰጡት መንፈሳዊ ስጦታዎች ጋር በማነጻጸር እንዳስተማረው፤ የመጀመሪያዎቹ የመንግሥቱ ዜጎች የአጥቢያ ጉባኤዎችን በሚያደርጉበት ጊዜ በስብሰባው የሚካፈሉትን ሁሉ ለማነጽ የሚያገለግሉ ናቸው:: ይህም ለማያዊ ስጦታ በሆኑ ቋንቋዎች የንጉሡን ፈቃድ ለህዝቡ ማሣወቅን የሚያካትት ነው:: በጉባኤው ያሉ ሁሉ መልዕክቱን በትክክል እንዲረዱት ለማድረግ፤ በስብሰባው በተካፈሉት ሰዎች ቋንቋ መልዕክቱ ይተረጎማል:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

“ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል:: ለአንዱ ጥበብ መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና . . . ለአንዱም በልዩ ዐይነት ልሣን መናገር ለአንዱም በልሣናት የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ይሰጠዋል::”

“እናንተ የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ:: እግዚአብሔርም በቤተክርስቲያን አንዳንዶችን አስቀድሞ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛም ነቢያትን፣ ሦስተኛም አስተማሪዎችን፣ ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን፣ ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታ፣ እርዳታንም፣ አገዛዝንም፣ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሣኖችንም አድርጓል:: ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን?”

“እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ምንድን ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፣ ትምህርት አለው፣ መግለጥ አለው፣ በልሣን መናገር አለው፣ መተርጎም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን:: በልሣን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ::”

“ስለዚህም ምክንያት በልሣን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ”

ጳውሎስ ያስተማረው፤ የንጉሡን ፈቃድ ለማያዊ በሆኑ ቋንቋዎች አማካይነት በገዢው እርዳታ የንጉሡን የልብ አሣብ ለሕዝቡ ለመግለጥ ለአንዱ ይሰጠዋል:: ጳውሎስ፤ ስጦታውን “ለግል መታነጽ” ሳይሆን “ለጋራ ጥቅም” ማለቱን ልብ ይበሉ:: ይህም ህዝቡ ሁሉ የንጉሡን ፈቃድ እንዲያውቁ፣ በቃሉም በኩል



ለመምከርና ለማጽናናት የሚደረግ ነው:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ያጠቃልላል፤

> ልሣናት የገዢው ህልውና በእኛ ሕይወት ውስጥ ለመኖሩ ተጨማሪ መገለጫ ነው

“ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ፣ በልሣኖች ከመናገር አትከልክሉ፤ ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን::” በጉባኤ መካከል የሚነገሩ ልሣናትና የልሣናት ትርጉሞች፤ በመንግሥቱ ህገ መንግሥት ተደንግጎ በተቀመጠው መመሪያ መሠረት እስከተፈጸሙ ድረስ ድርጊቱን ልናበረታታ ያስፈልገናል::

## በልሣን የምንናገርባቸው ዐሥር ምክንያቶች

በልሣናት ከመጸለይ ይልቅ በመንፈስ መሞላት የበለጠ ነገር ነው፤ ይሁን እንጂ በልሣናት መናገር ገዢው በእኛ ሕይወት ውስጥ ለመኖሩ ዓይነተኛና አስፈላጊ መግለጫ ነው:: በልሣን መጸለይ ፈጽሞ የማይደርቅና የማያቋርጥ ምንጭ ነው:: መንፈሳዊ ሕይወታችንን ያበለጽጋል፤ ይገነባልም:: በእኔ የሕይወት ልምምድ፤ ሌሎቹ የመንፈስ ስጦታዎች እንዲለቀቁ ለማድረግና ለመጠቀም ወሣኝና ቁልፍ ነገር ነው:: እርግጥ ነው ይህ ልሣናትን በመተርጎም ፀጋ ሲደገፍ ይገባዋል፤ ይልቁንም ከሌሎች በተለይም ከትንቢት፣ ከጥበብና ከእውቀት ስጦታዎች ጋር በተጓዳኝ የሚሄድ ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ቋንቋ መጠቀም የሚያስፈልጋቸው ስጦታዎች ናቸው::

ከዚህ በመቀጠል ማንኛውም የመንግሥቱ ዜጋ ለምን በልሣናት መናገር እንደሚያስፈልገው ዐሥር ምክንያቶችን በዝርዝር እንመልከት::

### 1. ከመንግሥቱ ጋር ግንኙነት ስለመኖሩ ምልክት በመሆኑ ነው::

ብዙውን ጊዜ፤ ልሣናት መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የመኖሩና በመንፈስ የመሞላታችን የመጀመሪያ መለኮታዊ ማስረጃ ናቸው:: ይህንን እውነት በበዓለ ሃምሣ ቀን የኢየሱስ ተከታዮች መንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ተመልክተናል:: ቀጥሎ ደግሞ በተርሴሱ ሰው በጳውሎስ መንግሥታዊ አገልግሎት ውስጥ አይተነዋል:: ባለመድኃኒቱ ሉቃስ በየሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ዘግቧል፤ “አጵሎስ በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ አንዳንድ ደቀመዛሙርትንም አገኘ::”

እዚህ ስፍራ ላይ ሰዎቹ "ደቀመዛሙርት" መባላቸውን ልብ በሉ:: እነዚህ ሰዎች በመሠረቱ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት ነበሩ፤ ጳውሎስ እያላቸው ያለው ይህን ይመስላል፤ "እናንተ አሁን በትክክለኛው መንገድ ላይ ናችሁ፤ ነገር ግን ስለ ኢየሱስ ልትሰሙ ያስፈልጋችኋል፤ ዮሐንስ የመሠከረለት ስለእርሱ ነበር:: እናንተም እርሱ ያዘጋጀላችሁን ተስፋ ልትቀበሉ ያስፈልጋችኋል:: በመንፈስ ቅዱስ ልትሞሉ ይገባችኋል::"

እነዚህ ደቀመዛሙርት ለጳውሎስ፣ "መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳን አልሰማንም" አሉት:: እነዚህ ሰዎች በዚህ ዘመን በቤተክርስቲያን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታቸው በንቃት እንዳይሠራ ሥነ-መለኮታቸው ከከለከላቸው ሰዎች ብዙም አይለዩም:: በንጉሡና በመንግሥቱም ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ ገዢው በሕይወታቸው ስለሚጫወተው ሙሉ ሚና ገና አልተረዱም::

እነዚህ ደቀመዛሙርት የመንግሥቱን ወንጌል በሰሙ ጊዜ፤ ይህም መጥምቁ ዮሐንስ አስቀድሞ እንዳመለከታቸውና ጳውሎስም በዝርዝር እንደገለጠላቸው፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውሃ ተጠመቁ:: ጳውሎስ እጆቹን በጫነባቸውና በጸለየላቸውም ጊዜ፤ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ፤ ወዲያውያኑም በልሣናት ተናገሩ፣ ተነበዩም::

ሰማያዊ ስጦታ በሆኑት ቋንቋዎች መናገራችን፤ ከአገር ቤት (ከመንግሥተ ሰማይ) ጋር ግንኙነት እንዳለን ምስክር ነው::

**2. ለማነጽ ነው::**

በልሣን መናገር መንፈሣችን እንዲታነጽና እንዲታደስ ያደርጋል:: በገዢው በኩል ከንጉሡ ጋር ግንኙነት ባደረግን ጊዜ በግል እንጠናከራለን:: ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤ "በልሣን የሚናገር ራሱን ያንጻል"፣ በመሆኑም ለእኛ የተሰጡን ልሣናት ለአዳም እንደነበረው ያለምንም ጣልቃገብ በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት እንዲያስችሉን ነው::

**3. የገዢው ህልውና በውስጣችን መኖሩን እንዲያሳስበን ነው::**

ልሣናት የመንፈስ ቅዱስ ህልውና በውስጣችን እንዳለ ያሳስቡናል፤ የእርሱንም ህልውና በተረዳን ጊዜ እንጽናናለን፣ እንበረታታለንም:: ኢየሱስ እንዲህ አለ፤

"እኔም አብን እለምናለሁ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን



ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር፤ በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ::"

**4. ጸሎታችን ከንጉሡ ፈቃድ ጋር የተስማማ ሆኖ እንዲቀጥል ያደርጋል::**

በልሣን መጸለይ ጸሎቶቻችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ተስማምተው እንዲቀጥሉ ከማድረጉም በላይ በራስ ወዳድነት ከመጸለይ የተቆጠብን እንድንሆን ያደርገናል:: ቀደም ሲል ከጳውሎስ መልዕክት ላይ እንደጠቀስኩት፤

"እንዲሁ ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንደምንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፤ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሣብ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለቅዱሳን ይማልዳልና::"

**5. እምነትን ለማነሳሳት ይረዳል**

በልሣናት መጸለይ እምነትን ያነሣሣል:: መንፈስ ሙሉ ለሙሉ ጥያቄዎቻችንን እንደሚመልስ ባወቅን ጊዜ፤ ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ እንችላለን:: እምነትን ማግኘት ደግሞ በንጉሥ - አባት ዙፋን ፊት በዓላማና በመተማመን በመቅረብ በልሣን ወደመጸለይ ይመራናል:: የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ የሆነው የይሁዳ መልዕክት ፀሀፊ ስለ እምነትና በልሣን መናገርን አስመልክቶ "እናንተ ግን፣ ወዳጆች ሆይ፣ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖት ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ ቅዱስም እየጸለያችሁ ..." ሲል ይናገራል::

**6. በዓለም ነገር ከመመረዝ ተጠብቀን እንድንቆይ ይረዳናል**

ዓለማዊ በሆነ ባህል መካከል እየኖርን እንኳን፤ ልሣናት ያለማቋረጥ ከእግዚአብሔር መንግሥት ባህል ጋር ግንኙነት እንዲኖረን ያደርጋሉ:: በስራ ላይ ሆነን፣ በቤታችን ወይም በማንኛ ውም ስፍራ ሆነን ከንጉሥ - አባት ጋር መነጋገር እንችላለን:: በገዢው አማካይነት ከንጉሡ ጋር የሚኖረን ግንኙነት፤ አስተሳሰባችንና ድርጊታችን ንጹህ እንዲሆን ይረዳናል:: ራሳችንን ብቻ ሳይሆን በሰማያዊ ተግባቦት በኩል በመንግሥቱ ጉዳና ያሉትን ሌሎችን ጭምር እናደፋፍራለን:: ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈስዊም ቅኔ እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ::"

## 7. ለማናውቃቸው መጸለይ እንድንችል ያስችለናል

መንፈስ ቅዱስ እኛ ፈጽሞ የማናውቃቸውን ነገሮች ያውቃል፤ በመሆኑም ሰማያዊ ስጦታ በሆኑት ቋንቋዎች አማካይነት በመጸለይ በሰላምና በመታመን ልንማልድ እንችላለን:: ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ፤ "እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ስለ ቅዱሳን ይማልድልናል" ሲል ይናገራል::

## 8. መንፈሳዊ መነቃቃትን ለመቀበል ነው::

ልሣናት ለጭንቀት፣ ላለመረጋጋትና እንቆቅልሽ ለሆኑብን ነገሮች፤ እንደ የመንፈሳዊ ህክምና ዘዴዎች ናቸው::

"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ፤ አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና ሃሣባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል::

## 9. ምስጋናን በማቅረብ እንዲረዳን

ልሣናት በመንፈሣዊ ነገሮች ውስጥ ያልሰመዱትን ይረዳሉ - ሁላችንም ደግሞ ለንጉሡ የሚገባውን ምስጋናና ውዳሴ ማቅረብ እንድንችል ይረዱናል:: ሰዋዊና መንፈሳዊ የሆነውን ቋንቋ በማጣመር መጸሰይ ከንጉሡ ጋር ከምናደርጋቸው ከሌሎች ግንኙነቶች በተጨማሪ አዕምሯችንና መንፈሳችን ምስጋናችንን እንዲገልጽ ይረዳዋል:: ጳውሎስ፣ "በመንፈሴ እጸልያለሁ፤ በአዕምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ፤ በአዕምሮም ደግሞ እጸልያለሁ" ሲል ጽፏል::

## 10. አንደበታችንን መግዛት እንዲያስችለን

በመጨረሻም - ግን በትንሹ ሳይሆን - ሰማያዊ ስጦታ የሆኑ ቋንቋዎች አንደበቶቻችን በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ያደርጋሉ፤ ይህም በሕይወታችን ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ነገር ነው:: በአዲስ ኪዳን በያዕቆብ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተጽፎ ይነበባል፤ "ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት ነው:: ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ:: ወንድሞቼ ሆይ፣ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም:: ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውሃ ያመነጫልን?" አንደበት ለገዢው ታልፎ ከተሰጠ ብቻ ነው ከንጉሡና ከመንግሥቱም ጋር የተስማማ የሕይወትን ቃል ይናገር ዘንድ በቁጥጥር ሥር ሊውል የሚችለው::



## ልሣናት ለመላው የሰው ዘር የተሰጡ ናቸው

በመንግሥቱ ባህል መገለጫ ላይ ያተኮረውን ይህንን ምዕራፍ ለማጠቃለል፤ በልሣናት መናገር ለካሪዝማቲካውያንና ለፔንተኮስታል ክርስቲያኖች ብቻ የተሰጠ እንዳልሆነ ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: ለመላው ዓለም የተሰጠ ነው፤ ምክንያቱም ንጉሡ - ልጅ የመጣው በምድር ላይ ላሉ ህዝቦች ሁሉ ይህንን ስጦታ ሊሰጣቸው በመሆኑ ነው:: በአሁኑ ጊዜ በምድር ላይ ሰባት ቢሊዮን የሚጠጋ ህዝብ እንዳለ ይገመታል:: ስጦታው ለሁሉም ዘሮች ነው - ለቻይናውያን፣ ለፈረንሣዊያን፣ ለሱዳናውያን፣ ለአውስትራሊያውያን፣ ለዳንሽ፣ ለሜክሲኳውያን ሁሉ ነው - የእግዚአብሔር የልብ ሃሣብ ለሁሉም ነው፣ ልዩነት የለም::

> በልሣናት መናገር በራስህ ሰዋዊ የትውልድ ቋንቋህ እንደምትናገረው ተገቢ ነገር ነው::

በበዓለ ሃምሣ ቀን ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ "የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና" አላቸው:: እንደ መንግሥቱ ተጠሪነታችን፤ ሰዎች ሁሉ (ያለምንም ልዩነት) ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዲገቡ መርዳት የእኛ ተግባር ነው፤ በዚህም የልሣንና ሌሎችን ስጦታዎች ከገዢው ሊቀበሉ ይችላሉ፤ ይህም በምድር ላይ የመንግሥቱን ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል::

## የልሣናትን ዓላማ ልብ ይበሉ፤ ተግባቦት ነው

ልሣናት ውብ ነገሮች ናቸው፤ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ አስተምህሮዎች፣ ቤተእምነቶች እንዲያውም በጥቅሉ ሃይማኖት ተደርገው ይወሰዳሉ:: ልሣናት በሰማይና በምድር መካከል ተግባቦት እንዲኖር የሚያስችሉ ከሰማይ የተሰጡ ቋንቋዎች ወደ ግብ የሚያደርሱን መንገዶች የመሆናቸውን እውነት ለማየት ተስኖናል::

ልሣናት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አስተዳዳራዊ ነገሮች ሆነው ሣለ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች አድርገን እንወስዳቸዋለን:: በልሣናት በኩል ገዢው ጥያቄዎቻችንን ለንጉሡ ያቀርባል፤ የንጉሡንም ፈቃድ ወደ እኛ ያመጣል:: ያለ ገዢው ውጤታማ የሆነ ጸሎት ለመጸለይ አንችልም፤ ምክንያቱም የንጉሡን ልብ የሚያውቀውና ጥያቄዎቻችን ከመንግሥቱ ዓላማዎች ጋር የሚጣጣሙበትን መንገድ የሚረዳው እርሱ ነው::

በልሣናት መናገር በራስህ ሰዋዊ የትውልድ ቋንቋህ እንደምትናገረው ተገቢ ነው፤ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሣይኛ ወይም ስዋሂሊ ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ አዘውትሮ በልሣን ይናገር ነበር። እንዲህ ሲልም ጽፏል፤ "በመንፈሴ እጸልያለሁ፤ በአዕምሮም ደግሞ እጸልያለሁ።" እንደ መንግሥተ ሰማይ ዜግነታችን እኛም በተመሳሳይ ሁኔታ ልናደርግ ይጠበቅብናል።



# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## የገዢው አስተዳደር

*የሰው ዘር ራሱን በራሱ ማስተዳደር አለመቻል፤*

*የአስተዳደርን ተፈላጊነት ያመለክታል።*

የአንድ ገዢ ቀዳሚ ኃላፊነት ለእርሱ ታልፎ በተሰጠው ግዛት ላይ አስተዳደርን ማስፈን ነው። እንደዚሁ ሁሉ፤ ሰማያዊው ገዢ ቅኝ ግዛት በሆነችው ምድር ላይ መንግሥታዊ አስተዳደርን የማስፈን ኃላፊነት አለበት። እርሱ በዚህ ያለው የመንግሥቱን ዜጎች በግዛቱ ላይ እንዴት ሥልጣን እንደሚኖራቸው ለማሠልጠን ነው፤ ምክንያቱም ይህ በእርሱ አመራር ሥራ የሚኖረን ይፋዊ ተግባራችን ነው።

በምዕራፍ ዐስር ውስጥ እንደተመለከትው፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የመንግሥቱ ዜጎች በቅኝ ግዛቱ ውስጥ መንግሥታዊ የሆነውን ተግባራቸውን ማቀላጠፍ ይችሉ ዘንድ በገዢው በኩል የተሰጡ የውክልናና የኃይል ክፍፍሎሽ ናቸው። ዓላማቸውም በምድር ከባቢ ሁሉ ላይ በጎ የሆነ ተጽእኖ ያመጡ ዘንድ ነው። ንጉሡ ልጅ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፤ ሰዎችን ፈውሷል፤ አጋንንትን አስወጥቷል፤ ተአምራትን አድርጓል፤ እንዲያውም የሰርግ ቤት አስተዳዳሪ በተጨነቀ ጊዜ እርሱን ለመርዳት ውሃን ወደ ወይን ጠጅ ለውጧል። በምድር ላይ የሚታዩ ተግባራዊ ሥራዎችን አከናውኗል። በገዢው ኃይል በኩልም የሰዎችን ችግሮች ለመፍታት ዞሯል። በዚህ ዘመን በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእኛ ሕይወት የቀጠለው ሥራውም ይሄው ነው።

### ሥልጣናዊ ኃይል የተሰጠው ገዢው እንደፈቀደ ነው

በምድር ባለው መንግሥት፣ ገዢው በቅኝ ግዛቱ ውስጥ የተለያዩ ሰዎችን በተለያዩ አስተዳደራዊ የሥልጣን ስፍራዎች ላይ እንዲሾም በንጉሡ ሥልጣን ተሰጥቶታል። ሰማያዊውን አስተዳደር በሚመለከትም አሠራሩ እንዲሁ ነው። ጳውሎስ፤ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ከዘረዘረ በኋላ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ እያንዳንዱን ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።" የትኛዎቹ ስጦታዎች ለማን እንደሚሰጡ የእርሱ መብትና ኃላፊነት ነው። የገዢውን ሥልጣንና ኃይል አግባብ ባለው ሁኔታ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ልንማር ያስፈልገናል፤ እንደዚያ ከሆነ ድንቀኛ የሆነ ሥራውን ለዓለም

በማስተዋወቅ በምድር ላይ ባለው መንግሥት ለውጥን ለማምጣት እንችላለን::

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ይኖሩ ለነበሩት የመንግሥቱ ዜጎች በጻፈው የመጀመሪያ መልዕክቱ፤ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ዝርዝር አስፍሯል፤

"ስለ መንፈሳዊ ነገርም ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ፤ ለአንዱ ጥበብ መናገር (ቃል) በመንፈስ ይሰጠዋል፤ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር (ቃል) ይሰጠዋል፤ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፤ ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፤ ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፣ ለአንዱም ትንቢት መናገር፣ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፣ ለአንዱም በልዩ ዐይነት ልሳን መናገር፣ ለአንዱም በልሣኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል::"

## ሥልጣናዊ ኃይል የተሰጠው ለሰማያዊው አስተዳደር አገልግሎት ነው

ከገዢው ዘንድ የተቀበልነው የትኛውም ሥልጣንና ኃይል ለሰማያዊው መንግስት አገልግሎት እንጂ ግላዊ ለሆነ ጥቅማችን አይደለም:: ገዢው የመንግሥቱን ሥልጣን በውክልና ሲሰጠን፤ ቀጥተኛ በሆነ መንገድና በመንግሥቱ ህገ መንግሥት አማካይነት፣ ስጦታዎቹን በትክክለኛና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ያስተምረናል:: የማስተዳደር ተግባሩ ሌሎችን የምናገለግልበት እንጂ በእነርሱ ላይ ጌታ የምንሆንበት እንዳልሆነ ያሳየናል:: ጴጥሮስ በመጀመሪያው መጽሐፉ እንዲህ ይላል፤ "ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደመሆናችሁ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ::" በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ጳውሎስም እንዲህ በማለት ያረጋግጥልናል፤

> ከገዢው የተቀበልነው ማንኛውም ሥልጣንና ኃይል ለሰማያዊው መንግሥት ነው::

> "የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፤ መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፤ ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፤ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው:: ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል::"

እንዳለመታደል ሆኖ፤ የመንፈሳዊ ስጦታዎችን አጠቃቀም አስመልክቶ አንዳንድ የማይመቹ ልምምዶች አሉ:: አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ



ስጦታዎቻቸውን ከመንግሥቱ ዜጎች ላይ ገንዘብን ለመግፈፍ ይጠቀሙበታል:: ሰዎቹ ገንዘብን ወደ እነርሱ ቢልኩ እንደሚፈወሱ በመንገር ፈውስን "ይሸጣሉ":: ወይም ደግሞ ስጦታውን አግባብ በሌለው መንገድ ይጠቀሙበታል፤ ለምሣሌም፤ የትንቢት ስጦታን ከእግዚአብሔር ዘንድ መልዕክት አለን በማለት ከማጽናናትና ከመገንባት ይልቅ ሰዎችን ለመኮነን ይገለገሉበታል::

የእውነተኛ አስተዳደር ዓላማ ዜጎቹን ማገልገል ነው:: በመሆኑም፤ የሰማያዊው መንግሥት ገዢ ስጦታ ስጥቶህ ከሆነ፤ የመንግሥቱ ዜጎች የሆኑ ወገኖችህን ለማገልገል እንድትጠቀምበት ነው:: ስጦታው ገንዘብ እንድትሰበስብበት፣ ስለራስህ ማንነት ጉራ እንድትነዛበት ወይም ሌሎችን እንድትቆጣጠርበት የተሰጠህ አይደለም::

## ሥልጣናዊ ኃይል የግል ንብረት አይደለም

ምድራዊ በሆነው መንግሥት፤ አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ሥራውን እንዲሠራበት መኪና ወይም ኮምፒዩተር ቢሰጠው፤ እርሱ በፈለገው መንገድ ሊጠቀምበት የሚችል የግል ንብረቱ አይደለም:: በይፋ የተሰጠውን ኃላፊነት ይወጣ ዘንድ ብቻ እንዲረዳው ሊጠቀምበት ይገባል:: መኪናው ወይም ኮምፒዩተሩ የእርሱ የግል ንብረት አይደለም፤ መንግሥት በጠየቀው ጊዜ ወይም እርሱ ሥራውን ሲለቅ ያስረክባል:: እነዚህን ነገሮች መጠቀሙ እንደ ችሮታ የተደረገለት ነገር እንጂ መብቱ ሆኖ አይደለም::

በሰማያዊው መንግሥት ለተሰጡት መንፈሳዊ ስጦታዎችም ይህ ያልነው ነገር እውነት ነው:: ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ የመንግሥቱ ዜጎች ይጠቀሙበት ዘንድ በገዢው የተሰጣቸው ኃይል ከራሳቸው ችሎታ የመጣ እንደሆነ ማመን ጀምረዋል:: ይህ ቀደም ሲል የተወያየንበትን ችግር ወደማስከተል ያመራል፣ ይኸውም የተሰጣቸውን ኃይል ለራስ ዓላማ መገልገል:: ይህ ኃይልን ያለ አግባብ ለተጠቀመውም ይሁን አገልግሎቱን ለሚቀበሉትም አደገኛ ነው:: እርሱ ጥሪውን ከማሳካት ይደናቀፋል፤ ከእርሱ አገልግሎትም ተጠቃሚ ሊሆኑ የተገባቸው ሰዎች ሊያገኙት የሚገባውን እርዳታ ሳያገኙ ይመለሳሉ::

## በውክልና የተሰጠው ኃይል የቅኝ ግዛቱን ጥያቄዎች ሁሉ የሚመልስ ነው

ገዢው፤ ከንጉሡ - ልጅ ጋር በመተባበር፤ ለመንግሥቱ ዜጐች የውክልና ኃይል ይሰጣል፣ ይህንን የሚያደርገው የሰማያዊውን መንግሥት ከፍተኛ ተጽእኖ በምድር ላይ ለማሳደር ሲባል የቅኝ ግዛቱን ጥያቄዎች ሁሉ ይመልስ ዘንድ ነው:: ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ ሲል ጽፏል፤

"እርሱም (ኢየሱስ) አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ ሌሎቹም ነቢያት፣ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፤ ሙሉ ሰውም ወደመሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመስራትና ለክርስቶስ አካል ህንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ:: "

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ ስለ መንፈሣዊ ስጦታዎች ከተለያየ ተልዕኮአቸው፤ ማለትም በመንግሥቱ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ሁሉ ለማነጽ ካላቸው ጠቀሜታ አኳያ ይናገራል:: በመሆኑም፤ መንግሥቱ በዓለም በሚኖሩ ሰዎችና በዓለም ካባቢ በሚያሳድረው በጎ ተጽእኖ ህልውናውን ያሳያል:: በገዢው በኩል ለመንግሥቱ ዜጎች በውክልና የተሰጠው ኃይል፤ ከጨለማው መንግሥት የሚሰነዘርባቸውን ግጭትና ተቃውሞ መቋቋም ይችሉ ዘንድ ያስታጥቃቸዋል፤ ይህ ጥቃቱ እነርሱን ለመጥቀም ሳይሆን በዓለም የሚኖሩትን ህዝቦች ሁሉ ለማውደም የሚሰነዘር ጥቃት ነው::

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በመንግሥቱ አስተዳደር አኳያ ሥልጣናዊ ኃይል ይገልጣሉ

እስኪ አሁን ደግሞ ዘጠኙን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች፤ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያ መልዕክቱ ባሰፈረው ዝርዝር መሠረት እንቃኝ:: ምልከታችን ገዢው በምድር ላይ ካለው የተለየ አስተዳደር አኳያ ይሆናል:: ስጦታዎቹ በሶስት ፈርጆች ይፈረጃሉ፤

- ሦስቱ አንድን ነገር *ይናገራሉ::*
- ሦስቱ አንድን ነገር *ይሠራሉ::*
- ሦስቱ አንድን ነገር *ይገልጣሉ::*

"የሚናገሩት" ሦስቱ የንግግር ስጦታዎች ናቸው፤ ትንቢት፣ ልዩ ዓይነት ልሣናትና በልሣኖች የተነገረውን መተርጎም:: "የሚሠሩት" ሦስቱ ደግሞ የኃይል ስጦታዎች ናቸው፤ እምነት፣ ተአምራታዊ ኃይል ወይም ተአምራትን ማድረግ እና የመፈወስ ስጦታ:: "የሚገልጡት" ሦስቱ የመገለጥ ስጦታዎች ናቸው፤ የመልዕክት ወይም የጥበብ ቃል፤ የመልዕክት ወይም የእውቀት ቃል እና መናፍስትን መለየት::

ልዩ ልዩ ዓይነት ስጦታዎች ቢኖሩም፤ የዓላማ አንድነት ግን አላቸው፤ ይህም የመንግሥቱ ዜጎች የንጉሡ ባህርይ እንዲኖራቸውና ምድር የመንግሥተ ሰማይን መልክ ትይዝ ዘንድ በመለወጥ የመንግሥቱን ኃይል እንዲጠቀሙ ነው:: ከመገለጥ ሥጦታዎች በመነሣት



እንጀምራለን:: እነዚህ ስጦታዎች እውነታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ዓላማን፣ ሰበበ ነገርን፣ መድረሻንና አንድ ነገር ሰዋዊ፣ መንግሥተ ሰማያዊ ወይም ከጨለማው መንግሥት መሆኑን ከመለየት ጋር የተያያዙ ናቸው።

## ሥልጣናዊ የጥበብ ቃል

"ለአንዱም ጥበብ መናገር በመንፈስ ይሰጠዋል:: " መልዕክት ወይም የጥበብ ቃል የእግዚአብሔርን ፈቃድና መለኮታዊ ዓላማ አስመልክቶ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን መለኮታዊ ግልጠት ነው:: የመንግሥቱ ዜጎች በችግርና ግራ በመጋባት ወቅት ሊያደርጉ የሚችሉትን በላጭ ነገር እንዲያውቁ የሚያስችላቸው ከገዢው ዘንድ በእውቅና የተሰጠ ኃይል ነው:: ለምሣሌ ያህል፤ ህጋዊ ምክር በምትፈልግበት ጊዜ ጠበቃ ታነጋግራለህ፤ እናም ላጋጠመህ ሁኔታ ተስማሚ የሆነ ህጋዊ ጥበብ ይሰጥሃል:: የጥበብ ቃል በአንድ በተለየ ሁኔታ ውስጥ ምን መናገር ወይም ማድረግ እንደሚገባን በገዢው በኩል ከንጉሡ ዘንድ የሚሰጠን ልዩ መመሪያ ነው::

**የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የመንግሥቱ ዜጎች ምድርን በመንግሥተ ሰማይ ምሣሌ ለመለወጥ እንዲያስችላቸው ያገለግላሉ::**

ከመንግሥቱ ህገ መንግሥት ሊገኝ የሚችል ተገቢ (የተፈጥሮ) የሆነ ጥበብ አለ:: ለምሣሌ ያህል የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ በሆነው በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ፤ የሙሴ ተተኪ የሆነውን ኢያሱን፣ በሕይወቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ በቃሉ የተማረውን ነገር ተግባራዊ እንዲያደርግ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አበረታታው፤ "የዚህ ህግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜ መንገድህ ይቃናልሃል፤ ይከናውንልሃልም::"

መለኮታዊ የሆነው ጥበብ በተፈጥሮ ከሚገኘው ጥበብ የተለየ ነው፤ ይህ ጥበብ በገዢው በኩል ለመንግሥቱ ዜጋ (ወይም ዜጎች) በቀጥታ የሚመጣ ሲሆን፤ በሕይወቱ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ውስጥ በጥበብ እንዲመላለስ ያስችለዋል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ጥበብ በራዕይ፣ በህልም፣ ከንጉሡ ዘንድ በሚመጣ መልአክ (መልዕክት)፣ ወይም ገዢው በመንግሥቱ ዜጋ ልብ ውስጥ በሚያሳድረው ቃል በኩል እንደሚለቀቅ ይገለጻል:: ለምሣሌ ያህል በጳውሎስ ሕይወት፤

- ✓ መንፈስ ቅዱስ በአንጾኪያ ይኖሩ ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች፣ ጳውሎስንና ባርናባስን ለተጠሩበት የመንግሥቱ ሥራ እንዲለዩዋቸው መመሪያ በመስጠት ተናግሮአቸዋል::

- ✓ ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም በመርከብ በሚወሰድበት ጊዜ መርከቧን አስቸጋሪ የሆነ ማዕበል ባጋጠማትም ጊዜ፤ ጳውሎስ በመርከቧ ውስጥ ለነበሩት ሁሉ የተስፋና የመጽናናትን ቃል ተቀበለ፤

"አይዟችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ፤ ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳን አይጠፋምና:: የእርሱ የምሆንና ደግሞም የማመልከው የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ ነበርና፤ እርሱም ጳውሎስ ሆይ አትፍራ፣ በቄሣር ፊት ልትቆም ይገባሃል፤ እነሆ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል አለኝ::" ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሆይ አይዟችሁ እንደተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን አምናለሁ:: ነገር ግን ወደ አንዲት ደሴት እንድንወድቅ ያስፈልገናል:: "

ጳውሎስ ከንጉሡ መልዕክተኛ የተቀበለው ማበረታቻ፣ ለዚያ ሕይወታቸውን ላስጨነቀው ሁኔታ እንዴት ዓይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው አሳያቸው::

የጥበብ ቃል ለተቀበለው ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ሊያገለግል ይችላል:: በሁለቱም ሁኔታዎች በኩል፤ የመንግሥቱ አስተዳደር ዜጎቹን በምድር በሚገኘው ቅኝ ግዛት ላይ አስተዳደራዊ ፖሊሲንና ዓላማን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዴት መተግበር እንዲችሉ ያስተምራል::

## ሥልጣናዊ የእውቀት ቃል

"ለሌላውም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር ይሰጠዋል::" ጥበብ ተግባራዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ እውቀት ደግሞ በውክልና ስልጣን እጅግ የተቀሳጠፉ ትክክለኛ የሆኑ ውሳኔዎችን ለመስጠት እንዲቻል አስፈላጊ የሆነው መረጃ እንዲኖር የሚያስችል ነው:: በአብዛኛው ከአስተዳደሩ ለአንተ የሚሰጡትን ፖሊሲዎች የመረዳት ችሎታህን የሚመለከት ነው፣ በተለይም ደግሞ ንጉሡ የሚያስበውን እንድትረዳ ችሎታን ይሰጥሃል፤ ይህም በገዢው በኩል በንጉሡ ልብ ውስጥ ስላሉ ስለተወሰኑ ጉዳዮች የሚሆን መለኮታዊ መገለጥ ነው::

ንጉሡ ሙሉ የሆነ እውቀት አለው፣ ነገር ግን ለዜጎቹ ሁሉንም አይገልጽላቸውም:: የእውቀት ቃል ንጉሡ ከሚያውቀው ተከፍሎ የሚሰጥ ነው - ይህም በተለይ ተግባራዊ ግዳጃቸውን ይወጡ ዘንድ የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ማለት ነው:: አንዳንድ የሰዎች (የምድር) መንግሥታት ለሠራተኞቻቸው "ማወቅ የሚያስፈልግህን ብቻ እወቅ" በሚል መርህ

> የዕውቀት ቃል
> የሚሰጠው ማወቅ
> የሚገባህን ስወቅ
> በሚል መርህ
> ተመስርቶ ነው::



ላይ ተመስርተው ኃላፊነቶቻቸውን ሊወጡ የሚያስፈልጋቸውን የተወሰኑ መረጃዎች ብቻ ይ ሰጧቸዋል:: የእውቀት ቃልም የሚሠራው በዚሁ መንገድ ነው::

የእውቀት ቃል ምናልባትም ውስጣዊ በሆነ መገለጥ፣ በልሣናት ትርጉም፣ በትንቢት ቃል፣ በራዕይ ወይም በመልአክ በኩል ይገለጥ ይሆናል:: እንደገናም፣ ይህ በተፈጥሮ ከሚሆን ልምምድ፣ ከመረጃ ወይም በጣም ከተዘወተረ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሊገኝ የሚችል አይደለም:: የእውቀት ቃል መለኮታዊ ነው፤ ይህም ማለት በተለመደው መንገድ የምናውቀው አይደለም፣ በራሳችን ልንማረው የምንችለውም አይደለም:: ለምሳሌ:-

- ✓ ኢየሱስ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛትን ሰማርያዊት ሴት፣ አምስት ባሎች እንደነበሯትና አሁን ደግሞ ከሌላ ሰው ጋር እንደምትኖር በነገራት ጊዜ የእውቀትን ቃል እንደተጠቀመ ያመለክታል:: የዚህ የእውቀት ቃል መግለጫ ዓላማ የእርሷን አትኩሮት ለመሳብና በንጉሡ ላይ ያላት እምነት እንዲዳብር ለማድረግ ነው፣ በዚህም ሌሎች ደግሞ ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር እንዴት እርቅ ማድረግ እንደሚችሉ ይገነዘቡ ዘንድ ነበር::
- ✓ አጋቦስ የተባለ ነብይ፤ በመላ በሮም ግዛት አስተዳደር ስር ባሉ ግዛቶች ሁሉ ላይ ረሃብ እንደሚሆን የሚያስጠነቅቅ የእውቀት ቃል ተሰጠው:: (በዕውቀት ቃልና በጥበብ ቃል መካከል ያለውን ተያያዥነት በመገንዘብ፣ የመንግሥቱ ዜጐች የእውቀት ቃሉን በመቀበል ተግባራዊ አደረጉ (የጥበብ ቃል ተጠቀሙ):: በዚህ ረገድ በይሁዳ ይኖሩ ለነበሩ ለመንግሥቱ ዜጎች እርዳታን ይልኩ ዘንድ ወሰኑ)
- ✓ ሐናንያና ሰፔራ የተባሉ ባልና ሚስት ለቤተክርስቲያን ስለ ሰጡት የገንዘብ እርዳታ እንደዋሹ ለጴጥሮስ መለኮታዊ እውቀት ተሰጥቶት ነበር::
- ✓ ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ፤ በእስያ በነበሩ በሰባቱ አብያተክርስቲያናት የመንግሥቱ ዜጎች ስለነበረው ውስጣዊ መንፈሣዊ ሁኔታቸው የዕውቀት ቃል በራዕይ ተሰጥቶት ነበር፤ በመሆኑም ከንጉሡ ዘንድ የሆነውን የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ መልዕክት ሊያስተላልፍላቸው ችሏል::

ገዢው በእውቀት ቃል አማካይነት፤ ከንጉሡ ዘንድ የሆነውን መልዕክት ለመንግሥቱ ዜጎች እንዲህ፤ "በዚህ ስፍራ እየተሠራ ያለው ስህተት ይህ ነው"፣ ወይም "በቅኝ ግዛቱ ውስጥ እየተከናወነ ያለው ትክክለኛ ሥራ ይሄኛው ነው፤ በመልካም ሥራችሁ በመትጋት ቀጥሉ" ብሎ ሊያስተላልፍ ይችላል:: ምናልባት ደግሞ ለአንድ የመንግሥቱ ዜጋ

ሌላው ሰው (ዜጋ) በመንግሥቱ ውስጥ በአግባቡ ለመሥራት ምን እንደሚያስፈልገው እንዲገልጽለት አስፈላጊ መረጃ ሊሰጠው ይችላል።

## ሥልጣናዊ የእምነት ኃይል

"ለሌላውም በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል"። ሥልጣናዊ የእምነት ኃይል መለኮታዊ የሆነ እምነት ወይም መተማመን ነው። ይህ ዜጐቹ የመንግሥቱን ፖሊሲዎች በእምነት በመቀበል ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ እንዲችሉ ከአስተዳደሩ የሚሰጣቸው ልዩ የእምነት ችሎታ ነው።

እያንዳንዱ የመንግሥቱ ዜጋ እምነት አለው። በርግጥ የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሃፊ፤ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፤ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" ሲል ጽፏል። በመሆኑም የእምነት ስጦታ፣ ማለት እኛ ንጉሡ ልጅ ስለ እኛ በፈፀመው መስዋእት አምነን፣ ምህረት በመቀበል ወደ መንግሥቱ ከገባንበት እምነት ጋር አንድ አይደለም። ይህ ድነትን ያገኘንበት እምነት የሚመነጨው የመንግሥቱን ህገመንግሥት በማመናችን አማካይነት ነው። ለዚህም ነው ጳውሎስ፣ "እምነት ከመስማት ነው፤ መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው" ሲል የጻፈው። የእምነት ስጦታ ወይም የመንፈስ ፍሬ የሆነው "ታማኝነት" ተብሎ የሚጠራውም አይደለም። የመንግሥቱ አማኞች በዕለት ተዕለት ኑሯቸው በንጉሡ ላይ ታምነው ዓላማውን በሕይወታቸው በመተግበራቸው መጽናናትንና ሰላምን እንደሚያመጣላቸው እንደሚያምኑት ዓይነት እምነትም አይደለም። እንደዚህ ያለው እምነት ግን በሕይወት ተሞክሮና በንጉሡ ቃል ተግባራዊነት እያደገ ሊሄድ የሚችል ነው።

ይልቅስ፤ የእምነት ስጦታ፤ ለአንድ የመንግሥቱ ዜጋ የመንግሥቱን ዓላማ አስመልክቶ የተፈቀደ ልዩ የውክልና ሥልጣን ሊሆን ይህም ያለምንም ጥርጥር በመጨረሻው ላይ ሊገለጥ ስላለው ለአንድ ለተለየ ውጤት እንደሆነ ያውቃል። ይህንን ዓይነት እምነት አስመልክቶ ጥቂት ምሣሌዎችን ቀጥዬ አቀርባለሁ። ምሣሌቹንም ስትቃኙ በእምነት ስጦታና ተአምራትን በማድረግ ስጦታ መካከል ያለውን ተያያዥነት ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። (በዚህ አውድ ውስጥ አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ ሰጪ፤ የእምነት ስጦታን "ድንቅን - ሠሪ" እምነት ሲል ያብራራዋል።)

- የሦስቱ ዕብራውያን ሰዎች እምነት፣ በጥንታዊቷ ባቢሎን የመንግሥት ባለሥልጣናት የነበሩት እግዚአብሔር ይነድ ከነበረው እቶን እሣት ውስጥ ሊያመጣ ይችላል ማለታቸው።



- የኢየሱስ መታመን፣ ከሞተ አራት ቀናት የሆነው **አልዓዛር ከሞት** ተነስቶ በሕይወት ይኖራል ማለት።
- የጴጥሮስና የዮሐንስ ማመንታት የሌለው (ጽኑ) እምነት፤ ገና ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ሽባ ሆኖ የተወለደው ሰው በኢየሱስ ስም ይፈወሳል ማለት።

በመሆኑም የእምነት ስጦታ፣ ገዢው፤ የመንግሥቱ ዜጎች የተስፋውን ቃልና የሰማያዊውን አስተዳደር ኃይል እንዲታመኑ የሚያነቃቃበት ስጦታ ነው። በዚህም የመንግሥቱ ዜጎች የተሰጣቸውን ተግባራዊ ግዳጅ፤ ገዢው ሥራውን ለመስራት በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ጥንቃቄ ይወስዳል በሚል መታመን ያለፍርሃት እንዲወጡ ያበረታታቸዋል።

## ሥልጣናዊ የፈውስ ኃይል

"ለሌላውም የመፈወስ ስጦታ በዚያው በአንድ መንፈስ ይሰጠዋል"። የመፈወስ ስጦታዎች ለበሽታዎችና ለልዩ ልዩ አካላ ጎደሎነት መለኮታዊ ፈውሶች ናቸው። እዚህ ላይ የትኛውንም ዓይነት ተፈጥሯዊ ችሎታ ማለትም የህክምና ሳይንስ ወይም የሰው ተፈጥሯዊ ችሎታ ምንጭ የሆነ ማንኛውንም ዓይነት ዘዴ አያካትትም። በምድር ካለው ከሰማያዊ መንግሥት አስተዳደር አኳያ፤ ፈውስ ንጉሡ ለህዝቡ ደህንነት ያለው በጎ ፈቃድና ያንንም መልካም ፈቃዱን ለማረጋገጥ ያለውን መርሃ ግብር የሚያሣይ ነው።

ይህ የመፈውስ ኃይል "ስጦታዎች" ተብሎ በብዙ ቁጥር ተገልጾ እናገኛለን። "ፈውስ" የሚለውን ቃል በዚህ በያዝነው አውድ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ በብዙ ቁጥር እንጠቀምበታለን፤ "የመፈወስ ስጦታዎች" እያልንም እንጠቅሳለን። በብዙ ቁጥር መጠቀሱ የተለያዩ ዓይነት በሽታዎችን የመፈወስ ችሎታን ለመግለጽ ነው። የማቴዎስ መጽሐፍ፣ "ኢየሱስም በምኩራባቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በህዝብም ያለውን <u>ደዌና ህማም ሁሉ እየፈወሰ</u> በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር" በማለት ይዘግባል።

የመፈወስ ስጦታዎች፤ ልዩ ልዩ በሽታዎችን፣ አዕምሮአዊም ሆነ አካላዊ፣ ከራሳችንም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ወይም ከንጉሥ - አባት ጋር እንዳንስማማ የሚያደርጉንን ሁሉ ይዳስሳሉ። ይህም ፍርሃትን፣ ብቸኝነትንና ድብርትን የመሳሰሉ ችግሮችን ያካተተ ነው። የፈውስ ስጦታዎች የሰው ሁለንተናን የሚያድሱ፣ ሙሉና ጤነኛ እንዲሆን የሚያስችሉ ናቸው።

በሐኪሞች ህክምናም ይሁን በአካላዊ ተፈጥሯዊ የመፈወስ ሂደት የሚከናወን የትኛውም ዓይነት ፈውስ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን ልንገነዘብ ያስፈልገናል። የመፈወስ ስጦታዎች ሐኪሞችን

የሚቃረኑ አይደሉም:: ይሁን እንጂ መለኮታዊ ፈውስ፣ በህክምና ባለሙያዎች ክብካቤ የሚገኝ ፈውስም ይሁን የአካል ተፈጥሯዊ የመፈወስ ችሎታ ለየቅል የሆኑ የፈውስ መንገዶች መሆናቸውን ልብ ልንል ይገባናል:: የመጀመሪያው የሚመጣው ከሌላ ዓለም ነው፣ ሁለተኛው ፈጣሪ በገዛ ራሳችን አካል ውስጥ ያስቀመጠውን የመፈወስ ችሎታ <u>የሚያግዝ</u> ብቻ ነው፣ ሦስተኛው ደግሞ ውስጣዊ የሆነና እብሮን የተፈጠረ ብቃት ነው:: በተጨማሪም፤ በፈውስ ስጦታዎችና ንጉሡ እኛን ለመፈወስ ያለውን ፍላጐት ከቃሉ በተረዳነው እምነት በመለማመድ በተቀበልነው ፈውስ መካከል ልዩነት እንዳለ ልናውቅ ያስፈልጋል:: ምናልባትም አንድ ሰው ከጴጥሮስ የመጀመሪያው መልዕክት፤ "እርሱ ራሱ በስጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ" የሚለውን ቃል ለራሱ አድርጎ በመውሰድ ቢጠቀምበት ሊፈወስ ይችላል:: ይሁን እንጂ የፈውስ ስጦታዎች ገዢው ልዩ የሆነ የፈውስ ስጦታን በሰጠው በመንግሥቱ ዜጋ በኩል የሚገለጡ ናቸው:: ተግባራዊ የሚሆኑትም የመንግሥቱ ዜጋ የገዢውን የኃይል ውክልና ተቀብሎ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው::

> የመፈወስ ስጦታዎች የሰው ሙሉ አካል እንዲታደስ የተሰጡ ናቸው::

ሌላው ልንገነዘበው የሚያስፈልገን ነገር፣ የመፈወስ ስጦታዎችንም ሆነ ማንኛቸውንም ሌሎች ስጦታዎችን፣ በራሳችን ፈቃድ እንዲሠሩ ልናደርግ አንችልም:: ስጦታዎቹ እንደ ገዢው ፈቃድ ብቻ የሚሰጡ ሲሆን፤ እርሱ የሚሰጠንን ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ ለመቀበል ደግሞ በተከፈተ አዕምሮ ተዘጋጅተን ልንጠብቅ ያስፈልጋል::

ቀጥሎ የሚቀርቡት አንዳንድ የፈውስ ምሣሌዎች፤ ከህክምና እርዳታ በላይ የሆኑ፤ ከገዢው ኃይልን በተቀበለ ሰው ጣልቃገብነት አማካይነት የተከናወኑ ናቸው::

- ✓ እጁ የሰለለች ሰው ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ሆነ፤ ሰውነቱ ሽባ የሆነና በሞት አልጋ ላይ የነበረው የመቶ አለቃው ሎሌ ተፈወሰ፤ ለአሥራ ሁለት ዓመታት ደም ይፈሳት የነበረች፣ አንዳች እርዳታ ባታገኝም ወደ ብዙ ባለመድሃኒተኞች የሄደች ሴት ሙሉ ለሙሉ ተፈወሰች፤ እያንዳንዳቸው የተፈወሱት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይሠራ በነበረው በኢየሱስ ነበር::
- ✓ በጴጥሮስ አገልግሎት በኩል፤ ሽባ የነበረውና ለስምንት ዓመታትም በአልጋ ላይ የነበረው ኤኒያ የተባለ ሰው ሙሉ ለሙሉ ፈውስን ተቀበለ::
- ✓ ጳውሎስ፣ በሚሊጢን ደሴት ውስጥ በተቅማጥና በንዳድ በሽታ ታሞ የነበረውን ሰው ፈወሰው::



ፈውስና ከፍያለ (ኮምፓሽን) እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው ይባላል:: ርኅራኄ የድጋፍ ስሜት (ሲምፓዚ) ብቻውን በቂ አይደለም:: የመደገፍ ስሜት ሲባል ለሰሰውዬው ሃዘኔታ ሲሰማህ ማለት ነው፤ ስለ በሽታው ታዝናለህ፣ ልትረዳውም ትፈልጋለህ:: ከፍ ያለ ርኅራኄ (ኮምፓሽን) ግን ሰውዬውን ከበሽታው ወይም ከሚያሰቃየው ችግር ነፃ ለማውጣት የምናሣየውና ልንቆጣጠረው የማንችለው መሻት ነው:: ከፍ ባለ ርኅራኄ ውስጥ መከራን ለማቅለል የሚሻ እውነተኛ የሆነ ፍቅር አለ::

በመሆኑም በምድር ላይ ባለው በሰማያዊ መንግሥት አስተዳደር ውስጥ፤ የፈውስ ስጦታዎች ገዢው ለመንግሥቱ ዜጐች፣ ሌሎችን በመንግሥቱ ባልተለመደ በማናቸውም ነገር እንዳይወረሩ ለማድረግ፣ በውክልና የሰጣቸው ናቸው:: በዚህ መንገድ፣ በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ችግሩ እንዳለ ያረጋግጣል፣ አሉታዊ ሁኔታዎችን እንደሚያስከትልም ያሳያል:: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፣ ፈውስ ትክክለኛ ፍትህን የሚያሰፍን ነው:: ገዢው የመንግሥቱ ዜጎች በጤንነት የመኖር መብታቸውን ያረጋግጣል::

## ሥልጣናዊ የተአምራት ኃይል

"ለሌላውም ተአምራትን የማድረግ ኃይል ይሰጠዋል::" በአንድ በኩል ስንመለከት፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ ከተፈጥሯዊ ችሎታዎቻችንና ልምምዶቻችን በላይ ስለሆኑ ተአምራት ናቸው:: ይሁን እንጂ የተአምራት ኃይል ወይም ተአምራትን ማድረግ ከሰው ልጆች መረዳት ያለፈ ልዩ የሆነ ተግባር ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ተአምር፣ የተለመደው ተፈጥሯዊ ሂደት ሲዛባ፣ የተለመደው የነገሮች ባህርይ በጊዜያዊነት ሲቋረጥና ሁኔታዎች መልካቸውን ሲቀይሩ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል የሚደረግ ከአዕምሮ የሚያልፍ መለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ነው:: ስለዚህ ስጦታ ጥቂት ምሣሌዎችን እንመልከት::

- ✓ እስራኤላውያን ከግብፃውያን አሳዳጆቻቸው አምልጠው በደረቅ ምድር ይሻገሩ ዘንድ፤ የሙሴ ቀይ ባህርን መክፈል::
- ✓ በነቢዩ ኤልያስ አማካይነት ታላቅ ረሃብ በነበረበት ዘመን ለመበለቲቱ ያለማቋረጥ የፈሰሰላት የዘይትና የዱቄት አቅርቦት::
- ✓ የኢየሱስ አምስት እንጀራና ሁለት አሣን በማብዛት ከአምስት ሺህ በላይ የሚሆን ሰዎችን መመገቡ::
- ✓ የኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሣት::
- ✓ የጴጥሮስ ዶርቃን ከሞት ማስነሣት::
- ✓ በጳውሎስ የተሰበከውን የመንግሥቱን ወንጌል በመቃወሙ ምክንያት የጠንቋዩ ኤልማስ (በርያሱስ) ለጊዜው መታወር::

አስደናቂው ነገር፤ ተአምራት የማድረግ ኃይልን ወይም ተአምራትን የግሪክ ቃል "ዱናሚስ" ይላል፤ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ" ባላቸው ጊዜ የተጠቀመው ተመሳሳይ ቃል ነው:: ተአምራት የመንግሥቱ ኃይል "ፍንዳታ" ናቸው፤ በሚመለከሩትም ሰዎች ዘንድ አግራሞትን የሚያመጡ ድንቅ ነገሮች ናቸው::

በመሆኑም ሰማያዊው መንግሥት በምድር ላይ ባለው አስተዳደር ውስጥ፤ ተአምራት በመንግሥቱ አስተዳደር በኩል ለህዝቡ ልዩ ለሆኑ ፍላጎቶች የሚሰጡ ናቸው:: ተአምሩ ምንም ይሁን ምን፣ ምግብን መስጠት ቢሆን፤ ከሞት ማስነሣት ወይም ሌላ ምንም ነገር ቢሆን፤ የተለጠ ነው:: ተአምራት መዝናኛዎች አይደሉም፤ በገዢው ሥልጣን (ቁጥጥር) ሥር፣ በመንግሥቱ ዜጎች አማካይነት የመንግሥቱን ህልውና ለማረጋገጥና የቅኝ ግዛቱን ከባቢያዊ ሁኔታ ለመለወጥ የመቻሉን እውነት ለማሳየት የሚተገበሩ የገዢው ውጤቶች ናቸው::

## ሥልጣናዊ የትንቢት ኃይል

"ለሌላውም ትንቢት መናገር ይሰጠዋል" ትንቢት፤ ምድራዊ በሆነና በአድማጮቹ ወይም በአድማጩ በታወቀ ቋንቋ የሚነገር፤ በሆነ መንገድ ከንጉሡ ዘንድ የሚሰጥ መልዕክት ነው:: የመንግሥቱ ዜጎች ቀደም ሲል በመንግሥቱ ስለ ተነገራቸው መረጃ ከሰማይ አስተዳደር የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው::

ጳውሎስ የትንቢት ስጦታን አስመልክቶ እንዲህ ጽፏል፤

> "ፍቅርን ተከታተሉ፤ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ:: ልሣን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም የሚያስተውለው የለምና:: በመንፈስ ግን ሚስጥርን ይናገራል፤ ትንቢት የሚናገር ግን ለማነጽ፣ ለመምከርና ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል:: በልሣን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል:: ሁላችሁም በልሣኖች እንድትናገሩ እወድ ነበር፤ ትንቢተ ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ:: ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩ ባይተረጎም በልሣን ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል::"

ጳውሎስ እንዳለው፣ የትንቢት ዓላማ፤ ማነጽ፣ መምከርና ማጽናናት ነው:: ትንቢት ከስጦታዎች ሁሉ በጣም ጠቃሚ ስጦታ እንደሆነም ያመለክታል፤ ምክንያቱም የሚያንጸው የመንግሥቱን ዜጎች ሁሉ ነው:: "ማነጽ" የሚሰው ቃል በግሪክ ቋንቋ፤ መንፈሣዊ እድገትን አስመልክቶ "የመገንባትን ተግባር" የሚያመለክትን ሀሣብ ያዘለ ነው:: በመሆኑም ትንቢት በመንግሥቱ አቅጣጫ ለምችን ማበረታታትን ወይም



መገንባትን ያመለክታል:: "መምከር" ለሚለው ቃል የግሪክ ቋንቋ ትርጉም፤ "ከአንድ ሰው አጠገብ ሆኖ፤ ለመምከር ወይም "ለማጽናናት" መናገርን" የሚያመለክት ነው:: "ማጽናናት" ማለትም "ለማንኛውም ሰው ቀረብ ብሎ መናገርን የሚያሳይ ሲሆን፤ ይህም ከመምከር ይልቅ በታላቅ ትህትና የመጽናኛ ቃል መናገርን" የሚያሳይ ነው:: ይህንን ቃል የምመለከተው፤ ለምች በችግር ውስጥ በገቡ ጊዜ ከማረጋጋትና ሰላም እንዲኖራቸው ከማድረግ ጋር አያይዤ ነው::

ጳውሎስ በተለይ ይህ የትንቢት ስጦታ ሌሎችን ለመጥቀም በብርቱ ሊፈለግ እንደሚገባው ይናገራል:: ነቢዩ ኢዮኤል፤ "ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ይናገራሉ" እንዲሁም፤ "በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ መንፈሴን አፈሣለሁ፤ ትንቢትም ይናገራሉ" ሲል ተናግሯል::

> የትንቢት ዓላማ ማነፅ፣ መምከርና ማጽናናት ነው::

ትንቢት ለመንግሥቱ ዜጎች የተለጠ ታላቅ ስጦታ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ አጠቃቀሙ ተዛብቶ እንመለከታለን:: በዚህ ስጦታ አጠቃቀም ረገድ ልንከተላቸው የሚገቡ አብይ መመሪያዎች ቀጥለው ተዘርዝረዋል፤

1. ትንቢት የአንድዮሽ ወገን ብቻ አይደለም:: በለጭውና በተቀባዩ ሲረጋገጥ የሚገባው ነው፣ የሁለትዮሽ ወገን መግባባትና ትክክል መናበብን ያካትታል::
2. ሁልጊዜም ትንቢት ለመልዕክት ተቀባዩ መመሪያን ከመስጠት ይልቅ ቀደም ሲል ያወቀውን አንድ ነገር በማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው::
3. ትንቢት የሚነገረው እውቀት ላላቸውና ለሚረዱ ለምች ነው::
4. የማነጽ፣ የመምከርና የማጽናናት ተግባሮች በመንግሥቱ ዜጎች ጉባኤ መካከል የጉባኤው መሪ በሚያስተላልፈው በእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በኩል ሊተላለፉ ይችላሉ።
5. የትንቢት ስጦታ ፈጽሞ ሊከለከል አይገባውም፤ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "መንፈስን አታጥፉ፤ ትንቢትንም አትናቁ::"
6. ትንቢትን ወዲያውኑ በቅጽበት ከመቀበል ይልቅ መፈተን ያስፈልጋል:: ጳውሎስ፣ "ሁሉን ፈትኑ፣ እውነትን ያዙ" ብሏል:: በተጨማሪም፤ "ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ፣ ሌሎችም ይለዩዋቸው" ሲል ይናገራል::

7. የትንቢት ቃል ሰጪው በትንቢቱ "ቁጥጥር ሥር" የዋለ አይደለም። ትንቢቱን ለመናገር ወይም ላለመናገር ምርጫ አለው፤ ሊናገረው ምቹ የሚሆንበትንም ጊዜ መወሰን የእርሱ ድርሻ ነው። አንድ ሰው ትንቢትን በሚቀበልበት ጊዜ፣ በዓይነቱ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ላይ ሊያተኩርና በአጠቃቀሙም ረገድ ራስን መግዛትን ሊለማመድ ያስፈልገዋል። ጳውሎስ እንዳለው፣ "ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ ሁላችሁ በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ"፣ እንዲሁም፤ "የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፤ እግዚአብሔር የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና" ይላል።

በተጨማሪም፤ ሁሉም የመንግሥቱ ዜጎች በብርቱ ይፈልጉት ዘንድ እንዲበረታቱ በተባለው ትንቢት ስጦታና ለተወሰኑ የመንግሥቱ ዜጎች በመንፈስ በሚሰጠው "የነቢያት ቢሮ" መካከል ያለውን ልዩነት ልንገነዘብ ያስፈልገናል። ልዩነቱን በዚህ መንገድ ልናስበው እንችላለን፤ የትንቢት ስጦታ የሚሰጠው ሊመጣ ያለውን ነገር አስቀድሞ ለመናገር፣ ወይም የንጉሡን ፈቃድ ለማወጅ ነው። የነቢያት ቢሮ እንደ ትንቢት ስጦታ ሁሉ ሊመጣ ያለውን ነገር አስቀድሞ የመናገርን ጨምሮ ወይም የመንግሥቱ አስተዳደር ነገሮች ከመከሰታቸው በፊት ለአንድ ዜጋው ዜናውን አስቀድሞ እንዲቀበል የሚሰጠው ችሎታ ነው። ይህ ምናልባትም በመጭው ጊዜ ንጉሡ ሊያደርግ ያሰበውን ዕቅድ ማሳወቅ ሊሆን ይችላል። ነቢይ ሁል ጊዜ በእርሱ ሕይወት ውስጥ የሚሰሩ ሌሎች የመገለጥ ስጦታዎች አሉት፣ በተጨማሪ እንደ የእውቀት ቃል ወይም የጥበብ ቃል ወይም መናፍስትን የመለየት ስጦታዎች ይኖሩታል።

አንድ ሰው የትንቢት ስጦታን የሚለማመድ ቢሆን፤ ይህ ማለት ይህ ሰው የነቢይ ቢሮ ያለው ሰው ነው ማለት አይደለም። በሌላ አገላለጽ፤ ምናልባትም ይህ ሥፍራ እርሱ ለማያዊውን መንግሥት በቋሚነት የሚወክልበት ስፍራ ወይም ኃላፊነት አይደለም ማለት ነው። ይህም በአንድ በተወሰነ ጊዜ ከንጉሡ ዘንድ አንድ ልዩ መረጃ (መልዕክት) የተሰጠው ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ሰዎች የሌሎችን የነቢያት ቢሮ ጸጋ ልምምድ በመመልከት እነርሱም መጭውን ነገር ለመተንበይ ይፈልጋሉ፤ የሥልጣን ውክልና በሌለበት ሁኔታ ለመተንበይ ቢሞክሩ፤ ይህ ወደ ብዙ ግራ መጋባትና ስጦታውን ያለ አግባብ ወደመጠቀም ያመራል። እያንዳንዱ ሰው መሥራት ያለበት ገዢው በሰጠው ስጦታ ብቻ ነው።

የሚከተሉት አንዳንድ የትንቢት ምሣሌዎች ናቸው።

- ✓ በኤፌሶን ይኖሩ የነበሩ ደቀመዛሙርት መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉ ጊዜ፤ "በልሣናት ጸለዩ፤ ትንቢትንም ተናገሩ።"



- ✓ ወንጌላዊው ፊልጶስ ትንቢትን የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት።
- ✓ አጋቦስ የተባለው ነቢይ በሮም ግዛት ሥር ባሉ ሀገሮች ሁሉ ላይ ርሃብ እንደሚሆን ተነበየ። በተጨማሪም ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ በሮም ከተማ በቄሣር ፊት እንደሚቆም ተናገረ።

በመሆኑም ሥልጣናዊ የትንቢት ኃይል፤ የመንግሥቱ ዜጎች በመንግሥቱ ውስጥ በሚኖራቸው ሕይወት የሚደግፋቸውን ጠቃሚ የሆነ መረጃና መጽናናትም እንዲያገኙ በገዢው በኩል ለሰዎች የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ ያህል፤ ባሃማስ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር በነበረችበት ዘመን "እውሉ ንፋሱ ይመጣል፤ ነገር ግን የሚነሣውን የትኛውንም ችግር ለመቋቋም ለጊዜው የሚሆን እቅድ አለን። አንድ ነገር የሚከሰት ቢሆን መንግሥት ሊያደርግ የሚገባው ነገር ይሄ ነው" የሚሉ መልዕክቶችን ከአስተዳደሩ በመቀበል ግንኙነት እናደርግ ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ከሰማያዊው መንግሥት የሚመጡ ትንቢቶች፤ "በጣም አስቸጋሪ በሆነ ጊዜ ውስጥ እያለፋችሁ ነው፤ ነገር ግን ችግሮቻችሁን ለማቃለልና ከገባችሁበት ቀውስ ውስጥ እናንተን ለማውጣት እርዳታን እየላክን ነው" የሚሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በዚህ መንገድ፤ ትንቢት የመንግሥቱ ዜጎች በምንም ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ እያለፉ ይሁን፤ ሰማያዊው መንግሥት በእነርሱ ጉዳይ ዙሪያ አሁንም በሥራ ላይ እንደሆነ የሚያሳስብ ነው። ትንቢትን ከተቀበልን በኋላ፤ ምንም እንኳን ወዲያውኑ ተገልጦ ባናየውም፤ የምንፈልገው ነገር ሁሉ - ነጻ መውጣት ወይም ነፃነት፣ ሰላም ወይም ፈውስ ሊሆን ይችላል - በመንገድ ላይ መሆኑን ልናውቅ እንችላለን።

## ሥልጣናዊ መናፍስትን የመለየት ኃይል

"ለሌላውም መናፍስትን መለየት ይሰጠዋል።" መናፍስትን ለይቶ ማወቅ ወይም መናፍስትን የመለየት ስጦታ፤ የመንግሥቱ ዜጋ ስለመለኮታዊው ዓለምና ስለ አሠራሩም እውቀት እንዲኖረው ያደርገዋል። መገለጡም የሚያተኩረው ለብቻ ተነጥለው ባሉ መናፍስት ላይ ሲሆን፤ በጥበብ ቃል አማካይነት ከሚሆነው መለየት ጋር አሳክረን እንዳንመለከተውም ያስፈልጋል። መናፍስትን መለየት፤ መንፈሳዊ የሆነ አዕምሮን የማንበብ ብቃት፣ ስነ አዕምሯዊ አመለካከት ወይም አዕምሮን ሰርስሮ የመግባት ኃይል አይደለም። የሌሎች ሰዎችን ባህርይ ወይም ስህተቶችን ፈልፍሎ መግለጥም አይደለም። መናፍስትን የመለየት ስጦታ ሰዋዊ ባልሆኑ

> የመለየት ስጦታ
> ከንጉሡ ዘንድ
> የሆነውን ግንኙነት
> ለመለየት ያበቃናል።

መናፍስት ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። አንዳንዶች ይህን ስጦታ ክፉ መናፍስትን በመለየት ላይ ብቻ የሚያተኩር እንደሆነ አድርገው ያምናሉ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱንም ማለትም፤ መልካም የሆኑትን የሰማያዊውን መንግሥት መንፈሳዊ አካላትንና እርኩሳን የሆኑትን የጨለማውን መንግሥት መንፈሳዊ አካላትን መለየትን ጭምር የሚያካትት ነው። ጳውሎስ "ሰይጣን ራሱን የብርሃን መልአክ እንዲመስል ይለውጣልና" ሲል ጽፏል። የምንቀበላቸው መልእክቶች ወይም አስተያየቶች ከንጉሡ ወይም ከጠላቱ (ከክፉው) ዘንድ መሆኑን ለይተን ልናውቅ ያስፈልገናል።

የሥልጣናዊ የመለየት ኃይል አንዱ ምሣሌ፤ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን መልክ የመለየት ችሎታ ነው።

- ✓ ሙሴ ይህ ችሎታ ተሰጥቶት ነበር፤ በሁለተኛው መጽሐፉ በኦሪት ዘፀአት ሁኔታውን እንዲህ ዘግቦታል፤ "እግዚአብሔርም አለ፤ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ አለ፤ በዓለቱ ላይ ትቆማለህ፤ ክብሬም ባለፈ ጊዜ በሰንጣቃው ዓለት አኖርሃለሁ፤ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይህ እጋርዳለሁ፤ እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፤ ጀርባዬን ታያለህ ፊቴን ግን አታይም።"
- ✓ ነቢዩ ኢሣያስ ከተቀደሰው የሰማይ ንጉሥ ይህ ችሎታ በራዕይ ተሰጥቶት ነበር፤ እርሱም እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረዥምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፤ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፤ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው፤ በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፤ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። አንዱም ለአንዱ፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች፤ እያለ ይጮህ ነበር።"

የዚህ ስጦታ ሌላው ምሳሌ መለኮታዊ የሆኑ መገለጫዎችን ምንጭ መግለጥ ነው።

- ✓ ጳውሎስ በጨለማው መንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆና የሟርት መንፈስ ያለባትን ወይም መጭውን የመናገር ችሎታ የነበራትን ገረድ መንፈስ ለየው፤ መንፈሱንም ከእርሷ አወጣው።
- ✓ ቆርኔሌዎስ የተባለው የመቶ አለቃ በራዕይ የታየው መልአክ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ ተረዳ፤ በዚያ ራዕይ ውስጥም የተነገረውን መመሪያ ተግባራዊ አደረገ፤ በዚህም ምክንያት እርሱና ቤተሰቡ፤ ወዳጆቹም ሁሉ ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ግንኙነት አደረጉ።



ሥልጣናዊ መናፍስትን የመለየት ስጦታ አብዛኛውን ጊዜ የሚሠራው ከእውቀት ቃል ወይም ከጥበብ ቃል ጋር ተደራቢ ሆኖ ነው። የመንግሥቱን አስተዳደር በሚመለከት! ይህ ስጦታ የመንግሥቱ ዜጎች በዙሪያቸው ላለው መለኮታዊ ዓለም ንቁ ስሜት እንዲኖራቸው ለማድረግ ከመንግሥቱ የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ ያህል! የተሰጠህን የሥልጣን ውክልና በብቃት ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ቢገጥምህና ተግባራዊ ግዳጆችህን ለመወጣት ሳትችል ብትቀር፤ ሥልጣናዊ መናፍስትን የመለየት ስጦታህ ከጨለማው መንግሥት መናፍስት ተጽእኖ ሥር እንደሆንክ እንድታይ ያስችልሃል። ድል ለመንሳትም ምን ማድረግ እንደሚኖርብህ ሊነግርህ ይችላል።

## ሥልጣናዊ ልዩ ወይም የተለያዩ ዐይነት የልሣናት ኃይል

"ለአንዱም በልዩ ልዩ ዓይነት ልሣናት መናገር ይሰጠዋል።" ልዩ ልዩ ዓይነት ልሣናት፤ ተናጋሪው ወይም ሰሚው ሊረዳቸው በማይችላቸው ቋንቋዎች ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰጡ መለኮታዊ ንግግሮች ናቸው። እነዚህ ንግግሮች ገዢው ዜጎቹን አስመልክቶ ለንጉሡ የሚያቀርባቸው ገለጻዎች ወይም ከንጉሡ ዘንድ በገዢው በኩል ለዜጎቹ በምላሽ የተሰጡ ገለፃዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ቀደም ባለው ምዕራፍ ውስጥ፤ ልሣናት የመንግስቱ ዜጎች በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላታቸው እንደ ቀዳሚ ማረጋገጫ ምልክት መሆናቸውን ተነጋግረናል። ትኩረት የሰጠነውም እነዚህን ከሰማይ የተሰጡ ቋንቋዎች ማንኛውም አማኝ ሊቃበላቸው እንደሚገባ ነበር። በእነዚህ ልሳናት የመናገር ዓላማም እያንዳንዱ በየግል ከንጉሥ - አባት ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት ጠቀሜታ እንደሆነ ተመልክተናል። ልሣን በዋናነት በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔርን የምናወድስበት፣ የምናመልክበት፣ ጥያቄዎቻችንንም ለርሱ የምናቀርብበት መንፈሳዊ ልምምድ ነው። መንፈሳዊ ልሣን ብዙውን ጊዜ ግላዊ (ምሥጢራዊ) እና ለአንድ ሰው ለራሱ ብቻ የሆነ ሲሆን የልዩ ልዩ ዓይነት ልሣናት ስጦታ ግን ለጉባኤ የሆነና ሌሎችን የሚመለከት ነው።

በመሆኑም፤ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሣናት ስጦታዎችን ግላዊ ለሆነ ዓላማ ከምንጠቀምበት ልሣን ለይተን፤ ለጉባኤ አገልግሎት የሚውሉ ልሣናት በማለት እንጠራቸዋለን። የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳናት ስጦታ የሚገለጠው የመንግሥቱ ዜጎች በተሰበሰቡ ጊዜ ነው። ጳውሎስ እንደዚህ ሲል ጽፏል፤ ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? "ሁሉስ በልሣናት ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን?" በዚህ ስፍራ ጳውሎስ እያብራራ ያለው፣ ገዢው እንደፈቀደ ስለዜጎቹ ሁሉ ጥቅም ስለሚሰጣቸው የተወሰኑና ልዩ ስለሆኑ ስጦታዎች ነው።

ጳውሎስ፤ የመንግሥቱ ዜጎች በተሰበሰቡ ጊዜ ይህንን ስጦታ እንዴት ሊጠቀሙበት እንደሚገባ ምሳሌዎችን ይሰጣል::

> “በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፤ ትምህርት አለው፤ መግለጥ አለው፤ በልሣን መናገር አለው፣ መተርጎም አለው:: ሁሉ ለማነጽ ይሁን:: በልሣን የሚናገር ቢኖር ሁለት ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ፤ አንዱም ይተርጉም፤ የሚተረጉም ባይኖር ግን በማህበር መካከል ዝም ይበልና፤ ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር::”

የልሳናት ስጦታ በመንግሥቱ ዜጎች ጉባኤ መካከል በሚሠራበት ጊዜ፤ ያለምንም ማቋረጥ የሚነገር ወይም ደግሞ ሌሎች በልሣን እየተናገሩ ባሉበት በዚያው ሰዓት ውስጥ የሚነገር አይደለም:: በቅደም ተከተል የሚደረግና ሁለት ወይም ቢበዛ ሶስት ሰዎችን ብቻ የሚያካትት ነው:: ጳውሎስ በዚያ ስፍራ ልሣኑን መተርጎም የሚችል ሰው ከሌለ፤ ልሣናት በጉባኤ መካከል በጎላ ድምጽ መነገር እንደሌለባቸው ጽፏል:: የሚያቀርበውም ምክንያት ይህን የሚመስል ነው፤ “እንዲያማ ካልሆነ አንተ በመንፈስ ብትባርክ ባልተማሩት ስፍራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ እንዴት አድርጎ ለምስጋናህ አሜን ይላል?” እንደገናም ደግሞ ጳውሎስ አንድ ሰው የተቀበለው ልሣን እንዲተረጉምለት መጸለይ እንደሚገባው ይጠቁማል፤ ትርጉም ከተሰጠ ብቻ ልሣኑ ለጉባኤ ስለሚነገር ነው:: “ስለዚህ በልሣን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ::”

ንጉሡ በልሳን የምንጸልየው ምን እንደሆነ በትክክል እንድናውቅ የሚፈልግበት ጊዜ አለ፣ በሌሎች ጊዜዎች ደግሞ በልሣን የምንፀልየው ምን እንደሆነ አይገልጥልንም:: በልሣን የምንናገረውን ልንገልጸው እንችል ዘንድ መንገዱ ካልተሰጠን፤ በጉባኤ መካከል ልንናገረው አይገባንም::

የልሣን ስጦታ በአንተ መስራቱን እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? በውስጥህ ከፍ ያለ መሻትና በዙሪያህ ላሉ ሰዎች ከፍ ያለ ርህራሄ ይሰማሃል:: አንዳንዶቹ ቃላት በአዕምሮህ ውስጥ መዝለል ይጀምራሉ:: እነዚህን ቃላት በአሣብህ አይኖች ልታያቸው የቻልክ ይመስልሃል፤ ወይም ቃላቶቹ እየተወረወሩ ሲመጡ ይሰሙሃል:: ከዚያም ከመንግሥቱ ጋር ባለህ ግንኙነት እንደተሰጠህ የእምነትና ገዢው አንተን ሲያነሳሳ እንደታዘዝክበት መጠን ትናገራቸዋለህ::

ልሣንን የመተርጎም ስጦታ የተቀበለው ሰው፤ (ሌላ ሰው በመናገር ላይ እስካልሆነ ድረስ) ትርጉሙን ለመግለጽ መዘግየት የለበትም፤ ይልቁንም ሌሎች ከንጉሡ የተላከላቸውን ቃል በትክክል ከማድመጥ እንዳይሰናከሉ ትርጉሙን በእምነት ማቅረብ ይገባዋል:: በተጨማሪም፤ ቃሉ በእውነት ከንጉሡ ዘንድ ከሆነ፤ ዜጎቹን ያንጻል፤ አይኮንናቸውም ወይም ተስፋ አያስቆርጣቸውም:: እንደ ትንቢት ሁሉ፤ ብዙውን ጊዜ ልዩ ልሣን አንድን ነገር አስመልክቶ አዲስን መመሪያ ከመስጠት ይልቅ



አስቀድሞ የታወቀ ነገር ማጽኛ ወይም ማረጋገጫ ነው። አንዳንድ ጊዜም ትንቢት ልሣንን ተከትሎ የሚመጣ ሊሆን ይችላል።

በተጨማሪም፤ ይህንንና ሌሎችን መንፈሳዊ ስጦታዎችን የሚለማመድ ማንም ቢሆን፤ ራሱን የሚገዛ ሊሆንና በጉባኤውም ለመመዘን ፈቃደኛ ሊሆን ያስፈልገዋል:: ይህም የሚሆነው በመንግሥቱ ዜጎች መካከል ሰላምና ሥርዓትን ለማስፈን ነው:: ሁላችንም ይህን ልብ ልንል ይገባናል፤ ልሣናትም ይሁኑ ሌሎች ስጦታዎች የተሰጡን ማን በመሆናችን ወይም ምን ያህል መንፈሳውያን በመሆናችን አይደለም፤ ይልቁንም ንጉሡ እኛንና ከእኛ ጋር ያሉ ዜጎቹን በመውደዱና ከእኛም ጋር ግንኙነት ማድረግን ስለፈለገ ነው::

> ቃሉ በእውነት ከንጉሡ ዘንድ ከሆነ ዜጎቹን ያንጻል፤ አይኮንናቸውም ወይም ተስፋ አያስቆርጣቸውም

በመጨረሻውም፤ አንዳንድ ጊዜ የልዩ ልሳን ስጦታ በምድር ላይ ያለ ቋንቋን (ቋንቋዎችን) ቅርጽ ይይዛል፤ (ይጠቀማል)፤ ይህም ከመንግሥቱ ውጭ ያሉ ሰዎች መረዳት እንዲችሉና በዚህም ከንጉሡ ጋር ለመታረቅ እንዲቀርቡ ለማስቻል ነው:: በመሆኑም፤ ልሣናት ፖሊሲውን፣ ምኞቱንና ፈቃዱን ለዜጎቹና ለሌሎች በምድር ላሉ ህዝቦች ለማስተላለፍ እንዲችሉ ለመንግሥቱ ዜጐች ከሰማያዊ አስተዳደር የሚሰጡ ችሎታዎች ናቸው::

## ሥልጣናዊ ልሣንን የመተርጎም ኃይል

“ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል::” ልሣናትን የመተርጎም ኃይል የሚገለጠው ገዢው በልዩ ቋንቋ የተነገረውን ንግግር ትርጉም ለአንድ የመንግሥቱ ዜጋ ሲገልጽና፤ ሰውዬውም ትርጉሙን ለጉባኤ ሲናገር ነው:: በዚህ ዐውድ “ትርጉም” የሚለው ቃል ጠቃሚ ሀሣብ እንዳለው አምናለሁ:: ይህ ቃል በቃል እንደሚሆን ያለ ትርጉም አይደለም፤ ነገር ግን ዜጐች በሚሰሙት ሰዋዊ ቋንቋ ግንኙነቱን እንዲረዱ የሚያስችል ትርጉም ነው::

ለምሳሌ ያህል፣ በሰዋዊ ቋንቋ በምንነጋገርበት ጊዜ፤ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያለውን ቃል ወይም ሐረግ ወደ ሌላ ቋንቋ ቃል በቃል ልንተረጉማቸው የማንችላቸው አሉ፤ እንደዚያም ሆኖ መሠረታዊ የሆነ ትርጉማቸውን ይዘው ይተላለፋሉ፤ በተለይም በተለመደው የንግግር ወይም የጽሁፍ መደበኛ አውዳቸው ሳይሆን በንግግር ውስጥ ከያዙት ሀሣብ አኳያ የምንመለከታቸው ከሆነ ነገሩ የቀለለ ይሆናል:: እንዲህ ያለው ሁኔታ የሚፈጠረው፣ ለምሣሌ ያህል፣ በእንግሊዝኛ የተነገረውን አንድ ነገር ወስደን ለፈረንሣይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በምንተረጉምበት ጊዜ ነው:: በዚህም ምክንያት በተነገረበት ቋንቋና በትርጉሙ መካከል ምናልባት

የርዝመት ልዩነት ሊኖር ይችላል። ይህንን መሠረታዊ እውነት ልሣኖችን በመተርጎም ረገድ ልንገለገልበት እንችላለን። በሰማያዊው ቋንቋ የሚነገር ድምጽ ከተነገረበት መነሻ ድምፅ ረዝሞ ወይም አጥሮ ትርጉሙ ሲቀርብ ይችላል።

በግልጽ እንደሚታየው፤ ልሣንን የመተርጎም ስጦታ ለብቻው (ነፃ) ሆኖ የሚሠራ ሳይሆን፤ ልሣንን በመናገር ስጦታ ላይ የተመሠረተ ነው። ዓላማውም የሚሰሙት የመንግሥቱ ዜጎች ሁሉ መመሪያን እንዲያገኙ፣ እንዲጠነቀቁ፣ እንዲጠነክሩና እንዲጽናኑ የልሣኑንም ትርጉም በግልጽ (በጉልህ) እንዲረዱት ነው። ጳውሎስ፤ "ማህበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩ ባይተረጎም፤ በልሣኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል" ሲል ጽፏል።

## ውጤታማ የሆነ አገልግሎት

ሁሉም የሥልጣናዊ ኃይል ምሳሌዎች፣ እውነተኛ የሆኑና ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ላይ ሰማያዊውን መንግሥት ወክለን ስንንቀሳቀስ ስኬታማ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት አስተዋጽኦ አላቸው። እያንዳንዱ ስጦታ የመጣው ከአንድ መንፈስ ሲሆን የሚሰራውም ለዚያው መንፈስ ነው። በተጨማሪም፣ ስጦታዎቹ ቅኝ ግዛት በሆነች ምድር ውስጥ የመንግሥቱን አስተዳደር የመኖር ማረጋገጫ ለማሳየት የተሰጡና የንጉሡን ቸርነት እንዲሁም ለዜጎቹ በጎነት ያለውን የላቀ መሻት የሚገልጡ ናቸው። ሁሉም የሚሰጡት በእንዱ ገዢ አማካይነት ሲሆን፤ እርሱም እንደወደደ ለእያንዳንዱ ያከፋፍላቸዋል። ምናልባት አንድ ሰው የተሰጠውን ስጦታ ለአንድ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግልበት ሲሰጠው ይችላል ወይም ደግሞ ያንን ስጦታ መግለጡን እንዲቀጥልበት ሲያደርግ ይችላል። ገዢው ለሚሠራባቸው መንገዶች ንቁዎች ልንሆን ያስፈልጋል። እርሱ ያላደረገውን ነገር በግድ ልንሠራ ወይም እርሱ የሠራውን ነገር ልናጠፋ መሞከር አይገባንም።

## በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን መቀበል

ሥልጣናዊ ኃይል የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ ነው። የመንግሥቱ ዜጎች ሁሉ በምድር ላይ ድል ነሺዎች ሆነውና እንደ ንጉሥ እምባሳደርነታቸው ጥሪያቸውን በሚገባ ለመፈጸም ይችሉ ዘንድ ይህ ጥምቀት ያስፈልጋቸዋል። ቀደም ሲል እንዳየነው አዲስ ልደትን መቀበል የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን፤ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ደግሞ ሁለተኛው ደረጃ ነው። ያለመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፣ በምድር ልንኖርና ሰማያዊ መንግሥትን ልናገለግል የሚገባንን ያህል

> **የመንፈስ ስጦታዎች በገዢው ፈቃድና ውክልና የሚሰጡ ናቸው።**



ልናገለግል አልተዘጋጀንም ማለት ነው። ብዙ አማኞች ከንጉሡ ጋር ግንኙነት ማድረግ ጀምረዋል፤ ይሁን እንጂ እየተለማመዱ ያሉት የመንግሥቱን ሕይወት በሙላትና በብቃት ለመግለጥ አስፈላጊ ከሆነው ከንጉሡ ኃይል ገና ጥቂቱን ብቻ ነው።

መንፈሳዊ ኃይል፤ በገዢው ህልውና መጥለቅለቅና መሞላትን ለሚሻ ለማንኛውም አማኝ እንዲያው የተሰጠ ልዩ መብት ነው። አዲስ ልደትን በተቀበልን ጊዜ የንጉሡን ህጋዊ መብት ወይም ሥልጣን ተቀብለናል። ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጸፏል፤ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው"። ነገር ግን ኢየሱስ ልዩ ዓይነት ኃይልን ደግሞ እንደምንቀበል ተናግሯል፤ ይህም ሁሉን የሚያስችል፤ የሚፈነዳም ኃይል ነው። "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ"። እንደገናም በዚህ ስፍራ ኃይል ተብሎ ለተጠቀሰው ቃል የግሪክ ቋንቋ ትርጉም "ዱናሚስ" ወይም "ተአምራዊ ኃይል" የሚል ነው። ከዚህም ቃል ነው ዳይናማይት (ድማሚት) የሚለውን ቃል ያገኘነው።

የማስቻል ብቃቱ ጌታን አግኝተን በተለወጥንበት ጊዜ በጥቂቱ በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ ምልዐቱን ግን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በመንፈስ መመላለሳችንን ስንቀጥል እንቀበላለን። ዳግም በተወለድን ጊዜ የመንፈስ ቅዱስን ስብእና ተቀብለናል፤ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ደግሞ ኃይልን እንቀበላለን። ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የመንፈስ ቅዱስ ስብእና ያስፈልገናል፤ በምድር ላይ ድል ነሺዎች ሆነን እንኖር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ ያስፈልገናል።

በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የምንቀበለው ኃይል፣ በመጀመሪያ ደረጃ፤ ዓለምን ከንጉሥ - አባት ጋር ለማስታረቅ፤ የኢየሱስን ባህርይና ዓላማ መመስከር የምንችልበትን ብቃት ይሰጠናል። በሁለተኛ ደረጃ፤ ይህ ኃይል መቼም ይሁን በየትም ስፍራ ዝግጁ ሆኖ ከእኛ ጋር ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሣ ቀን ከመውረዱ በፊት፤ ደቀመዛሙርቱ በይሁዳ ከተሞች በሽተኞችን እንዲፈውሱ፣ አጋንንትን እንዲያወጡ ኢየሱስ በላካቸው ጊዜ የመንግሥቱን ኃይል ተለማምደዋል፤ ይሁን እንጂ ይህ ኃይል በቋሚነት በሕይወታቸው ውስጥ አልነበረም። ኢየሱስ ወደ አባቱ ስለተመለሰና መንፈሱን በሕይወታችን ካፈሰሰው በኋላ ግን መንፈሱ አሁንም በእኛ ውስጥ በቋሚነት ይኖራል።

ንጉሡ ልጅ፤ በገዢው አስተዳደር አማካይነት በእኛ እጆች ዓለምን ሊቤዥና ሊፈውስ እቅዱን ዘርግቷል። ይህንን ሚና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችለን ኃይል ደግሞ እጅግ መሠረታዊ ነው። ይሁን እንጂ የዚህን ኃይል ባህርዩንም ልንገነዘበው ያስፈልጋል። በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቁ ነገር ግን የተቀበሉትን ስጦታ በአግባቡ ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎችን አውቃለሁ። ቆም ብለው፣ ጥምቀቱን ወይም የጥምቀቱን ኃይል በእነርሱ

ውስጥ ሙሉ ሰሙሉ እንዳልተሰቀቀ ወይም ያስ አግባብ እንደሚጠቀሙበት ሊገነዘቡት ያስፈልጋቸዋል።

በመሆኑም ይህንን ምዕራፍ፤ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ምንነትና እንዴትስ መቀበል እንደሚቻል የሚገልጹ ጥቂት መሪ ሀሣቦችን በመስጠት እጠቀልለዋለሁ።

1. መንፈስ ቅዱስ፣ ገዢው፣ ልትቀበለው የተሰጠህ ስጦታ እንጂ በዋጋ የምትገዛው አይደለም።
2. የመንፈስን ጥምቀት ለመቀበል በምትችልበት አቋም ውስጥ ራስህን አስቀምጥ። አዲስ ልደት ወይም ድነት ቀዳሚዎቹ ነገሮች ናቸው። ደቀመዝሙሩ ጴጥሮስ እንዲህ ይላል፤ "ንስሃ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (ገና ወደ አዲስ ልደት ያልገባህ ከሆንክ በዚህ መጽሐፍ በምዕራፍ ስምንት መጨረሻ ላይ የሰፈረውን ሀሣብ አንብብ)።
3. ንጉሡ - አባት መንፈሱን እንዲያፈስልህ ጠይቀው፤ እናም ትክክለኛ ያልሆነ ነገር እቀበል ይሆን ብለህ ፈጽሞ አትፍራ። ኢየሱስ፣ "አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ማናችሁም ልጁ እንጀራ ቢለምነው እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፈንታ እባብ ይሰጠዋልን? ወይስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ፤ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፤ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን አይሰጣቸው!" ንጉሡ - አባታችን መንፈሱን ለሚለምኑት ልጆቹ ሌላ ያልተገባ ነገር እንደማይሰጥ ልንተማመንበት እንችላለን።
4. በልሣን ልትናገር ይጠበቅብሃል። መንፈስ ቅዱስ ቃሎቹን ይሰጥሃል፤ ንግግሩን የምታደርገው ግን አንተ ነህ። አንዳንድ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ምላሣቸውን "ወስዶ" እስኪያናግራቸው ድረስ ይጠብቃሉ። ይሁን እንጂ የምናደርገው ማንኛውም ልምምድ በመስኮትና በሰው መካከል ባለ ትብብር የሚከናወን ነው። ለአዕምሮህ ወይም ለቀደመ ልምምድህ ሳይሆን ለመንፈስህ ስፍራ ልቀቅለት።
5. በመንፈስ መመላለሳችንን እንቀጥል። በመንፈስ እንደተሞላን እንቆያለን። በየዕለቱ ገዢውን ስንጠማ፣ ምሪቱን ስንታዘዝና ራሳችንን ስናቀርብ፤ ንጉሡ - አባት በዓለም ሊሠራ ላለው ሥራ ሊጠቀምብን ዝግጁዎች እንሆናለን። መንፈሱ የሚሠራው በእግዚአብሔር ቃል አማካይነት ስለሆነ፤ የንጉሡን ሀሣብና ልብ ማወቅ እንድንችል፤ እንዲሁም ፈቃዱን፣ ፈቃዱንም ከሚያደርገው ኃይሉ ጋር በማቀናጀት



ዝግጁዎች እንሆን ዘንድ ያለ ማቋረጥ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ አለብን።

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማለት ሰማያዊ የሆነው ኃይል በአንተ ውስጥና በአንተም በኩል መለቀቅ ማለት ነው። በልሣን መጸለይ ማለት በአንተ፣ በመንፈስ ቅዱስና በአብ መካከል ያለ ውስጣዊና ግላዊ ግንኙነት ማለት ነው። በመሆኑም በሕይወትህ ውስጥ የእግዚአብሔርን ኃይል መለቀቅ ስትለማመድና ሰማያዊ ስጦታ በሆነው ቋንቋ ወደ አብ ስትጸልይ፤ በስሜት ውስጥ ልትገባ ትችላለህ። ይህ ስሜት እንዲያው ስሜት ስለሆነ ብቻ የሚመጣ አይደለም፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ኃይልና እውነት ጋር የተያያዘ ነው። ምንም እንኳን ልምምዱ ስሜታዊ ሊሆን ቢችልም፤ እግዚአብሔር ስሜታችንን በአግባቡ እንድንገታው ይጠብቅብናል። ጳውሎስ እንዲህ ሲል አስተምሮናል፤ "የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ"። በዚህ መንገድ፣ በእግዚአብሔር እንጂ በራሳችን እቅድና መሻት አንቀሳቀስም።

በመንግሥቱ ኃይል አማካይነት በምድር ላይ ባህርዩንና ፈቃዱን በአግባቡ ስትገልጹ እግዚአብሔር ይባርካችሁ!

# ምዕራፍ ዐሥራ ዐራት

## ለመላው ዓለም ገዢው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

### *ለዓለማችንና ለችግሮቿ ውጤታማና አግባብ ያለው እርዳታ ከራሷ ከዓለም ሊመጣ አይችልም።*

የምዕተ ዓመቱ ለዓት መቁጠሪያ እጀታ፣ መሬት በተባለችው ፕላኔት ውስጥ እየተከናወነ ያለውን ታሪክ እየመዘነና እየዘገበ በመራመድ፤ ገና በውል ወዳላወቅነው ወደ ሃያ አንደኛ ክፍለ ዘመን ጠሊቅ ውሃ ሲመራን፤ በዓለማችንና በትውልዱም ያለው ማንኛውም ነገር መውደቅ የጀመረ ይመስላል። ለደህንነታችን ስንል በረዥም ዘመናት ውስጥ የመሠረትናቸው ተቋሞቻችን ከመሠረታቸው ተናውጠዋል።

የእሸባሪነት ዓለም ዓቀፋዊ እየሆነ መምጣት፣ የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና ዋስትና ማጣት፣ የዘይትና የነዳጅ ዋጋ መናር፣ የኒኩሊየር መሣሪያዎች ሥጋት እንደገና መፈጠር፤ የጎሣ፣ የባህል፣ የሃይማኖትና የዘር ግጭቶች፤ የፖለቲካና የዲፕሎማሲያዊ ደርድሮች፣ የሞራልና የማህበራዊ ሕይወት ምስቅልቅሎች፣ የሰው ልጆች ስጋት በከፍተኛ ፍጥነት መጨመር፣ በምድር ባሉ ነዋሪዎች መካከል የተስፋ ቢስነት መንፈስ የተለመዱ ነገሮች ሆነዋል።

የሰው ልጅ ለውድቀቱ መሠረታዊ ምክንያት በሆነው ነገር ላይ ትኩረት ባለመስጠት፤ በራሱ ጥረት ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በአዕምሯዊ፤ ሃይማኖታዊ፣ ሳይንሳዊ፣ ፍልስፍናዊና ፖለቲካዊ ሥርዓቶች አማካይነት ለመቀየር በሚያደርገው ጥረት ፍርሃቱ እየተባባለ መጥቷል። በዚህ ረገድ ምናልባትም ለሰው ልጆች ውድቀት እንደ ተጨባጭ ማስረጃ ሆነው ሊቀርቡ የሚችሉት፤ የሰው ልጅ የመሠረታቸው ቀደምት የሆኑ መንግሥታት፣ ዓለም ተቋማትና ህብረቶች፤ ለምሣሌም እንደ የተባበሩት መንግሥታት፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም፣ የዓለም ባንክ፣ የዓለም ሠራተኞች ማህበር እና የቡድን ስምንት አገሮች ተቋም የተሰኙት ተቋማት ያደረጓቸው ጥረቶች መክነው መቅረታቸው ነው።

እውነተኞች ከሆንን፤ ለዓለማችንና ለችግሮቿ ውጤታማና አግባብ ያለው እርዳታ ከራሷ ከዓለም የሚመነጭ አይደለም ብለን ብንደመድም ምናልባትም ትክክለኞች እንሆናለን። ከሌላኛው ዓለም እርዳታ ያስፈልገናል። የሰው ልጆች ራሳቸው ያመነጩትን ችግር ራሳቸው



አይፈቱትም፤ ሊፈቱትም አይችሉም የሚል እምነትና ልምምድ አለኝ። የሰው ልጅ እርዳታን ፍለጋ አይኖቹን ወደ ሌላ ዓለም ማንሣት አለበት። በዚህ እውነት ላይ ያለኝ እምነት ነው ለዚህ መጽሐፍ መጀመርና በውስጡም ላቀፈው ሀሣብ ምክንያት የሆነኝ። ተፈጥሯዊ የሆነችው ዓለማችን እስተማማኝ፣ ተግባራዊና ውጤታማ የሆነ እርዳታ ያስፈልጋታል። አሁን ያሉት አስተዳደራዊ ተቋሞቻችን እጅግ ከፍ ባለና በላቀ አስተዳደር ሊገዙ ያስፈልጋቸዋል።

> ሰማያዊ መንግሥት ከመታወቅ ያለፈ በምድር ላይ ካለ ከየትኛውም መንግሥት በላጭና ለምንኖርባትም ዓለም በጣም በአስቸኳይ አስፈላጊ ነው።

ስለዚህም ነው፤ መላው ዓለም - እያንዳንዱ ሰው በነጠላና መላው ዓለም በጋራ - ለገዢው መመለስ እውቅና ሊሰጥና ሊቀበል የሚያስፈልገው። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ሰማያዊው መንግሥት እንደገና በምድር ላይ የሚመለሰው ለኛ በገዢው በኩል በተሰጠን በንጉሡ ሕይወትና ኃይል አማካይነት ብቻ ነው። ይህ መንግሥት ከመታወቅ ያለፈ፣ በምድር ላይ ካለ ከየትኛውም መንግሥት ይልቅ ታላቅና ኃያልም ነው። እንደገናም አሁን እኛ ለምንኖርባት ዓለም በጣም አስቸኳይ በሆነ ሁኔታ የሚያስፈልጋት ይኸው መንግሥት ነው።

የአገራት ጥሩነት በውስጣቸው እንዳቀፉት ማኅበረሰብ ዓይነት ነው፤ የማኅበረሰብም ጥሩነት መለኪያው በውስጡ ያቀፈው ቤተሰብ ሁኔታ ነው። የቤተሰብም ጥሩነት በውስጡ ያሉት ግለሰቦች ጥሩነት ያህል ነው። በመሆኑም የአንድ አገር ጥራት የሚለካው በውስጡ ባሉት ህዝቦቹ ጥራት ነው። ይህ እውነት በተለይ የሚሠራውና ወሣኝ የሚሆነው የአገራትን መሪዎች አስመልክቶ ነው። አብዛኛውን ጊዜ መሪዎች ሲራመዱ አገር (ሕዝብ) ይራመዳል። የመሪዎቻችን እሴቶች፣ ደረጃዎችና ስነምግባራዊ አመለካከቶች አብዛኛውን ጊዜ የህዝቦቻችንን ቆራጥነትና ህግንም የሚወስኑ ይሆናሉ፤ እናም በህዝቡ የሕይወት ዘይቤና ባህል ላይ ተጽእኖ ያመጣሉ።

በመሆኑም፤ የአገራችን ህዝቦች፣ መሪዎች አድርገን በእኛ ላይ የምንሾማቸው ግለሰቦችና በማህበረሰባችን ውስጥ ያሉ ተቋማት፤ ጠንካራ አቋም፣ እምነት፣ ስነምግባር፣ እሴት እና ደረጃ የሌላቸው ከሆኑ፤ የራሳችን ብልሹ ባህርይ ሰለባዎች ሆነን እንደምንቀጥል ማወቁ መሠረታዊ ወሳኝ ነው።

ስለዚህም ነው፤ ፈጣሪ በምድር ላይ ነዋሪ ሆኑ ሰዎችን ሕይወት ሁሉ፤ በራሱ በፈጣሪው መንፈስ - በመንፈስ ቅዱስ - በሰማያት ገዢ መሞላት የሚያስፈልገው አድርጎ ያቀደው፣ ያዘጋጀውም። በዚህ እሳቤ፣ ሀገራዊ ማህበረሰቦች እና በምድር ላይ ያለ ዓለም ዓቀፋዊ የሆነው ሕይወት

ሁሉ በገዢው በመንፈስ ቅዱስ በኩልና በእርሱም ውስጥ እንዲኖሩ ነበር የታቀዱት:: የመንፈስ ቅዱስ ስብእናና ሚና ሃይማኖታዊ የሆነ ጉዳይ አይደለም፤ ይልቁንም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ትኩረት ያለው ነው:: በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ብሔራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳይ በመሆኑ በዚህ መልኩ ሊታይና ሊቀርብም ይገባዋል::

## ግለሰባዊ ዓላማና ስኬታማነት

እንደ ግለሰብ፤ እያንዳንዳችን ለእውነተኛ ሕይወት፣ ዓላማና ስኬታማነት ገዢውን ልንፈልገው ይገባል:: ገና ከመነሻው በመጀመሪያው የሰው ልጅ ሕይወትን ያስጀመረው የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ በተለያዩ በሶስት መንገዶች ነበር የሠራው (1) በማይታየው የሰው መንፈስ፣ በእግዚአብሔር መልክ በተሠራው፤ (2) በሰው ነፍስ ውስጥ - አዕምሮ፣ ፈቃድ እና ስሜት (ይህም በጥቅሉ የሰው አሣብ ተብሎ የሚጠራው ነው)፤ (3) በሰው ፍጥረታዊ አካል፣ የመንፈሱና የነፍሱ ህያው መያዣ በሆነው:: የአዳም ነፍስና አካል በምድር ያለውን ከባቢ እንዲገነዘብ ባስቻለው ጊዜ፤ በውስጡ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ለመንፈሱ ደግሞ፤ ስለፈጣሪው ንጉሥ እውቀት እንዲኖረውና ከሰማያዊው አስተዳደር ጋር በቀጥታ እንዲገናኝ ችሎታን ሰጠው::

> ንጉሡ፤ ገዢውን እንደገና
> እንዲቀበለውና ከህመም፣
> ከሃዘንና ከሞት
> እንዲላቀቅ ይፈልጋል

የሰው ልጆች ወደዚህ ሕይወትና ሙላት እንደገና ሊመለሱ ያስፈልጋቸዋል:: የተፈጠርነው የእግዚአብሔርን ባህርይ ልንገልጽ ነው፤ በመሆኑም በውስጣችን በሚኖረው በመንፈሱ አማካይነት በእውነቱ የርሱ ባሕርይ ካለን ብቻ ልንገናኘውና ባሕርዩን ልናንፀባርቅ እንችላለን::

ስለዚህ የግለሰባዊ ሕይወታችን ትርጉም - ማለትም የተፈጠርንበትን ዓላማ መኖርና ሙሉ እምቅ ችሎታችንን መለማመድ - ሙሉ ለሙሉ ገዢውን በመቀበላችን ላይ የተመሠረተ ነው::

## የነገሥታትና የካህናት የዓለም ማህበረሰብ

ምንም እንኳን ንጉሣችን የሚገናኘን በየግላችን ቢሆንም፤ የመንግሥቱ ዜጎች ተገልለውና ተነጥለው ይኖሩ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ አይደለም:: የእርሱ እቅድ በምድር ላይ የሚነግሥ የነገሥታትና የካህናት ማህበረሰብ ነው:: ለሁሉም የሰው ዘር ሕይወት ገዢው ቁልፍ ነው:: በመሆኑም የዓለም ማህበረሰብ አስቀድሞ ወደ ተፈጠረበት የሕይወት ዓላማ እንዲገባ ከተፈለገ የግድ በገዢው ሊመራ ያስፈልገዋል::



ዓለም በጥቅሉ፤ የገዢውን ህልውናና በጎ ተጽእኖ ተቃውማለች:: ስለዚህም ነው በምድር ላይ ጦርነትን፣ ማህበራዊ ቀውሶችን የምንቀምሰው::

ዓለም፣ ገዢውን እንደገና እንድትቀበል ንጉሡ ይፈልጋል። ምድር በዙሪያዋ ከከበባት ከስቃይ፣ ከሀዘን፣ ከውድመት እና ከሞት እንድትገላገል ይፈልጋል:: የሰማያዊው አስተዳደር እንደገና መመስረት፤ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በምድር ላይ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ እንዲያሳድሩና እንዲቆጣጠሩ ችሎታቸውን ይመልሳል::

የነገሥታትና የካህናት ማህበረሰብ ለትክክለኛ ዓላማ ተባብሮ ቢሠራ (ይህም ማለት ንጉሡን ማክበርና ባሕርዩን መግለጽ ማለት ነው)፣ እኛም በእውነተኛ ህብረት፤ በመንግሥቱ ባህርይ በምድር ላይ በጎ ተጽእኖን ለማሳደር ታላቅ ኃይል ይኖረናል::

በመሆኑም እንድንበረታታና፣

- ✓ ማህበራዊ መረጋጋትን::
- ✓ የኢኮኖሚ እድገትን::
- ✓ ትክክለኛ ከባቢን::
- ✓ የትምህርት እድገትን::
- ✓ አካላዊ ጤንነትና ሙሉ አካልን::
- ✓ ሳይንሳዊ የፈጠራ ግኝቶችን::
- ✓ ፖለቲካዊ ታማኝነትን::
- ✓ አስተዳደራዊ ፍትህን::
- ✓ ባህላዊ መግባባቶችን እንድንፈጥር ያስችለናል::

## መልካም መሪ

መጽናናትን ከሚሰጥ፣ ከፍተኛ የሆነውን የግልና የማህበር ችሎታ በመጠቀም በሕይወታቸው ስኬታሞች እንዲሆኑ ከሚያስችል አስተዳደር ጋር መሥራት የማይፈልግ ከቶ ማነው? ነቢዩ ኢሣያስ ይህንን በገዢው አማካይነት በንጉሡ ልጅ አገዛዝ ስር የሆነውን ሰማያዊ አስተዳደር እንደዚህ ይገልጸዋል፤

> "ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለሙ ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግስቱም ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም:: የእግዚአብሔር ቅንነት ይህንን ያደርጋል::" ሁሉ በሁሉ የሆነ

እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ለሕዝቡ ካለው ጠንካራ ፍቅሩ የተነሣ ነው::

በተጨማሪም፤ ይህ አገዛዝ እውነተኛ አገዛዝ ነው የሚባለው ንጉሡ ለዜጎቹ ካለው ታላቅ ፍቅርና በሕይወታቸውም ከፍ ያለ መልካም ነገር እንዲሆንላቸው ካለው መሻቱ የተነሣ ብቻ ነው::

ይሁን እንጂ፤ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሌላ ዓለምን ለመቆጣጠር የሚተጋ፣ ረዳቶችም ያሉት ክፉ አለቃ ደግሞ በእርግጥ መኖሩን ይነግረናል::

- ✓ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደሆነው በአየር ላይ ስልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ በፊት ተመላለሳችሁባቸው::
- ✓ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር፤ ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ::
- ✓ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ::

የዚህ ጨለማ ዓለም አለቃ ሉሲፈር ወይም ሰይጣን የተባለው ነው፤ እርሱም በሰማይ የአምልኮ መሪ የነበረ ከሃዲ ጄኔራል፣ በዓመጹም ምክንያት የወደቀ ነው:: ይሄው አለቃ ነው ገና ከፍጥረታችን መጀመሪያ ጀምሮ በሰው ልጅ ፍጥረት ውስጥ መልካም የነበረውን ነገር በማጥቃት ያበላሸው:: አገዛዙ ቀጣይነት እንዲኖረው ስለሚፈልግ በዓለም ውስጥ ያለው ሀዘንና ጨለማ እንዲቀጥል ይወዳል:: መላውን የዓለም ህዝብ በዚህ አስከፊ አገዛዙ ሥር አንድ ለማድረግም ይፈልጋል፤ ዓላማውም ፈጽሞ ከእጁ መዳፍ ነፃ እንዳይወጡ ለማድረግ ነው::

ሰይጣን በምድር ላይ የነበረው ኃይል መሰበር ስለሚገባውና በጨለማው አገዛዝ ምክንያት በነቀዘው ዓለም ውስጥ የነበርነው እኛ ወደ ሰማያዊው መንግሥት ብርሃን እንድንፈልስ ስለሚያስፈልግ ንጉሡ ልጅ መምጣት የተገባውም ለዚህ ነው:: ነቢዩ ኢሣያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤ "በጨለማ የተቀመጠው ህዝብ ብርሃን አየ፤ በሞት አገር ጥላ የተቀመጡትም ብርሃን ወጣላቸው::"

ሰይጣን በጨለማና በሞት ሲመሰል፣ ንጉሡ - ልጅ፣ ኢየሱስ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብርሃንና በሕይወት ተገልጿል፤

"ብርሃኑም (እርሱ) በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል፤ እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል"



"ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ሁሉም በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡ በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች:: ብርሃንም በጨለማ ይበራል፤ ጨለማም አላሸነፈውም:: "

ኢየሱስም ስለራሱ የተናገረው በዚህ መንገድ ነበር፤

"እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም"

"በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ አይኖርም እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ"

ኢየሱስ ለሥነ - መለኮት ምሁር ለሆነው ለሐዋርያ ጳውሎስ እንዲህ አለው፤

"የኃጢአትንም ስርየት በእኔም በማመን በተቀደሱት መካከል ርስትን ያገኙ ዘንድ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከሰይጣንም ሥልጣን ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ዓይናቸውን ትከፍት ዘንድ፣ እልክሃለሁ::"

ጳውሎስ ለ1ኛው ክፍለ ዘመን የመንግሥቱ አማኞች እንዲህ አስተማረ፤

"ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፣ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤ የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ፣ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ::"

"እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን፤ በቤዛነቱንም እርሱንም የኃጢአትን ሥርየት ወዳገኘንበት ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግሥት አፈለሰን:: "

> ንጉሡ ልጅ የመጣው ከጨለማ ወደ ሰማያዊው መንግስት ብርሃን ሲያፈልሰን ነው

የዓለም ህዝቦች ሁሉ በአስቸኳይ የመንግሥቱ ብርሃንና ሕይወት ያስፈልጋቸዋል፤ ይህም የሚመጣው በገዢው በኩል ከንጉሡ ልጅ ብቻ ነው:: በመንፈስ ቅዱስ መመለስ አማካይነት በምድር ላይ የሰማያዊው መንግሥት መኖር (መገኘት) ማለት የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት፣ እናም የኢየሱስ መልዕክት መኖር ማለት ነው:: የሰው ልጅ ሁሉ ታሪክ - እናም የሁላችንም - ማምለጥ በማንችልበት ሁኔታ ከዚህ መንግሥት ጋር የተሣሰረ ነው:: በገዢው ምሪት አማካይነት በምድር ላይ የመንግሥቱን አገዛዝ መለማመድ በወል የተሰጠን ዓላማና ጥሪያችንም ነው::

ራሳችንን ለገዢው ህልውና አሳልፈን በመስጠት በሕይወታችን እንዲሠራ ስንፈቅድ፤ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት እናስፋፋለን። ያን ጊዜ በማናቸውም ሕይወት ገጽታዎች፤ ለውጥ ይከተላል፤ በሁሉም አገራት ህዝቦችና ብሔሮች፣ በየትኛውም ዘር፣ በምስራቅና በምዕራብ፣ በማንኛውም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ውስጥ ለውጥ መምጣት ይጀምራል። መምህራን፣ አርቲስቶች፣ የሂሳብ ሠራተኞች፣ የጤና ባለሙያዎች፣ ገበሬዎች፣ ሳይንቲስቶች፣ ኢኮኖሚስቶች፣ ልብስ ሰፊዎች፣ የመንግሥት መሪዎች፣ የቤት እመቤቶች እንደ ሰማያዊው መንግሥት ፈቃድ ይለወጣሉ፤ ውጤቱም ሕይወት እንጂ ግራመጋባት፣ ጭንቀትና ሞት አይሆንም።

መንፈሱ ቃሉን በሙላት በመግለጽ ለዓለም ሕይወትን ይሰጣል። በማንኛውም መልኩ በመንፈሱ በኩል ወደ ሰዎች የሚመጣ ተጽእኖ በመጨረሻው ሕይወትን የሚያመጣ ነው፤ ይህም ወደ መላው አገራት የሚደርስና የዓለም ማህበረሰብን የሚያነሳሳ ነው።

> መንፈሱ ቃሉን በሙላት በመግለጽ ለዓለም ሕይወትን ይሰጣል

ለምሳሌ ያህል፤ በአንድ አገር ውስጥ ያሉ ዳኞች ሁሉ በሰማያዊው ገዢ አመራር ለጭነት ሥር ቢሆኑና አስተሳሰባቸውም በመንግሥቱ ፍልስፍና ቢወረስ፤ በሚሰጡት ውሳኔ ምንነት ልትደነቅ አያስፈልግህም ወይም ደግሞ ፍትህ አልባ በሆነ ሕጋዊ አሠራር አትንገላታም። በመንፈስ ቁጥጥር ሥር የዋለ ባህል ሕይወትን የሚንከባከብና የሚጠብቅ ባህል ነው የሚሆነው።

"ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፤ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው።"

## የምድር ሙሉ በሙሉ ወደ መንግሥቱ መለወጥ

ዓለም በመጨረሻው ሙሉ ለሙሉ ወደ ንጉሡ መልክና ምሳሌ ስመለወጥ መንዣን ትቀጥላለች። የዚህ እቅድ የፍጻሜው ጫፍ የአዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መፈጠር ነው። በውጤቱም በባሕርይ ሰማይና ምድር አንድ ይሆናሉ፤ ይህም ማለት በመካከላቸው መሠረታዊ የሆነ ልዮነት አይኖርም፤ ማለት ነው። እግዚአብሔር ራሱ በሕዝቡ መካከል ይኖራል።

ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ የምድርን ወደ ሰማያዊው መንግሥት ባህርይ፤ የአመለካከት ቅኝትና እሴት ሙሉ በሙሉ የመለወጥ ሂደት እንዲህ ሲል ገልጿል። ከጥቅሶቹ ቀጥሎ በቅንፍ ውስጥ ያስቀመጥኳቸው ቃላት ለመንግሥቱ ሕይወት አንድምታዎች እንደሆኑ ያየኋቸውን ሀሣቦች ገልጫለሁ።



"አዲስን ሰማይና አዲስ **ምድርንም** አየሁ፤ **ፊተኛው** ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና" (**ምድር ሙሉ ለሙሉ** ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ተስማምታለች፤ **የጨለማው ግዛት** ህልውና (ዱካ) የለበትም). . .

"ቅድስቲቱንም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም **ለባሏ እንደ** ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር **ዘንድ** ስትወርድ አየሁ።" (የመንግሥቱ ዜጎች ሙሉ ለሙሉ **ንጹህ፣** የተለዩና አንድ የሆኑ (የተዋሃዱ) ናቸው፤ ከእግዚአብሔር ባህርይ ጋር አንድ ሆነዋል፤ እርስ በእርሳቸውም ስምምነት ያላቸው ናቸው)

"ታላቅም ድምጽ ከሰማይ፤ እነሆ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል እነርሱም ህዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል" (ገዢው በንጉሡ ህዝብ ውስጥ መኖሩን ይቀጥላል፤ እናም ንጉሡን ከሚወዳቸው ልጆቹ የሚለያቸው አንዳች ነገር አይኖርም)

"እንባዎችንም ሁሉ ከአይኖቻቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ሃዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ስርዓት አልፏልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ። በዙፋንም የተቀመጠው፤ እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ!" (የጨለማው መንግሥት ሙሉ ለሙሉ ወድሟል፤ የሕይወትና የብርሃን መንግሥት ሙሉ በሙሉ በምድር ላይ ነግሷል)

> መንፈስ ቅዱስ ለዓለም ቁልፍ ነው፤ በምድር ከፍተኛው ገዢ እርሱ ነው።

የአዲስ ሰማይና የአዲስ ምድር መፈጠር ንጉሡ ለገዢው መምጣት ያዘጋጀው እቅድ የመጨረሻው መጨረሻ ሲሆን ይህም ከመጀመሪያ በሃሣቡ የነበረ እቅድ ነው። በምድር የሚኖሩ ሰዎች የመንግሥቱን ሕይወት በሙላት የሚኖሩ፤ እውነተኛ የሆኑ የነገሥታትና የካህናት ማህበረሰብ ይሆናሉ።

## የመንግሥቱ ዜጎች

ደቀመዝሙሩ ጴጥሮስ በእርሱ ዘመን ለነበሩ የመንግሥቱ ዜጎች የሚከተለውን አዋጅ ጽፏል፤ አዋጁ በዚህ ዘመን ላለን ለእኛም የሚሠራ ነው፤

"እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፤ የንጉሥ ካህናት፤ ቅዱስ ህዝብ፤ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ:: እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተም ምህረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም፤ አሁን ግን ምህረትን አግኝታችኋል::"

መንፈስ ቅዱስ ለዓለም ቁልፍ ነው፤ በምድርም ላይ ትልቁ ስብእና (ሰውነት) እርሱ ነው፤ ምክንያቱም የሰማዩን መንግሥት ህልውናና ኃይል ወደ እኛ የሚያመጣው እርሱ ነው:: ከፈጣሪ ንጉሥህ ጋር ታርቀህ ከሆነ፣ ገዢውን ወደ ሕይወትህ ተቀበል እናም ልትሆን አስቀድሞ እንደተወሰነልህ እንደ ንጉሣዊ የመንግሥት ዜጋ ኑር!



## መልዕክት ለሦስተኛው ዓለም

በሦስተኛው ዓለም ያሉ አገራት፤ በምድር ላይ ካሉ ማናቸውም አገራት ይልቅ አንዳንድ እጅግ ፈታኝ የሆኑ ችግሮችን እየተጋፈጡ ነው:: እነርሱ በተለይ ለዘመናት ከተጫነባቸው ድህነት፣ በሽታ፣ ወረርሽኝና የየአገራቱን ሀብት ጠራርገው ለራሣቸው ለማግበስበስ በእምባገነንነት በሚገዙአቸው መሪዎቻቸው ምክንያት ከሚደርስባቸው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጭቆና ነፃ መሆን ያስፈልጋቸዋል:: በዚህ ምክንያት፣ ምናልባት በሦስተኛው ዓለም ያሉ ህዝቦች የሰማያዊው መንግሥት በጎ ተጽእኖ በምድራቸው ላይ እንደማይሠራ ሊሰማቸው ይችል ይሆናል::

የሦስተኛውን ዓለም አገራት ችግሮችና ተግዳሮቶችን በፖለቲካ፣ ህጋዊነትን በማስፈንና በሰብአዊ እርዳታዎች አማካይነት ለመፍታት ተሞክሯል:: እነዚህ ዘዴዎች በትክክል አስተዋፅኦ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን መልካም ሰዎችና ፕሮግራሞች አሏቸው፤ በአሁኑ ጊዜም ችግሮችን ለመቀነስ የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ ይገኛሉ:: ለኃይለኛና ዘላቂ መፍትሄ፣ ግን፤ ትኩረት እያደረግን ያለነው በተሣሣቱ ነገሮች ላይ ነው::

የመስፈሪያ ልክ የሌለው አንድ የላቀ ነገር ያስፈልገናል፤ ይህንንም ነገር እኔ፤ "ብሔራዊ ጥምቀት" ወይም በሦስተኛው ዓለም ህዝቦች ሕይወት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ወረራ ብዬ ነው የምጠራው:: እያንዳንዱ የሦስተኛው ዓለም አገር፤ ሥርዓትና መረጋጋት ወደ ህዝቡና ወደ መሪዎቹ እንዲመጣ ከፈለገ፤ አገር ዓቀፍ በሆነ መንገድ የሰማዩን መንግሥት ገዢ ሊገናኝ መውጣት አለበት::

ይህ ጥምቀት ከሁሉቱ ከፍልስፍናና ከኃይል አንዱ ነው:: ተግባራዊ የሚሆነውም በአገራቱ ካሉ መሪዎች እስከ ልጆች ድረስ መንፈስ ቅዱስ ወደ መላው ህዝብ ዘልቆ በመግባት ነው:: ቀደም ሲል እንዳየነው፤ እውነተኛ የሆነ መንግሥታዊ ፍልስፍና እንዲኖር፣ የሕይወታችንን አካሄድ ከሰማያዊው መንግሥት ንጉሥ አመራር ጋር ማስማማትና መላውን አመሰካከታችንን ከእርሱ የአመሰካከት ቅኝት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን መለወጥ ያስፈልገናል::

አንድ አገር እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ለመለማመድ፤ በርግጥ ገዢው በህዝቡ ውስጥ ለመኖር መምጣት አለበት:: ፈጣሪ ለሰው ልጆች የራሱን ባህርይ ከሰጣቸው በኋላ፣ እርሱ (1) በተለይ ለእነርሱ አስቦ በፈጠረውና ባዘጋጀው ግዝፈ ዓለም ላይ መሥራት እንዲችሉ ፍጥረታዊ አካል ሰጣቸው፣ እና (2) የራሱን መንፈስ እስትንፋስ በእነርሱ ውስጥ እፍ በማለት በምድር ላይ ጥሪያቸውን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ ሕይወትና ኃይልን ሰጣቸው::

በሦስተኛው ዓለም ወይም በማደግ ላይ ያሉ ተብለው በተፈረጁ አገራት ውስጥ አራት ቢሊዮን ህዝብ ያህል ይኖራል። የሦስተኛው ዓለም አገራት በዚህ ዓለም ውስጥ የተለየ ጥሪ አላቸው፤ ይሁን እንጂ ሙሉ ኃይላቸውን መጠቀም የሚችሉት የሰማያዊውን ገዢ ኃይልና የአመለካከት ቅኝት ከተቀበሉ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም ከሰማያዊው መንግሥት ጋር ሊያገናኛቸው የሚችለው ገዢው ነው።

የሦስተኛውን ዓለም ፍላጎት ለመመለስና ለማርካት አስፈላጊው ሥልጣን፣ ችሎታና እቅድ ያለው ፈጣሪ አምላክ ብቻ ሲሆን፤ ይህንንም የሚተገብረው በምድር ላይ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በሚሠራው ሥራ ነው። በማደግ ላይ ላሉ አገራት እርሱ እንዳለው ፍቅርና ትኩረት ያለው በምድር ላይ ማንም የለውም። በመሆኑም ማህበረሰብህንና አገርህን የሰማያዊ መንግሥት ምሣሌ ወደሚሆን ማህበረሰብና አገር ሊለውጥ ስለሚፈልግ - እንደ ሦስተኛው ዓለም ነዋሪነትህ፣ በመዝገቡ ውስጥ ሊያሰፍርህ ይሻል። በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና እርቅን ብታደርግ፤ ከዚያ በኋላ የሦስተኛው ዓለም አገራት አባል ብቻ አትሆንም፤ ይልቁንም በግዝፈ ዓለሙ ሁሉ ውስጥ እጅግ የበለጠገው፤ ኃያል የሆነው መንግሥት፤ ከሙሉ መብቱና፣ ጥቅሞቹ ጭምር ዜጋ ትሆናለህ።

ምድራዊ የሆኑ መሪዎች ግራ ሊያጋቡን ወይም ሊጨቁኑን ይችላሉ፤ ወይም ደግሞ እጅግ የቅርብ ናቸው የምንላቸውም ጓደኞቻችን የምንፈልገውን መልስ ላይሰጡን ይችላሉ። ይሁን እንጂ ስለእኛ ተግቶ በእኛው ውስጥ ሆኖ በሚሠራው፣ በግልና በአገራዊ ሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ችግሮች አሸንፈን ለመውጣት የሚያስችሉንን መለኮታዊ ስጦታዎችና ብቃቶች በሚሰጠን በሰማያዊው ገዢ ላይ ልንደገፍ እንችላለን። ከንጉሡ መንፈስ እርዳታን፣ ብርታትንና የጥያቄዎቻችንን መልስ ልንቀበል እንችላለን።

ማናቸውም በሕይወትህ ውስጥ ከቁጥጥር ውጭ የሚመስሉ ነገሮች ለምሳሌም፤ ፍጻሜህ በማን እጅና ቁጥጥር ሥር እንደሆነ፤ ገቢህን እንዴት ማሳደግ ወይም አዲስ ንግድን እንዴት እንደምትጀምር፤ አስተማማኝ የሆነ የጤና እንክብካቤ እንዴት እንደምታገኝ ወይም ደግሞ ለአንተና ለቤተሰብህ የሚሆነውን በቀጣይነት የሚያስፈልግህን ምግብ እንኳን ከየት እንደምታገኝ ለገዢው አሳልፈህ ልትሰጥ ትችላለህ። ሕይወትህን ሁሉ ርኅሩኅ በሆነው፣ ፍላጎትህ በሚገባው፣ ደህንነትህን በሚሻና ስኬታማ እንድትሆን በሚመኝልህ ፈጣሪ ፍጹማዊ አገዛዝ ሥር ማስቀመጥ ትችላለህ።

በሦስተኛው ዓለም ያሉ አገሮች ከፍ ያለ እድገት እንዲያመጡና በዓለም ማህበረሰብ ውስጥ ለዘለቄታው ለሚኖራቸው እጣ፤ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ከፈጣሪው ንጉሥ ጋር ህብረታቸውንና ግንኙነታቸውን ማደስ እጅግ ወሳኙ ነገር ነው። የሦስተኛው ዓለም ወይም በማደግ ላይ



ያሉ አገራት ከነቀዘ ባህል፣ ከድህነትና ከተስፋ ቢስነት ነጻ ሊሆኑ ያስፈልጋቸዋል። ገዢው በአገራቸው ውስጥ የሚኖረውን የሁሉንም ሰው ሕይወት ከፍ ወዳለ ደረጃ እንዲያሸጋግርና ብሔራዊ ሀብቶቻቸውንና ጥሩ ቁሶቻቸውን ለመላው ህዝባቸው መልካም ጥቅም እንዴት ማግኘት እንደሚገባቸው የሰማያዊው መንግሥት ጥበብ እንዲሰጣቸው ሊፈቅዱለት ያስፈልጋል።

ለሦስተኛው ዓለም ወይም በማደግ ላይ ያሉ ለተባሉት አገራት፤ ለትውልዳቸውና ለመላው ህዝባቸው ያለኝ ፀሎትና መልካም ምኞት፤ መንፈስ ቅዱስን አስቀድመው ወደ ግል ሕይወታቸው በመቀጠልም ወደ ህዝባዊ ባህላቸው "እንኳን ደህናመጣህ" በማለት እንዲቀበሉት ነው፣ እርሱ ብቸኛ ኃያልና ከፍ ያለ ርኅሩህ ነው፣ እርሱ ብቻ። የአገሮቻቸውን እሴቶች፣ ስነምግባሮች፣ ደረጃዎች፣ ማህበራዊ ንቃተህሊናና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎቻቸውን የሚቀይር እንደሆነና ከሰማይ የመጣ ገዢ እንደሆነ አውቀው እንዲቀበሉትና እንዲፈቅዱለት ነው።

# የጥቅስ ማውጫ


**መግቢያ**

ገጽ 12 “ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ...” (ሮሜ 1፥20)
ገጽ 12 “የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ...” (2ቆሮ 4፥18)
ገጽ 12 “መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለም” (ዮሐ 18፥36)
ገጽ 14 “በእርሱ ሁሉ ተፈጥረዋል ...” (ቆላ 1፥16)

**ስመነሻ**

ገጽ 9 “በመጀመሪያውም ቃል ነበረ ...” (ዮሐ 1፥1-5)
ገጽ 9 “በመጀመሪያውም እግዚአብሔር ...” (ዘፍ 1፥1-2)

**ምዕራፍ አንድ፤ የተሰሚነት ኃይል**

ገጽ 27 “በጠፍርም በገተሩት ጊዜ ...” (የሐዋ 22፥25-29)
ገጽ 29 “ዘመኑ ተፈጸመ ...” (ማር 1፥15)

**ምዕራፍ ሁለት፤ አዳማዊ አስተዳደር**

ገጽ 32 “በመጀመሪያው እግዚአብሔር ...” (ዘፍ 1፥1)
ገጽ 32 “ብፁዕና ብቻውን ገዢ የሆነ ...” (1ጢሞ 6፥15)
ገጽ 33 “ዓለማትን በሥርዓት ያዘጋጀ ...” (መዝ 14፥1፤ 53፥1)
ገጽ 33 “ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ” (ዕብ 11፥3)
ገጽ 34 “ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን” (ዘፍ 1፥26-27)
ገጽ 35 “እግዚአብሔር፣ መሐሪ፣ ሞገስ ያለው ...” (ዘጸ 34፥6)
ገጽ 35 “ዓለሙንና በእርሱ ያለውን የፈጠረ” (ሐዋ 17፥24)
ገጽ 37 “ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ...” (1ቆሮ 6፥19)
ገጽ 37 “እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው” (ዘፍ 1፥28)
ገጽ 37 “ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ...” (ዘፍ 2፥16)
ገጽ 39 “በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ” (1ቆሮ 2፥11)
ገጽ 39 “የሰማይ ሰማያት የእግዚአብሔር ...” (መዝ 115፥16)
ገጽ 40 “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ...” (ዘፍ 2፥15)

**ምዕራፍ ሦስት፤ የነፃነት አዋጅ**

ገጽ 42 “እባቡም ለሴቲቱ አላት ...” (ዘፍ 3፥1-7)
ገጽ 43 “አዳምን ከአስወጣው (ፈጣሪ - ንጉሥ) በኋላ ...” (ዘፍ 3፥24)
ገጽ 44 “ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ ...” (ዘፍ 2፥16-17)
ገጽ 47 “ተገነዘቡ” (ዘፍ 3፥7) ወይም “አወቁ” (ዘፍ 3፥7 ኪጂምስ)
ገጽ 48 “በምድር ላይ የሚንቀሳቀሰውን ሁሉ ይግዙ” (ዘፍ 1፥26)
ገጽ 48 “ምድርም ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን” (ዘፍ 3፥17-19)
ገጽ 49 “ለሰው ቅን የምትመስል መንገድ አለች” (ምሳ 14፥12)
ገጽ 50 “ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና ...” (ሮሜ 3፥23)
ገጽ 51 “የውሸት አባት ... ነፍስ ገዳይ” (ዮሐ 8፥44)
ገጽ 51 “ሌባው ሊሰርቅና ...” (ዮሐ 10፥10)
ገጽ 52 “በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘሯ” (ዘፍ 3፥15)

**ምዕራፍ ዐራት፤ የገዢው መመለስ ተስፋ**

ገጽ 57 “እናንተም ለእኔ የካህናት መንግሥት” (ዘጻ 19፥6)
ገጽ 57 “ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ” (ዘሌ 20፥26)
ገጽ 58 “እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሣን ...” (ዘሌ 11፥44-45)
ገጽ 58 “የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ...” (ማቴ 5፥48)
ገጽ 59 “እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል ...” (ዘፍ 3፥15)
ገጽ 60 “ህፃን ተወልዶልናልና ...” (ኢሣ 9፥6)

ገጽ 60 "መስዋእትንና መባን አልወደድከም ..." (ዕብ 10፥5

ገጽ 61 "እግዚአብሔርም የሰውን ክፋት በምድ ላይ ..." (ዘፍ 6፥5-9፥1)

ገጽ 61 "እግዚአብሔር አምላክ ኖህን ባረከው ..." (ዘፍ 9፥1)

ገጽ 61 (ታላቅ ህዝብ ስለሚሆነው ልጁ ለአብርሃም የተሰጠ ተስፋና፤ የተስፋውም ፍጻሜ:: (ዘፍ 15፥1-6፤ 17፥15-21፤ 18፥2-19፤ 21፥1-7 ይመልከቱ)

ገጽ 61 (ኖህና አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የቀና መንገድ (ዘፍ 6፥8፤ 15፥6፤ ሮሜ 4፥3፤ ገላ 3፥6፤ ዕብ 11፥7-12፤ ያዕ 2፥23 ይመልከቱ)

ገጽ 62 ያዕቆብ ሊመጣ ባለው መሲህ የዘር ሃረግ ውስጥ ስለመግባት ስለመመረጡና/ እስራኤል ተብሎ ስሙ ስለመቀየሩ (ዘፍ 25፥21-26፤ 28፥10-15፤ 35፥10-12 ይመልከቱ)

ገጽ 62 ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች የእስራኤል ነገድ የመጀመሪያዎቹ ምንጮች:: (ዘፍ 35፥22-26፤ 49፥1-28 ይመልከቱ)

ገጽ 62 ይሁዳ ሊመጣ ያለው መሲህ ቀጣይ የዘር ሃረግ እንዲሆን ስመመረጡ:: (ዘፍ 49፥8-12 ይመልከቱ::)

ገጽ 62 ዐስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በግብጽ ውስጥ በዮሴፍ በኩል ጥበቃ እንደተደረገላቸው:: (ዘፍ 37፤ 39፥1-47፤ 12፤ 27 ይመልከቱ)

ገጽ 62 ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች በግብጽ ውስጥ ባሪያዎች ስለመሆናቸው:: (ዘጸ 1፥6-14 ይመልከቱ)

ገጽ 62 ሙሴ እስራኤላውያንን ነጻ ለማውጣት ስለመጠራቱ:: (ዘጸ 1፥15፤ 4፥31 ይመልከቱ:)

ገጽ 62 ሙሴ በግብፅ ላይ ስላመጣቸው መቅሰፍቶች:: (ዘጸ 6፥28-12፥36)

ገጽ 62 የቀይ ባህር መከፈል (ዘጸ 13፥17-14፥31)

ገጽ 62 የካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ህዝብ (ዘጸ 19፥6)



ገጽ 63 እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ቢታዘዙትና ቢታመኑበት ከህዝብ ሁሉ የተመረጠ እርስት እንደሚሆኑለት ስለመናገሩ:: (ዘጸ 19፥3-6፤ 39፥9-11)

ገጽ 64 ለእስራኤል ለሕይወቱ መመሪያ ወይም ህግ እንደተሰጠው:: ዘጸ 20፥1-23፥3፤ 24፥12-31፥18፤ 34፥12-27፤ 35፥1-19፤ 40፥1-15፤ ዘሌ 1-7፤ 11፥1-24፤ 25-27)

ገጽ 64 እስራኤላውያን በተራራው አጠገብ ከእግዚአብሔር ጋር እንደተገናኙ:: (ዘጸ 19፥9-20:21)

ገጽ 64 "ለያዕቆብ ቤት እንዲህ በል ..." ዘፀ 19፥3-6

ገጽ 64 ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን (ኤር 31፥33)::

ገጽ 65 እስራኤላውያን ህጉን ለመቀበል ስለመስማማታቸው (ዘጸ 24፥7-8)::

ገጽ 65 የዮርዳኖስ ወንዝ ስለመከፈሉ:: (ኢያ 3)

ገጽ 65 የኢያሪኮ ግንብ ስለመፍረሱ :: (ኢያ 6፥1-20)

ገጽ ፀሀይ ለሙሉ ቀን ሳትጠልቅ ስለመቆየቷ (ኢያ 10፥12-14)::

ገጽ 66 የአሮን ቤተሰብ ለክህነት ስለመመረጡና ሌሎች ሌዋውያንም እንዲረዷቸው ስለመደረጉ:: ዘጸ 28-29፤ 32፥25-29፤ ዘኍ 1፥47-53፤ 3፥5-13፤ 8፥5-26)

ገጽ 66 "እንደ ህጉም ከጥቂቶች በቀር ..." (ዕብ 9፥22)::

ገጽ 67 የእግዚአብሔር መንፈስ በስርየት መከደኛው ላይ በኪሩቤሎች መካከል ስለመኖሩ:: (ዘጸ 25፥22፤ ሌዋ 16፥2-34)

ገጽ 69 እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ምድራዊ ንጉሥ እንዲሰጣቸው ስለመጠየቃቸው:: (1ሳሙ 8፥4-22)

ገጽ 69 እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው ... (1ሳሙ 8፥7)::

ገጽ 69 የንጉሥ ዳዊት መሻት እንደ ሰማያዊው መንግሥት መሻት ስለመሆኑ:: (1ሳሙ 13፥13-14)::

ገጽ 69 ዳዊት ጎልያድን ስለመግደሉ:: (1ሳሙ 17፥4-51)

ገጽ 70 "አንተ ሰይፍና ጦር ጭሬም ይዘህ" (1ሳሙ 17፥45)

ገጽ 70 የሴቲቱ ዘር ከዳዊት ወገን እንደሚወጣ ስለመነገሩ:: (2ሳሙ 7፥12-16፤ ኢሳ 11፥1-10፤ ማቴ 1፥1-17)::

ገጽ 70 የነቢያት ሚና ምን ስለመሆኑ:: (ዘዳ 18፥15-22)

ገጽ 71 ኤልያስ የሴቲቱን ልጅ ከሞት እንዳስነሳ:: (1ነገ 17፥17-24)

ገጽ 71 ዳንኤል ስለ እስራኤል ህዝቦች መጻኢ ሕይወት ትንቢት ስለመቀበሉ (ዳን 10፥1-12፤ 13)

ገጽ 71 ዳንኤል ከአንበሶች ጉድጓድ በደህና ስለመውጣቱ:: (ዳን 6፥3-23)

ገጽ 71 ነቢያት እንደተንገላቱ:: (ማቴ 5፥11-12፤ ማቴ 23፥29-37)

ገጽ 71 የእግዚአብሔር መንፈስ ቤተመቅደሱን ለቆ ስለመሄዱ:: (ሕዝ 8፥1-11፥23)

ገጽ 72 "ህፃን ተወልዶልናልና" (ኢሣ 9፥6-7)

ገጽ 72 "የወይን እትክልት የተከለ ባለቤት" (ማቴ 21፥33-40፤43)

ገጽ 72 "መጥቶም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ" (ሚል 4፥6)

ገጽ 73 "ከዚህም በኋላ እንዲህ ይሆናል ..." (ኢዮ 2፥28-29)

ገጽ 73 "የጌታም ቀን ..." (ኢዮ 2፥11)

ገጽ 74 "መልእክተኛዬን እልካለሁ" (ሚል 3፥1)

ገጽ 74 "የአባቶችንም ልብ ..." (ሚል 4፥6)

ገጽ 74 "በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ" (ማቴ 3፥1-3)

ገጽ 74 "እኔ በውኃ አጠምቃለሁ ..." (ማቴ 3፥11)



**ምዕራፍ ዐምስት፤ የመንግሥቱ ዳግመኛ መወለድ**

ገጽ 77 "እግዚአብሔር መልአኩን ገብርኤልን ..." (ሉቃ 1፥26-30)

ገጽ 78 "ወንድ ልጅንም ትወልጃለሽ ..." (ሉቃ 1፥31-35፤ 37-38)

ገጽ 79 "የፍጥረት ሁሉ ሕይወት በደሙ ..." (ሌዋ 17፥14)

ገጽ 79 "ከሰማይ የመጣው ከሁሉ ..." (ዮሐ 3፥31፤34)

ገጽ 79 "እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ..." (ሉቃ 3፥16)

ገጽ 79 "ብትወዱኝ ቃሌን ጠብቁ ..." (ዮሐ 14፥15-20)

ገጽ 80 "በነጋታውም ዮሐንስ ኢየሱስ ..." (ዮሐ 1፥29-34)

ገጽ 81 "በእርሱ አካል የመለኮት ሙላት ተገልጦ ..." (ቆላ 2፥9)

ገጽ 81 "በመጀመሪያው ቃል ነበር" (ዮሐ 1፥1)

ገጽ 81 "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና" (ማር 1፥15)

ገጽ 82 "የጌታም ቀን ..." (ኢዮ 2፥11)

ገጽ 82 "ምድርና መላዋ የእግዚአብሔር ናት" (መዝ 24፥1)

ገጽ 82 "ሌባው ሊሰርቅና ..." (ዮሐ 10፥10)

ገጽ 82 "አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ..." (ማቴ 12፥29)

ገጽ 82 "ኢየሱስ 'ሁለተኛው' አዳም ስለመሆኑ::" (1ቆሮ 15፥45)

ገጽ 82 "አባታችን ሆይ፤ በሰማያት የምትኖር" (ማቴ 6፥9-10)

ገጽ 82 "የካህናት መንግሥትና የተቀደሰ ህዝብ" (ዘጸ 19፥6)

ገጽ 83 "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ" (ማቴ 4፥17)

ገጽ 83 "ኢየሱስም በገሊላ ሁሉ ..." (ማቴ 4፥23)

ገጽ 83 "እኔስ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማስወጣ ..." (ማቴ 12፥28)

ገጽ 83 "የእግዚአብሔር መንግሥት ..." (ማቴ 18፥23)

ገጽ 83 "የእግዚአብሔር መንግሥት ሰወይነ አትክልት" (ማቴ 20፥1)

ገጽ 83 "የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወስዳለች" (ማቴ 21፥43)

ገጽ 84 "ሰይጣንም ከፍ ወዳለ ተራራ ላይ አወጣው" (ማቴ 4፥8-11)

ገጽ 84 "የንስሃ ጥምቀት ..." (ማር 1፥4)

ገጽ 85 "የነብያት ጉባኤ ..." (2ነገ 2፥3፤4፥1)

ገጽ 86 "እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል..." (ማቴ 3፥13-14)

ገጽ 86 "ከእኔም በኋላ ከእኔ የሚበረታው ..." (ማር 1፥7-8)

ገጽ 87 "አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ" (ማቴ 3፥15)

ገጽ 87 "በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀመዛሙርቱ ..." (ዮሐ 1፥35-40)

ገጽ 88 "ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ..." (ማቴ 3፥16)

ገጽ 88 "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ..." (ማር 9፥7)

ገጽ 88 "ተከተለኝ" (ማቴ 4፥19)

ገጽ 88 "ሁለት ጌቶችን ማገልገል ..." (ማቴ 6፥24)

ገጽ 88 "በመንፈስ ቅዱስና በእሳትም ያጠምቃችኋል" (ማቴ 3፥11)

ገጽ 89 "በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና" (ምሳ 23፥7)

ገጽ 89 "ሀሳቤ እንደሀሳባችሁ ..." (ኢሳ 55፥8-9)

ገጽ 90 "በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ..." (ሉቃ 4፥1-2)

ገጽ 90 "ኢየሱስም ወደ ገሊላ ተመለሰ ..." (ሉቃ 4፥14)

ገጽ 90 "ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ ..." (ማቴ 4፥17)

ገጽ 90 "ትምህርቴ ከእኔ ከራሴ አይደለም" (ዮሐ 7፥16)

ገጽ 90 "የምትሰሙት ይህ ቃሌ ከራሴ ..." (ዮሐ 14፥24)



ገጽ 90 "አባቴ ሁል ጊዜ ይሠራል ..." (ዮሐ 5፥17)

ገጽ 90 "እኔና አብ አንድ ነን" (ዮሐ 10፥30)

ገጽ 90 "እውነቱንም ነገርኳችሁ፤ ልጅ በራሱ አንዳች ..." (ዮሐ 5፥19)

ገጽ 90 "የአባቴን ሥራ የማደርግ ከሆነ ..." (ዮሐ 10፥37-38)

ገጽ 91 "እግዚአብሔር አባታችሁ ከሆነ ..." (ዮሐ 8፥42)

ገጽ 91 "እኔ ከአባቴ ዘንድ መጥቻለሁና ..." (ዮሐ 16፥28)

ገጽ 91 "ኢየሱስ በሽተኞችን ስለመፈወሱ" (ሉቃ 7፥2-10)

ገጽ 91 "ኢየሱስ በሉሲፈር ሠራዊት የታሠረውን ነፃ እንዳወጣ" (ማር 5፥2-15)

ገጽ 91 "ኢየሱስ በጥቂት ዓሳና ዳቦ ሺዎችን እንደመገበ።" (ሉቃ 9፥11-17)

ገጽ 91 "ኢየሱስ ሰዎችን ከሞት እንዳስነሣ" (ሉቃ 7፥11-15)

ገጽ 92 "ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና ..." (ዮሐ 10፥17-18)

ገጽ 93 "ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ" (ሮሜ 6፥3-4)

ገጽ 93 "እኔ መልካም እረኛ ነኝ" (ዮሐ 10፥14-16)

ገጽ 93 "ክርስቶስ መከራ ይቀበላል፤ በሦስተኛውም ..." (ሉቃ 24፥46)

ገጽ 93 "ተፈጸመ" (ዮሐ 19፥30)

ገጽ 93 አባት ሆይ! ሰዓቱ ደርሷል ... (ዮሐ 17፥1-5)

ገጽ 94 "ምድርም እግዚአብሔርን በማወቅ ትሞላለች" (ዕን 2፥14)

ገጽ 94 "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በስጋ ላይ ..." (ገላ 5፥17-18)

ገጽ 94 “አባት ሆይ ብትፈቅድስ ይህች ድዋ ...” (ሉቃ 22፥42)

ገጽ 95 “ብትወዱኝስ ያዘዝኳችሁን ...” (ዮሐ 15፥15-16)

ገጽ 95 “በእኔ ብትሆኑ እኔም በእናንተ ...” (ዮሐ 15፥4-6)

ገጽ 95 “ጸጋዬ ይበቃሃል ...” (2ቆሮ 12፥9)

ገጽ 95 “ስደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝ” (2ቆሮ 12፥10)

ገጽ 96 “በእናንተ ዘንድ ይሆናል በእናንተም ውስጥ ...” (ዮሐ 14፥17)

ገጽ 96 “አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል እልክላችኋለሁ” (ሉቃ 24፥49)

ገጽ 97 “እርሱም በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል” (ማቴ 3፥11)

ገጽ 97 “የእውነት መንፈስ ... ከእናንተ ጋር ይኖራል ...” (ዮሐ 14፥17)

ገጽ 98 ኢየሱስ በውሃ ላይ ስለመራመዱ:: (ማቴ 14፥23-33)

ገጽ 98 ኢየሱስ ብዙ ዓሶች እንዲጠመዱ ስለማድረጉ:: (ሉቃ 5፥3-11)

ገጽ 98 ኢየሱስ ለምጻሙን ሰው እንደፈወሰ:: (ማር 1፥40-42)

ገጽ 98 እኔ አሁን ትቻችሁ እሄዳለሁ ነገር ግን ... (ዮሐ 14)

ገጽ 98 “የመቅደሱ መጋረጃ ከሁለት ስለመተርተሩ” (ማር 15፥37-38)

ገጽ 99 “የዘመኑም ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ ...” (ገላ 4፥4-7)

ገጽ 99 “አጽናኙም በመጣ ጊዜ” (ዮሐ 15፥26)

ገጽ 99 “የአብን የተስፋ ቃል እልክላችኋለሁ” (ሉቃ 24፥49)

ገጽ 100 “እኛ ያለ ቄሳር ንጉሥ የለንም ...” (ዮሐ 19፥12-16)

ገጽ 100 “ነፍሱን ተወ” (ዮሐ 19፥30)

ገጽ 100 “ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ ...” (ሮሜ ፥11)



## ምዕራፍ ስድስት፤ ንጉሡ ለዜጎቹ ያለው ፍቅር

ገጽ 102 “በእርሱ የሚያምን ሁሉ ...” (ዮሐ 3፥16)

ገጽ 103 አንድ ሰው ለዘለዓለም ለመኖር ቢፈልግ ለራሱ መሞት እንዳለበት፣ በመንግሥቱ ኃይል ለመበርታትም፣ በራሱ መድከም እንደሚገባው፤ (ዮሐ 11፥25-26፤ ማቴ 5፥3)

ገጽ 103 “እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ... (ፊል 2፥6-8)

ገጽ 103 “እኔም አብን እለምናለሁ...” (ዮሐ 14፥16-20)

ገጽ 104 “የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ” (2ቆሮ 8፥9)

ገጽ 104 “እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ” (ዮሐ 5፥19)

ገጽ 104 “አባት ሆይ በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር ...” (ዮሐ 17፥5)

ገጽ 104 “ኢየሱስም ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ...” (ማቴ 17፥1-5)

ገጽ 105 “የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ” (ገላ 4፥4-5)

ገጽ 105 ኢየሱስ ህጉ ለሚጠይቀው ስለመታዘዙና እንዳደረገውም (ማቴ 3፥15፤ 5፥17)

ገጽ 105 “በትእዛዜም ይሄዱ ዘንድ ፍርዴንም ...” (ሕዝ 11፥19-20)

ገጽ 105 ኢየሱስም ውሃ እንድትሰጠው ስለመጠየቁ (ዮሐ 4፥5-7

ገጽ 105 ኢየሱስ ከበለስ ፍሬ ፈልጎ ስለመቆሙ (ማቴ 21፥19)

ገጽ 105 “እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛል ...” (መዝ (121) ፥4)

ገጽ 105 ኢየሱስ ማዕበል በሚያናውጣት ጀልባ ውስጥ ስለመተኛቱ (ሉቃ 8፥22-25)

ገጽ 105 ኢየሱስ የሞትን መውጊያ ከሰው ላይ ስለማስወገዱ (1ቆሮ 15፥55-57)

ገጽ 106 ንጉሡ - አባት፣ ንጉሡ ልጅ በመሞቱ ደስተኛ ስለመሆኑ (ኢሳ 53፥10-11)

ገጽ 106 “የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና” (ሮሜ 6፥23)

ገጽ 106 “እግዚአብሔርም ጌታንም አስነሣ” (1ቆሮ 6፥14)

ገጽ 106 እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ... (2ቆሮ 5፥21)

ገጽ 106 “በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት” (ዮሐ 3፥16)

ገጽ 106 “እኔ መልካም የበጎች እረኛ ነኝ” (ዮሐ 10፥14-15)

ገጽ 107 “አሁን ወደ ላከኝ ወደ እርሱ እሄዳለሁ” (ዮሐ 16፥5-7፤16)

ገጽ 108 “እኔ እሄዳለሁ ... (ዮሐ 16፥7) ገኘሮው አሁን ከእናንተ ጋር ነው” (ዮሐ 14፥17)

ገጽ 108 “የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሷል” (ዮሐ 12፥32)

ገጽ 109 “እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ...” (ማቴ 7፥11)

ገጽ 109 “አንተ ታናሽ መንጋ መንግሥትን ይሰጥህ ...” (ሉቃ 12፥32)

## ምዕራፍ ሰባት፤ ግንኙነቱን እንደገና መመስረት

ገጽ 110 “በእናንተ ዘንድ ይሆናል፤ በእናንተም ውስጥ” (ዮሐ 14፥17)

ገጽ 110 “አባቴ እንደላከኝ እኔ ደግሞ ...” (ዮሐ 20፥21-22)

ገጽ 110 “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ፈጠረ ...” (ዘፍ 2፥7)

ገጽ 111 “ቴዎፍሎስ ሆይ ኢየሱስ የመረጣቸውን ...” (ሐዋ 1፥1-3)

ገጽ 112 “ፈሪሣውያንም የእግዚአብሔር መንግስት መቼ ...” (ሉቃ 17፥20-21)

ገጽ 112 “እውነት እላችኋለሁ ከዚህ ከቆሙት ...” (ማር 9፥1)



ገጽ 112 በበዓለ ሃምሣ ዕለት መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ መቶ ሃያ የሚያህሉ ደቀመዛሙርት በዚያ እንደነበሩ” (የሐዋ 1፥15-2፥3)

ገጽ 112 “ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተነጋገረ በኋላ ...” (ማር 16፥19)

ገጽ 112 “እኔም አብን እጠይቃለሁ ...” (ዮሐ 14፥16-17)

ገጽ 113 “አብ በስሜ የሚልከው መንፈስ ቅዱስ ...” (ዮሐ 14፥26)

ገጽ 113 “የአብን የተስፋ ቃል እልክላችኋለሁ” (ሉቃ 24፥49)

ገጽ 113 “ከእነርሱ ጋር እንጀራ እየቆረሰ ሳለ ...” (የሐዋ 1፥4-5፤8)

ገጽ 113 “ኃይልን ከላይ” (ሉቃ 24፥49)

ገጽ 114 “በዓለ ሃምሣ የተባለውም ቀን ...” (ሐዋ 2፥1-4)

ገጽ 114 የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በልዩ ልዩ ልሣናት መናገር ስለመቻላቸው (የሐዋ 2፥5-11)

ገጽ 114 “እነዚህም ምልክቶች ይከተሏችኋል” (ማር 16፥17)

ገጽ 114 “ለምንድነው እንደዚህ የምትናገሩት ...” (የሐዋ 2፥12-13)

ገጽ 115 “አይሁድና በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ...” (የሐዋ 2፥14-18፤ 32-33)

ገጽ 116 “መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም” (ዮሐ 18፥36)

ገጽ 116 “እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን ...” (ዮሐ 14፥12)

ገጽ 116 “በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርጋለሁ ...” (ዮሐ 14፥13)

## ምዕራፍ ስምንት፤ ገዢውን ወደ ስፍራው መመለስ

ገጽ 118 "እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ሁሉ" (ዮሐ 4፥14)

ገጽ 119 "በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና" (2ቆሮ 1፥21-22)

ገጽ 119 "አሁን፣ ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው ..." (2ቆሮ 5፥5)

ገጽ 119 "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል" (ኤፌ 1፥13-14)

ገጽ 119 "እንግዲያስ ከቅዱሳን ጋር" (ኤፌ 2፥19)

ገጽ 120 "እውነት እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታስሩት" (ማቴ 18፥18-20)

ገጽ 120 "እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውሃና ..." (ዮሐ 3፥5-7)

ገጽ 120 "እንግዲህ እንደተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን ..." (ኤፌ 5፥1-2)

ገጽ 121 "ኃይልን ትቀበላላችሁ" (የሐዋ 1፥8)

ገጽ 121 "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣ" (ዮሐ 7፥37-38)

ገጽ 121 "ይህንንም ስለ መንፈስ ቅዱስ ተናገረ" (ዮሐ 7፥39)

ገጽ 122 "እኔስ በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማስወጣ ... " (ማቴ 12፥28)

ገጽ 123 "ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ..." (ማቴ 11፥2-5)

ገጽ 123 "ይህ የመንግሥት ወንጌል ..." (ማቴ 24፥14)

ገጽ 123 "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ ..." (መዝ (19)፥1-4)

ገጽ 124 "ብርሃናችሁ በሰው ሁሉ ፊት ይብራ ..." (ማቴ 5፥16)

ገጽ 124 "አስቄዋ ለሚባል የምኩራብ አለቃ ሰባት ..." (የሐዋ 19፥14-17)

ገጽ 125 "ንስሃ ግቡ ተጠመቁም" (የሐዋ 2፥38)

ገጽ 126 "በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ" (ሮሜ 6፥4)



ገጽ 126 "ምን እንበላለን? ብላችሁ አትጨነቁ" (ማቴ 6፥31-34)

## ምዕራፍ ዘጠኝ፤ ግንኙነትን እንደገና የመመሥረት ውጤቶች

ገጽ 127 "እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰው ከውሃና ..." (ዮሐ 3፥5-8)

ገጽ 128 አለቅነት በንጉሡ ጫንቃ ላይ ስለመሆኑ፤ የንጉሡ ስሞች ለምሣሌም ድንቅ መካር ስለመባሉ:: (ኢሣ 9፥6)

ገጽ 128 "በመጨረሻውም ዘመን በስጋ ለባሽ ..." (ኢዮ 2፥28-29)

ገጽ 130 "በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ" (ገላ 3፥26-29)

ገጽ 130 "ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ ..." (የሐዋ 2፥38)

ገጽ 131 "ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ... " (2ጴጥ 3፥9)

ገጽ 131 በጸጋ በእምነት አድኖአችኋልና (ኤፌ 2፥8-9)

ገጽ 131 "እርሱም የኃጢአታችን ማስተስረያ ነው" (1ዮሐ 2፥2)

ገጽ 132 "የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅ ..." (ሮሜ 14፥17-18)

ገጽ 133 "ልሰቅልህ ሥልጣን አለኝ ወይም ልፈታህ" (ዮሐ 19፥10)

ገጽ 133 ኢየሱስ ዐስራ ሁለት ምድብ ሠራዊት መጥራት ስለመቻሉ" (ማቴ 26፥51-54)

ገጽ 133 "በእኔ ላይ አንዳች ሥልጣን ..." (ዮሐ 19፥11)

ገጽ 133 "በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ ..." (ማቴ 28፥18-20)

ገጽ 133 "ኃይልን ትቀበላላችሁ" (የሐዋ 1፥8)

ገጽ 134 "እኔ ከራሴ አንዳች አልናገርም" (ዮሐ 12፥49)

ገጽ 134 "አጽናኝ የሆነው መንፈስ ቅዱስ" (ዮሐ 14፥26)

ገጽ 134 "ነገር ግን እርሱ የእውነት መንፈስ" (ዮሐ 16፥13-15)

ገጽ 134 "አሁን እናንተ ታዝናላችሁ ..." (ዮሐ 16፥22-24፤ 26-28)

ገጽ 135 "የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ" (ማቴ 16፥19)

ገጽ 136 "ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ..." (2ጴጥ 3፥13)

ገጽ 136 "አዲስ ሰማይንና አዲስን ምድር አየሁ ..." (ራዕ 21፥1-5)

ገጽ 137 "ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም ..." (ገላ 5፥17)

ገጽ 137 "በመንፈስ ተመላለሱ የስጋንም ምኞት ..." (ገላ 5፥16)

ገጽ 137 "በእግዚአብሔር እሣብ ላይ የሚነሳውን ..." (2ቆሮ 10፥5)

ገጽ 137 "አሣቤ እንደ አሣባችሁ ..." (ኢሣ 55፥8-10)

ገጽ 138 "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ..." (2ቆሮ 5፥17)

ገጽ 138 "ከእነርሱም ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ..." (ዕብ 10፥16-17)

ገጽ 138 "ጽድቅ፣ ሰላምና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ" (ሮሜ 14፥17)

ገጽ 138 "በቅን ልብ እንቅረብ ..." (ዕብ 10፥22)

ገጽ 138 "በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ..." (ሮሜ 12፥2)

ገጽ 138 "እኔን ያየ አብን አይቷል" (ዮሐ 14፥9)

ገጽ 139 "ልጆቼ ሆይ እናንተ ከእግዚአብሔር ..." (1ዮሐ 4፥4)

ገጽ 139 "ለናንተ ወዳጆቼ እላችኋለሁ፣ ስጋን የሚገድሉትን ..." (ሉቃ 12፥4-8)

ገጽ 139 ንጉሡ የፍርሃት መንፈስ እንዳልሰጠን:: (2ጢሞ 1፥7)

ገጽ 140 "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ ..." (ኤፌ 2፥10)

ገጽ 142 "እንግዲህ ምህረትን እንድንቀበል ..." (ዕብ 4፥16)

ገጽ 143 "በርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ ..." (1ቆሮ 2፥11)

ገጽ 143 ኢየሱስ ብዙ ጊዜ ሲጸልይ ብቻውን ስለመለየቱ" (ማር 1፥35፤ ሉቃ 5፥16)



ገጽ 143 "ስትጸልዩም ..." (ማቴ 6፥5-7)

**ምዕራፍ ዐሥር፤ የገሀው ባህርይ**

ገጽ 146 "እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ..." (ዮሐ 16፥13-14)

ገጽ 147 "ብርቱ ንፋስም ተራሮችን ሰነጠቀ አለቶቹንም" (1ነገ 19፥11-13)

ገጽ 148 "በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ..." (ፊል 2፥6-7)

ገጽ 148 "መንፈስ ቅዱስም በአንቺ ላይ ..." (ሉቃ 1፥35)

ገጽ 148 "እኔና አብ አንድ ነን " (ዮሐ 10፥30)

ገጽ 148 "ማንም የሚወደኝ ቢኖር ቃሉን ..." (ዮሐ 14፥23)

ገጽ 149 "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚያመልኩትም ..." (ዮሐ 4፥24)

ገጽ 149 "ሌላም አጽናኝ ..." (ዮሐ 14፥16)

ገጽ 149 "አጽናኙ በመጣ ጊዜ ..." (ዮሐ 15፥26)

ገጽ 149 "እውነት እላችኋለሁ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ ... " (ማር 3፥28-29)

ገጽ 150 "ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል ዛሬ ድምጹን ..." (ዕብ 3፥7-8)

ገጽ 150 "መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ታጋሽ እንደሆነ ስለመናገሩ ..." (ዘፀ 34፥6፤ ሮሜ 2፥4)

ገጽ 151 "ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር ..." (ኤፌ 4፥30)

ገጽ 153 "የእውነት መንፈስ ኢየሱስ አለ..." (ዮሐ 16፥13-14)

ገጽ 153 "ነገር ግን አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ..." (ዮሐ 14፥26)

ገጽ 153 "እኔም አብን እለምናለሁ ..." (ዮሐ 14፥16)

ገጽ 153 "ጥቂት ጊዜ አለ እታዩኝም (ዮሐ 16፥16)

ገጽ 154 የጠፋውን በግ ስመፈለግ ስለወጣው እረኛ ምሳሌ የተሰጠ ማብራሪያ" (ሉቃ 15፥4-7)

ገጽ 154 "እርሱ የእውነት መንፈስ" (ዮሐ 16፥13)

ገጽ 155 "የእግዚአብሔርም መንፈስ ያርፍበታል" (ኢሣ 11፥2)

ገጽ 156 "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው" (ሉቃ 4፥18-19)

ገጽ 156 "ምድርም እግዚአብሔርን በማወቅ ..." (ዕን 2፥14)

ገጽ 156 "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ..." (ማቴ 28፥19-20)

ገጽ 157 "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ..." (ኤፌ 2፥10)

ገጽ 157 "ነገር ግን አይንም ያላየችው ..." (1ቆሮ 2፥9-10)

ገጽ 157 "የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም" (1ቆሮ 2፥12)

ገጽ 158 "ለፍጥረታዊም ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ..."
(1ቆሮ 2፥14)

ገጽ 158 "እርሱም መጥቶ ዓለምን ስለ ..." (ዮሐ 16፥8-11)

ገጽ 159 "በሰው ገመድ በፍቅርም አሥራት ..." (ሆሴ 11፥4)

ገጽ 159 "እርሱ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል" (ዮሐ 16፥13)

ገጽ "እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ ..."
(2ተሰ 2፥13)

**ምዕራፍ ዐሥራ አንድ፤ የገገርው ባህል**

ገጽ 163 "እንደሚያገሣ አንበሳ ..." (ምሳ 28፥15-16)

ገጽ 163 "ጻድቀን በበዙ ጊዜ ህዝብ ደስ ይሰዋል ..." (ምሳ 29፥2)

ገጽ 163 "የኢዮርብዓም ልጅ ናዳብ ..." (1ነገ 15፥25-26)

ገጽ 163 "የእሥራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን ስላስቆጣው ..." (1ነገ 15፥30)



ገጽ 163 "ኢዮርብአም የእስራኤል ህዝብ ጣኦት እንዲያመልኩ እንዳደረጋቸውና ሌዋውያን ያልሆኑ ካህናትን ስለመሾሙ" (1ነገ 12፥26-33፤ 13፥33-34)

ገጽ 163 "አክዓብ ከእርሱ በፊት ከነበሩት ይልቅ..." (1ነገ 16፥30-33)

ገጽ 163 "የታሠረውና የተሰቀቀውም እንደጠፋ ..." (2ነገ 14፥26)

ገጽ 164 "በእግዚአብሔርም ፊት መልካም የነበረውን አደረገ"
(2ነገ 18፥3፤5-7)

ገጽ 164 "እግዚአብሔር የይሁዳን ህዝብ ከአስጨናቂ ጠላቶቻቸው እንደታደገ" (2ነገ 18፥13-19፥37)

ገጽ 164 "እኔ መልካም እረኛ ነኝ ..." (ዮሐ 10፥11)

ገጽ 164 "እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ..." (ዮሐ 6፥35)

ገጽ 164 "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ..."
(ማቴ 11፥28-30)

ገጽ 165 "የአህዛብ አለቆች እንዲገዟቸው ..." (ማቴ 20፥25-28)

ገጽ 165 "የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ..." (ማቴ 4፥17)

ገጽ 166 የንጉሡን ባህርያት የሚገልጹ ዝርዝሮች (ገላ 5፥22-23)

ገጽ 166 "የመንፈስ ፍሬ ..." (ገላ 5፥22)

ገጽ 167 "የዋሆች ብፁዓን ናቸው ..." (ማቴ 5፥5)

ገጽ 167 "በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" (ማቴ 7፥16፤20)

ገጽ 168 "ሀገራችን በሰማይ ነው" (ፊል 3፥20)

ገጽ 168 "የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑቱ ..." (ገላ 5፥24-25)

ገጽ 168 "በእናንተ ውስጥ ያለው .. ." (1ዮሐ 4፥4)

ገጽ 168 "በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ሥራ ..."
(ገላ 5፥16-18)

ገጽ 169 "የሥጋም ሥራ የተገለጠ ነው ..." (ገላ 5፥19-21)

ገጽ 170 "ማስጠንቀቂያ በሚያስማበት ውስጣዊ ..." (ሮሜ 2፥14-15)

ገጽ 170 “ገዢው የንጉሡን ፈቃድ ያሳስበናል”
(ዮሐ 14፥26)

ገጽ 170 “የኔ ፈቃድ አይሁን ...” (ሉቃ 22፥42)

ገጽ 170 “ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ግን ...” (ዮሐ 6፥63)

ገጽ 171 “አባ አባት” (ሮሜ 8፥15፤ ገላ 4፥6)

ገጽ 171 ንጉሡ ነገሮችን የፈፀመው በፍቅር ብቻ አልነበረም፣ እርሱ ራሱ ፍቅር ነው” (1ዮሐ 4፥8፤16፤ ኤፌ 2፥14)

ገጽ 171 “የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ...”
(ማቴ 5፥48)

ገጽ 171 “ወይስ ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት ...”
(1ቆሮ 6፥19-20)

ገጽ 172 “የሰውነት መብራት ዓይንህ ናት ...” (ሉቃ 11፥34)

ገጽ 172 “ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ...”
(ዮሐ 17፥15-16፤18)

ገጽ 173 “በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ...”
(ኤፌ 2፥1-6:10)

ገጽ 173 “መልካሙን ሥራችሁን አይተው ...” (ማቴ 5፥16)

ገጽ 173 “የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች” (1ቆሮ 12፥7-11)

ገጽ 174 “ቃሉንም የተቀበሉት ተጠመቁ” (የሐዋ 2፥41-47)

**ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ፤ የመንግሥቱን ባህል መግለጥ**

ገጽ 180 “ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ...
(ዘፍ 11፥1-2)

ገጽ 181 ምሥራቁ የኤደን ገነት ክፍል በጥበቃ ሥር መዋሉ (ዘፍ 3፥24)

ገጽ 181 “የፈለጉት እስከ ሰማይ ድረስ የሚጠጋ ግንብ (ዘፍ 11፥1-9)

ገጽ 181 “ግንብንም እንሠራለን ለራሳችንም ...” (ዘፍ 11፥4)

ገጽ 181 “እነርሱ አንድ ወገን ናቸው ለሁሉ አንድ ... (ዘፍ 11፥6)



ገጽ 182 “ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ...
(ዘፍ 11፥7)

ገጽ 182 “ስለዚህም ስምዋ ባቢሎን ተባለ (ዘፍ 11፥9)

ገጽ 183 “ኃይልን ትቀበላላችሁ ... (የሐዋ. ሥራ 1፥8)

ገጽ 183 “ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል
(ማር 16፥17-18)

ገጽ 183 “በዓለ ሃምሣ የተባለውም ቀን ... (ሐዋ 2፥1)

ገጽ 184 “እግዚአብሔር ይህንን ኢየሱስን ከሞት ...
(ሐዋ 2፥32-33)

ገጽ 186 “እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ...
(ሮሜ 8፥26-27)

ገጽ 186 “እንግዲህ በልሣን መናገር ለማያምኑ ነው እንጂ
(1ቆሮ 14፥22)

ገጽ 187 “በልሣኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርን ሲያከብሩ ...
(የሐዋ 10፥46)

ገጽ 188 “እነርሱ አንድ ወገን ናቸው (ዘፍ 11፥6-9)

ገጽ 190 “በዓለም ምናልባትም ቁጥር የሌለው ቋንቋ ...
(1ቆሮ 14፥10-11)

ገጽ 190 “በልሣን የሚናገር ለእግዚአብሔር ... (1ቆሮ 14፥2)

ገጽ 191 ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን አብልጠን መሻት እንደሚገባን ስለመናገሩ (1ቆሮ 12፥7-8፤10)

ገጽ 191 “በልሣን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር ... (1ቆሮ 14፥2)

ገጽ 192 “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ...” (1ቆሮ 12፥7-8፤ 10)

ገጽ 192 “እናንተ አሁን የክርስቶስ አካል ናችሁ (1ቆሮ 12፥27-30)

ገጽ 192 “በምትሰበሰቡበት ጊዜ ... (1ቆሮ 14፥26-27)

ገጽ 192 “ስለዚህም በልሣን የሚናገር ... (1ቆሮ 14፥13)

| | |
|---|---|
| ገጽ 193 | "ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ትንቢት ለመናገር ... (1ቆሮ 14፥39-40) |
| ገጽ 193 | "እጵሎስ በቆሮንቶስ ሳለ ... (ሐዋ 19፥1) |
| ገጽ 193 | "አንዳንድ ደቀመዛሙርትንም አገኘ... (የሐዋ 19፥2-4) |
| ገጽ 194 | "መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንኳን ... (የሐዋ 19፥2) |
| ገጽ 194 | በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በውሃ ተጠቋቁ ... መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ላይ ወረደ፤ በልሣናት ተናገሩ እንደተናገሩ:: (ሐዋ 19፥5-6) |
| ገጽ 194 | "በልሣን የሚናገር ራሱን ያንጻል" (1ቆሮ 14፥4) |
| ገጽ 194 | "እኔም አብን እለምናለሁ ..." (ዮሐ 14፥16-17) |
| ገጽ 195 | "እንዲሁም መንፈስ ድካማችንን ያግዛል" (ሮሜ 8፥26-27) |
| ገጽ 195 | "ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ ..." (ይሁዳ 20) |
| ገጽ 195 | "በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ..." (ኤፌ 5፥19) |
| ገጽ 196 | "እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን ..." (ሮሜ 8፥26) |
| ገጽ 196 | "በነገር ሁሉ በፀሎትና በምልጃ ..." (ፊል 4፥6-7) |
| ገጽ 196 | "በመንፈሴ እጸልያለሁ ..." (1ቆሮ 14፥15) |
| ገጽ 196 | "ነገር ግን አንደበቱን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም" (ያዕ 3፥8፤ 10-11) |
| ገጽ 197 | "የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ" (የሐዋ 2፥39) |
| ገጽ 198 | "ጳውሎስ አዘወትሮ በልሣን ይጸልይ እንደነበረ" (1ቆሮ 14፥18) |
| ገጽ 198 | "በአዕምሮም እጸልያለሁ ..." (1ቆሮ 14፥15) |



## ምዕራፍ ዐስራ ሦስት:- የገገርው አስተዳደር

| | |
|---|---|
| ገጽ 199 | "ይህን ሁሉ ግን ያው አንዱ መንፈስ ..." (1ቆሮ 12፥11) |
| ገጽ 200 | "ስለ መንፈሳዊ ነገርም ታውቁ ዘንድ..." (1ቆሮ 12፥1፤ 8-10) "ስለ ጥበብ ቃል" "የእውቀት ቃል" "ተአምራትን ማድረግ" እና "መናፍስትን መለየት" |
| ገጽ 200 | "ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋን ደጋግ መጋቢዎች ..." (1ጴጥ 4፥10) |
| ገጽ 200 | "የፀጋ ሥጦታም ልዩ ልዩ ነው ..." (1ቆሮ 14፥4-6) |
| ገጽ 201 | "እርሱም አንዳንዶችን ሐዋርያት ..." (ኤፌ 4፥11-13) |
| ገጽ 203 | "ለአንዱም ጥበብ መናገር ..." (1ቆሮ 12፥8) |
| ገጽ 203 | "የዚህ መጽሐፍ ህግ ከአፍህ አይለይ" (ኢያ 1፥8) |
| ገጽ 203 | መንፈስ ቅዱስ ጳውሎስንና ባርናባስን ስጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ ሲል በጥበብ ቃል ስለመናገሩ (የሐዋ 13፥1-4) |
| ገጽ 204 | ጳውሎስ እስረኛ ሆኖ ወደ ሮም በሚወሰድበት ጊዜ መርከቧ የማዕበል ችግር እንዳጋጠመት (የሐዋ 27፥1-21) |
| ገጽ 204 | "እይዟችሁ ብየ እመክራችኋለሁ ..." (የሐዋ 27፥22-26) |
| ገጽ 204 | "ለሌላውም የእውቀትን ቃል መናገር ..." (1ቆሮ 12፥8) |
| ገጽ 205 | ኢየሱስ በውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛት ሴት አስቀድሞ አምስት ባሎች እንደነበሯት በእውቀት ቃል አማካይነት ስለማሳወቁ (ዮሐ 4፥5-42) |
| ገጽ 205 | አጋቦስ የተባለው ነቢይ ስለስባቱ የረሃብ ዓመታት የእውቀት ቃል ስለመቀበሉ (የሐዋ 11፥27-30) |
| ገጽ 205 | ሐናንያና ሰፔራ መሬታቸውን ስለሸጡበት ገንዘብ መዋሸታቸውን የሚያሳውቅ የእውቀት ቃል ጴጥሮስ እንደተቀበለ (የሐዋ 5፥1-11) |
| ገጽ 205 | ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ፤ በእስያ ስለነበሩ ሰባት አብያተክርስቲያናት በራዕይ በኩል የጥበብ ቃል ስለመቀበሉ (ራዕ 1፥1-4፤ 2፥1-3፥22) |
| ገጽ 206 | "ለሌላውም በዚያው መንፈስ እምነት ..." (1ቆሮ 12፥9) |

ገጽ 206 “ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ...”
(ዕብ 11፥6)

ገጽ 206 “እምነትም ከመስማት ነው...” (ሮሜ 10፥17)

ገጽ 206 ወደ እቶን እሳት ቢጣሉም እንኳን እግዚአብሔር ሊያድናቸው እንደሚችል ስለተናገሩት ሦስት ዕብራውያን እምነት (ዳን 3፥1-28)

ገጽ 207 አልዓዛር ከሞት ይነሳል የሚለው የኢየሱስ መታመን
(ዮሐ 11፥1-45)

ገጽ 207 የጴጥሮስና የዮሐንስ ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ሽባ የነበረው ሰው ይፈውሳል የሚል እምነት (የሐዋ 3፥1-8)

ገጽ 207 “ለሌላውም በዚያው መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ...”
(1ቆሮ 12፥9)

ገጽ 207 “የመፈወስ ኃይል ስጦታዎች” (1ቆሮ 12፥9)

ገጽ 207 “ኢየሱስም በገሊላ ሁሉ እየተዘዋወረ” (ማቴ 4፥23)

ገጽ 208 “እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከመ”
(1ጴጥ 2፥24)

ገጽ 208 የሰለለ የሰው እጅ ስለመፈወሱ፡፡ (ማር 3፥1-5) የመቶ አለቃው ሠራተኛ ስለመፈወሱ (ማቴ 8፥5-13፤ ሉቃ 7፥1-10) እውር ሆኖ የተወለደው ሰው ብርሃኑን ስለማግኘቱ (ዮሐ 9፥1-7) ለአስራ ሁለት ዓመት ጸም የሚፈሳት ሴት መፈወስ (ማር 5፥24-34)

ገጽ 208 በጴጥሮስ አገልግሎት በኩል ኤኒያ የተባለ ለስምንት ዓመታት ሽባ ሆኖ በአልጋ ላይ የኖረ ሰው ስለመፈወሱ (የሐዋ 9፥32-35)

ገጽ 208 ጳውሊዮስ በሚሊጢን ደሴት በተቅማጥና በንዳድ በሽታ ታሞ የነበረው ሰወ ስለመፈወሱ (ሐዋ 28፥7-8)

ገጽ 209 “ለሌላውም ተአምራትን ማድረግ” (1ቆሮ 12፥10)

ገጽ 209 ሙሴ ቀይ ባህርን በበትር ስለመክፈሉ (ዘጸ 14፥5-31)



ገጽ 209 ረሃብ በሆነ ጊዜ አንዲት ሴት ያለማቋረጥ ስለተለቀቀላት ዘይትና ዱቄት (1ነገ 17፥1-16)

ገጽ 209 ኢየሱስ በአምስት እንጀራና በሁለት አሣ አምስት ሺህ የሚያህሉ ሰዎችን ስለመመገቡ፡፡ (ዮሐ 6፥5-14)

ገጽ 209 የኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ማስነሳት፡፡ (ዮሐ 11፥38-45)

ገጽ 209 የጴጥሮስ ዶርቃን ከሞት ማስነሳት፡፡ (የሐዋ 9፥36-42)

ገጽ 209 ኤልማስ የተባለው ሰው ለጊዜውም ስለመታወሩ
(የሐዋ 13፥6-12)

ገጽ 210 “ለሌላውም ትንቢትን መናገር ...” (1ቆሮ 12፥10)

ገጽ 210 “ፍቅርን ተከታተሉ፤ ነገር ግን መንፈሳዊ ስጦታን
አጥብቃችሁ ፈልጉ” (1ቆሮ 14፥1-5)

ገጽ 211 “ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢትን ...”
(የሐዋ 2፥17)

ገጽ 211 “በዚያ ወራት በወንዶችና በሴቶች”
(የሐዋ 2፥18)

ገጽ 211 “መንፈስን አታጥፉ” (1ተሰ 5፥19-20)

ገጽ 211 “ሁሉን ፈትኑ፡፡ እውነቱን ያዙ ...” (1ተሰ 5፥21)

ገጽ 211 “ሁለት ወይም ሦስት ሆነው...” (1ቆሮ 14፥29)

ገጽ 212 “ሁሉም እንዲማሩ፤ ሁሉም እንዲመከሩ” (1ቆሮ 14፥31)

ገጽ 212 “የነቢያት መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ” (1ቆሮ 14፥32-33)

ገጽ 212 በኤፌሶን ይኖሩ የነበሩ ደቀመዛሙርት በልሣን ስለመናገራቸውና ትንቢትንም ስመናገራቸው (የሐዋ 19፥1-7)

ገጽ 213 “ወንጌላዊው ፊልጶስ ነቢያት የነበሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች እንደነበሩት (የሐዋ 21፥8-9)

ገጽ 213 አጋቦስ የተባለ ነቢይ ረሃብ እንደሚነሣና ጳውሎስም እንደሚታሰር ስለመተንበዩ (የሐዋ 11፥27-28፤ 21፥10-11)

ገጽ 213 "ለሌላውም መናፍስትን መለየት ... (1ቆሮ 12፥10)

ገጽ 214 "ሰይጣን ራሱን የብርሃን መልአክ ..." (2ቆሮ 11፥14)

ገጽ 214 "እግዚአብሔርም አለ እነሆ ስፍራ በእኔ ዘንድ ..." (ዘፀ 33፥21-33)

ገጽ 214 "ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት ..." (ኢሣ 6፥1-3)

ገጽ 214 የተርሴሱ ሰው ጳውሎስ በአንዲት ሠራተኛ ልጃገረድ ውስጥ የነበረውን የሟርተኝነት መንፈስ ስለመለየቱ (ሐዋ 16፥16-18)

ገጽ 214 መቶ አለቃው ቆርኔሊዎስ በራዕይ የታየው መልአክ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሆነ መለየቱ (የሐዋ 10፥1-48)

ገጽ 215 ለሌላውም በልዩ ዓይነት ልሣን የመናገር ... (1ቆሮ 12፥10)

ገጽ 215 "ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሣን ይናገራሉን?" (1ቆሮ 12፥30)

ገጽ 216 "በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ ..." (1ቆሮ 14፥26-28)

ገጽ 216 "መንፈስ እንዲያማ ካልሆነ አንተ ብትባርክ ..." (1ቆሮ 14፥16)

ገጽ 216 "ስለዚህም በልሣን የሚናገር::" (1ቆሮ 14፥13)

ገጽ 217 "ለአንዱም በልሣኖች የተነገረውን መተርጎም" (1ቆሮ 12፥10)

ገጽ 218 "ማኅበሩ ይታነፅ ዘንድ ..." (1ቆሮ 14፥5)

ገጽ 219 "ለተቀበሉት ሁሉ ግን ..." (ዮሐ 1፥12)

ገጽ 219 "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ" (የሐዋ 1፥8)

ገጽ 219 መንፈስ ቅዱስ በበዓለ ሃምሳ ቀን ከመውረዱ በፊት ደቀመዛሙርቱ በይሁዳ አጋንንትን ለማውጣት የመንግሥቱን ኃይል ስለመጠቀማቸው::" (ሉቃ 9፥1-6፤ 10፤ 10፥1-20)



ገጽ 220 "ንስሃ ግቡ ኃጢአታችሁም ..." (የሐዋ 2፥38)

ገጽ 220 "አባት ከሆናችሁ ከናንተ ማናችሁም ..." (ሉቃ 11፥11-13)

ገጽ 221 "የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛልና" (1ቆሮ 14፥32)

## ምዕራፍ ዐስራ ዐራት መላው ዓለም ገኸው የሚያስፈልገው ለምንድን ነው::

ገጽ 225 "ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለሙ ድረስ ..." (ኢሳ 9፥6-7)

ገጽ 226 "በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ..." (ኤፌ 2፥2)

ገጽ 226 "መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር ..." (ኤፌ 6፥12)

ገጽ 226 "ሐሰተኛ ክርስቶሶችና ሐሰተኛ ነቢያት ..." (ማቴ 24፥24)

ገጽ 226 "በጨለማ የተቀመጠ ህዝብ ..." (ማቴ 4፥16)

ገጽ 226 "ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ" (ሉቃ 1፥79)

ገጽ 227 "ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ..." (ዮሐ 1፥2-5)

ገጽ 227 "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" (ዮሐ 8፥12)

ገጽ 227 "እኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ አይኖርም" (ዮሐ 12፥46)

ገጽ 227 "የኃጢአትንም ሥርየት በእኔም በማመን ..." (የሐዋ 27፥17-18)

ገጽ 227 "ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ አሁን ግን" (ኤፌ 5፥8-9)

ገጽ 227 "እርሱ ከጨለማ ሥልጣን አዳነን ..." (ቆላ 1፥13-14)

ገጽ 228 "ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው" (ሮሜ 8፥6)

ገጽ 229 "አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን አየሁ ..." (ራዕ 21፥1-5)

ገጽ 229 "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን..." (1ጴጥ 2፥9-10)